# ሐመር

# ነገረ ምጽአት



## በውስጥ ገጾች


✞ ነገረ ምጽአት
✞ መከራ በክርስትና ሕይወት
✞ አባ ተከሥተ ብርሃን
✞ እንደ ራባቸው ሊሄዱ አይገባም (ማቴ.፲፬፥፲፮)
✞ ዘር ቆጣሪ
✞ ቤተ ክህነት እና ቤተ መንግሥት
✞ አሐቲ ቤተ ክርስቲያን
✞ ነገረ ጋብቻ (ከባለፈው የቀጠለ)



መጋቢት ፳፻፲፫ ዓ.ም.

# ሐመር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣
ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት
ጠብቆ የሚወጣ

## መጋቢት ፳፻፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመትና
ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዋና ክፍል
በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ
ትምህርታዊ መጽሔት




## ማውጫ


የማኅበሩ መልእክት
ከሰላም እንጂ ከግጭት የምናተርፈው ነገር የለምና ሁላችንም ለሰላም እንትጋ፤ ፫

ዐውደ ስብከት
መከራ በክርስትና ሕይወት ፭

ትምህርተ ሃይማኖት
ነገረ ምጽአት ፱

ዐቢይ ጉዳይ
ቤተ ክህነት እና ቤተ መንግሥት ፲

ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት
እንደ ራባቸው ሊሄዱ አይገባም ፳፮

እናስተዋውቃችሁ
ዐቃብያነ እምነት/ቀዋምያን ለቤተ ክርስቲያን ፲፱

የጥያቄዎቻችሁ መልስ ፳፪

ኪነ ጥበብ
ዘር ቆጣሪ ፴

የነገዋ ቤተ ክርስቲያን
አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ፴፭


፹ማኅበረ ቅዱሳን፹ እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና
አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይኽን ስያሜ
አግኝቷል።


## የዝግጅት ክፍሉ

ስልክ ፲፩፩-፳-፩፪-፪፳-፬፱
ፖ.ሣ.ቁ ፳፲፲፯፳
ኢ-ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት ስልክ
፲፩፩-፩-፭፭-፫፪-፫፱
የልማት ተቋም የስርጭት ክፍል ስልክ
፲፩፩-፩-፪፫፬፭-፪፱
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
፲፱፬፪-፫፳-፩፯-፱፩

ም/ዋና አዘጋጆች
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ
አድራሻ፡- ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ
ወረዳ ፲፭ የቤት ቁ. ፯፪፲

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ዲ/ን ኅሊና በለጠ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

ሌይ አውት ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሓፊ
ገነት ታደሰ

# ከሰላም እንጂ ከግጭት የምናተርፈው ነገር የለምና ሁላችንም ለሰላም እንትጋ!

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ  የሰላም እጦት እንደ ውኃ ጥም እያንገበገባት ትገኛለች። ምክንያቱን በተመለከተ እንኳንስ ችግሩ በቀጥታ የደረሰበት አካል ችግሩን ያደረሰውም ቢሆን ጉዳዩን ወደ ሌላ አካል መግፋት እንጂ የራሱ ችግር እንደሆነ አምኖ አይቀበልም። ይባስ ብሎም ቀድሞ በመጮኽ የተበደለና የተገፋ አድርጎ ለዓለም ያውጃል። ዓለም ደግሞ ቀድሞ የሚሰማውና ባይችልም መፍትሔ አመጣለሁ ብሎ የሚሞክረው ቀድሞ ለጮኸለት አካል ነው። ይህ ደግሞ እንደምንመለከተው ችግሩን የሚያባብስ እንጂ ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣ አይደለም።

በዋናነት ግን ሀገራችን እየተከተለችው ያለው የፖለቲካ ርእዮትና፣ ዓለማቀፋዊው የተሳሳተ ትርክት ሲሆን ከዚህም ባሻገር ሀገር በቀሎቹ እኩያን ወይም ጡት ነካሾች በሀገራችን ለሠላሳና ለአርባ ዓመታት የጥላቻ ንግግርና የሐሰት ትርክት፣ እንክርዳድን በትውልድ አእምሮ ላይ ሲዘሩ ኖረዋል። እኩያኑ የዘሩትን ራሳቸው ቢያጭዱት መልካም ነበር። የሚያሳዝነው እኩያኑ የዘሩትን ንጹሐኑ ያንኑ ማጨዳቸው ነው። ይህ ደግሞ አንዱ ሌላውን በጠላትነት እንዲመለከተው እያደረገ ወደ እርስ በእርስ ግድያና እልቂት አስገብቶናል። ለችግሩም መሠረታዊና ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ማምጣት ከማንችልበት ሁኔታ ላይ እንድንገኝ አድርጎናል።

በትግራይ፣ በማይካድራ፣ በመተከል፣ በወለጋ፣ ሰሞኑን ደግሞ በአጣየ አካባቢ የተከሠተው ችግር ሀገርንም ቤተ ክርስቲያንንም የሚጎዳት ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ቁርሾ (ዘላቂ ጠባሳ) ጥሎ የሚያልፍ እንጂ ማንም ቢሆን አንዳች ነገር የሚያተርፍበት ድርጊት አይደለም። ምን አልባት የሚያተርፍ አካል አለ ከተባለም የሰውን ሰላም የማይወደው፣ ሰይጣንና የግብር አበሮቹ ብቻ ናቸው። እንዲህ ያለውን መሠረታዊ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ  ከአንድ አካል ብቻ የሚጠበቅ ነገር አይደለምና ሁሉም በየድርሻው ሊታገለው ይገባል።

እንግዲህ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን የግጭት መንሥኤዎችና የሰላም ተግዳሮቶች በዘላቂነት በመፍታት የየራሳቸው የተለየ ድርሻ ካላቸው አካላት መካከል የመጀመሪያው መንግሥት ነው። ስለሆነም መንግሥት አሁን እየተከተለው ያለውን የፖለቲካ አካሄድ ቆም ብሎ በማጤን ችግሩን በአግባቡ ሊፈታ የሚያስችል ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ይኖርበታል። ችግር በተፈጠረ ቍጥር የርዳታ ቡድን እያቋቋሙ ለጊዜያዊ መፍትሔ መሯሯጡ ይህን ያህል የጎላ ጠቀሜታ የለውም። ነገሩ “ለሰጪም አያንሰው ለበይም አይደርሰው” ስለሚሆን መንግሥት በደከመውና በሮጠው ልክ ተጎጂዎችን መርዳት ሳይችል ይቀራል። ይህ ደግሞ ምንም እንኳን ብዙ ቢደክም የተጎጂዎችን ችግር ስለማይፈታ መልሶ ከትችትና ከወቀሳ ላይ ይጥለዋል። ይህ ማለት ግን ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ጊዜያዊ ርዳታም  ቢሆን አያስፈልግም ማለት አይደለም። ነገር ግን ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው ቆም ብሎ ከልብ ማሰብና የግጭት ምንጨን የሚያደርቅ ሥራ መሥራት ነው። አዳንዴ የጥፋት ቡድኖች የሚይዙት የጦር መሣሪያ፣ ያላቸው ቅንጅት፣ መረጃውን በፍጥነት ለሕዝብ ለማድረስና ግጭቱን ለማባባስ የሚንቀሳቀሱበት ፍጥነት ምን አልባትም በመንግሥት ውስጥ ያሉ አካላት ድጋፍ አለበት ብለን እስክንጠራጠር ድረስ የሚያደርሰን ሆኗል።

ወደ ፊት እየታሰበ ያለውን ሀገራዊ ምርጫም በሰላማዊ መንገድ ለማካሄድ ሰላም መቅደም አለበት። ሰው የህልውና ስጋት እያስጨነቀው ምረጡኝ ብሎ መቀስቀስም እንዲያው ለይስሙላ መንቀሳቀስ አልያም እኔ ከኖርኩ ምን ቸገረኝ የማለት ያህል ይመስላል። በእርግጥ “ዳሩ ሲፈታ መሀሉ ዳር ይሆናል” እንዲሉ አባቶች በሩቅ የምናየው የሚመስለን ችግር በአጭሩ

ካልተፈታ ነገ ከነገ ወዲያ መሀል ላይ የማይመጣበት ምክንያት የለም። ደግሞም መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ የዜጎችን ደኅንነት ማስጠበቅ ነውና በዚህ ላይ ጠንክር ብሎ ካልሠራ "ካልጠበቅሽው በላሽው" እንደሚባለው መንግሥት የሕዝብን ሰላም ካላስጠበቀ ሰላሜን ተነጥቄያለሁ ብሎ መንግሥት ላይ መጮኹ አይቀርም። ይህም ሁኔታ ከአጥፊዎች ባልተናነሰ ተጠያቂ ሊያደርገው እንደሚችል ማሰብ ይኖርበታል።

እነዚህን ሀገራዊ ችግሮች በዘላቂነት ከመፍታት አኳያ ሌላኛዋ ባለ ድርሻ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። እንደሚታወቀው ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት በቅዳሴዋ፣ በማሕሌቷ፣ በሥርዐተ አምልኮዋ ሁሉ ስለ ሰላም ያልጸለየችበት ጊዜ የለም። ይሁን እንጂ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማመልከቱ እንዳለ ሆኖ በሰው ሰውኛውም ከሚመለከተው አካል ጋር መሠረታዊ የሆነ ውይይት በማድረግ ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት መሥራት ይኖርባታል። እንደ ሀገረ ስብከት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ያሉ ቢሆንም ከችግሮቹ ስፋት አኳያ አጥጋቢ ናቸው ማለት አይቻልም። ሀገራዊ የሆነ ውይይት፣ በሲኖዶስም ሆነ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ደረጃ መደረግ ይኖርበታል። ችግር በተፈጠረ ቁጥር መግለጫ በመስጠት ብቻ ሳይሆን ከመንግሥት ጋርም በየደረጃው ጥልቅ ውይይት ማድረግና ዘላቂ የሆነ መፍትሔ የሚመጣበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል።

ሁል ጊዜ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ሌላው አይጠቃም ባይባልም የመጀመሪያዋ ተጠቂ ቤተ ክርስቲያን ናት። አባቶች ደግሞ ለቅዱስ ጴጥሮስ "በጎቼን ጠብቅ" ተብሎ የተሰጠው ኃላፊነት የእነርሱም ነው። ምንም እንኳን የአባቶቻችን መንጋን የመጠበቅ ኃላፊነት በቀዳሚነት ምእመናንን ከኃጢአትና ከክሕደት በመጠበቅ የጽድቅ ሥራን እንዲሠሩ በማድረግ መንግሥቱን እንዲወርሱ ማስቻል ቢሆንም ነፍስ የጽድቅ ሥራን የምትሠራው በሥጋ ህልውና ላይ ቆማ ስለሆነ ምእመናን በግፈኞች ሲገደሉ፣ አንድ ነገር ኮሽ ባለ ቁጥር ቤተ ክርስቲያን ስትቃጠል ዝም ብሎ ማየት ከተጠያቂነት አያድንምና እንደቀደሙ አባቶች ሳያፍሩና ሳይፈሩ መንግሥትን ድኃ ተበደለ ፍርድ ተጓደለ ተመለስ ሊሉት ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሀገርን ሰላምና ደኅንነት ከማስጠበቅ አኳያ የራሳቸው የሆነ ድርሻ ያላቸው ብዙ ሕዝብ የሚከተላቸውና ሐሳባቸውን የሚጋራቸው ፖለቲከኞች ናቸው። ይሁን እንጂ ፖለቲከኞች ዛሬ የሆነውንም ያልሆነውንም ወሬ በሕዝቡ አእምሮ ላይ እየነዙ ሰውን እርስ በእርስ አጋጭተን የፖለቲካ ጥቅም እናገኛለን የሚሉ ፖለቲከኞችን እየተመለከትን ነውና እነዚህ ፖለቲከኞች ይህ ዓይነት ድርጊታቸው ሊያጎድላቸው እንጂ ሊያተርፋቸው እንደማይችል መረዳት ይኖርባቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ "ስለዚያችም ምድር ክፉ የተናገሩ እነዚያ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት በመቅሰፍት ሞቱ" (ዘኁ.፲፬፥፴፯) ተብሎ እንደተጻፈ ክፉ ወሬ ለማንም አይጠቅምምና ቆም ብለው ሊያስቡበት ይገባል። ይልቁንስ ሕዝቡን እርስ በእርሱ እንዲተሳሰብ፣ ተከባብሮና ተዋድዶ እንዲኖር፣ በኢትዮጵያዊና በሰብአዊነት መንፈስ እንዲኖር ማስቻል ይገባል።

በመጨረሻም ሕዝቡ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ትርፍ እናገኛለን ብለው በሚያስቡትና በሚያወሩት ክፉ ወሬ እየተሰናከለ የማይጠፋ ጠባሳ ጥሎ ከመሄድ መቆጠብ ይኖርበታል። አንዳንዴ የሚነገር ሁሉ እውነት አይደለምና "ወሬያችሁን ለራሳችሁ አድርጉት" ሊላቸውም ይገባል። አብሮ ተሳስቦ የኖረ ሕዝብ፣ በኀዘኑም ሆነ በደስታው ጊዜ የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ልዩነት ሳይፈጥር አንድ ላይ የኖረ ሕዝብ በማኅበራዊ ሚዲያ በሚለቀቅ የጥፋትና የሐሰት ትርክት (ወሬ) ጉዳዩን ማባባስ አይገባምና ቆም ብሎ ማሰብ ይገባል። ደግሞም "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው" እንደሚባለው የመጣውን ወሬ ሁሉ እየተከተሉ ሀገርን ከማፍረስ መታቀብ ታላቅ ዋጋ አለው ። "ሀገራችንን ለወሬኞች፣ ለጠላት አሳልፈን አንሰጥም" ሊልም ይገባዋል።

ይህን ክፉ ወሬ ለወሬኞቹ በመተው ከየቦታቸው ተፈናቅለው፣ በብርድ ፣ በረኃብ፣ በጥም፣ ወዘተ. እየተሠቃዩ ያሉትን በኢትዮጵያዊነትና በሰብአዊነት መንፈስ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ጎሣ፣ ቀለም ወዘተ ሳንለይ ልንደርስላቸው ይገባል። በዚህም ሁሉ ተሳስበን በከንቱ ወሬ ሀገራችንን ከማፍረስ ተቆጥበን ክፉ ጠባሳን ሳይሆን መልካም ስምና መልካም ታሪክ ለመጪው ትውልድ ልናስተላልፍለት ይገባል። ✞ ✞ ✞

# መከራ በክርስትና ሕይወት

ዐውደ ስብከት

*ዲ/ን ደረጀ ድንቄ*

## መከራ ምንድን ነው?

መከራ ማለት ፈተና፣ ጭንቅ ማለት እንደሆነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላት መጽሐፋቸው ተርጉመውት እናገኛለን። (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፭፻፺፩) እንዲሁም ሊቀ ኅሩያን በላይ መኰንን ትንሣኤ አማርኛ-ግእዝ መዝገበ ቃላት በተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ ፈተና፣ ሀውክ፣ ሥቃይ የሚል አቻ ትርጉም ሰጥተውት እናገኛለን። (ትንሣኤ አማርኛ-ግእዝ መዝገበ ቃላት ገጽ ፳) ክርስቲያን ማለት ከውኃ እና ከመንፈስ በመጠመቅ ክርስቶስን የለበሰ ፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆነ ማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።›› (ገላ. ፫፥፳፯) እንዲል። ክርስቶስ ይህን ዓለም የወደደው ወይም ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር የገለጠው ደግሞ ራሱን ለመከራ አሳልፎ በመስጠትና በሥቃይ ውስጥ ነው። ጌታም ‹‹እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፤ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ›› (ማቴ. ፲፮፥፳፬) ሲል በሰጠው ትእዛዝ ውስጥ ክርስቲያኖች በጥምቀት ለለበሱት አምላክ ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡበት መንገድም መከራ እንደሆነ ልብ ይሏል! በአጠቃላይ የክርስትና ሕይወት ፍጹም የሆነ ሰማያዊ ደስታ የሚገኝበት ምድራዊ መከራ በዚህ ዓለም ሳለ የማይለየው ሕይወት ነው።

በአንድ ወቅት ጌታችን መከራ እንደሚቀበል ለደቀ መዛሙርቱ በሚነግራቸው ሰዓት፤ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹አይሁንብህ!›› (ማቴ.፲፮፥፳፪) ባለ ጊዜ ጌታችን ገሥፆት ነበር። ከዚህ ተግሣጽ በኋላ ግን ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ክርስትና እና መከራ አለመለያየት እንዲህ ይመክራል ‹‹ወዳጆች ሆይ በእናንተ መካከል እንደ እሳት ሊፈትናችሁ ስለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ›› ካለ በኋላ ይቀጥልና ‹‹የክርስቲያን ወገን እንደሆኑ መከራን መቀበል ግን፤ ስለዚህ ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር›› (፩ጴጥ. ፬፥፲፪-፲፯) ይላል። ቅዱስ ሉቃስም ‹‹ሐዋርያትንም ጠርተው ገረፉአቸው፤ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው››፤ በማለት ስለ ሐዋርያት ሥቃይ ከጻፈ በኋላ ‹‹እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ›› (ሐዋ. ፭፥፵፩) ይለናል። ሐዋርያት አካላዊ ሥቃዩ ሳይሰማቸው ቀርቶ ሳይሆን፤ የሁሉ ባለቤት ከሆነ አምላክ ጋር ዘወትር አብረው የሚሠሩ ናቸውና ልባቸው በሰማያዊው ደስታ ዕረፍትንና ሰላምን ያገኝ ስለ ነበር ነው። በእርግጥ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ›› (ዮሐ. ፲፮፥፴፫) በማለት በማያሻማ መልኩ በግልጽ ነግሮናል።

## መከራ ከየት ይመጣል?

አስቀድመን እንደጠቀስነው መከራ ስንል ሥቃይ፣ ሕመም፣ ደዌ፣ ቸነፈር፣ ጦርነት ወይም ሰላም ማጣት፣ ረኀብ ሊሆን ይችላል። መከራ የሚመጣባቸው መንገዶች የተለያዩ ሲሆኑ፤ ለዚህ ጽሑፍ የመከራን ምንጭ በሦስት ከፍለን እንመለከታለን።

**ሀ. ከራስ፡-** መከራ ከራሳችን የሥጋ ምኞት (ኃጢአት) የተነሣ ሊመጣ ይችላል፡ የሰው ልጅ ሥልጣን ለማግኘት፤ ገንዘብ ለማግኘት፤ ተቀባይነት አግኝቶ ታዋቂ ለመሆን፤ ራሱን ከሌላው አስበልጦ ለማስቀመጥ ካለው መሻት የተነሣ፤ ቀላል ወይም ከባድ መከራዎችን በራሱ ላይ ሊያመጣ ይችላል። እነዚህ ፍላጎቶች ኃላፊና ጠፊ ቢሆኑም እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚሄድበት መንገድ ግን ራስን እንዲሁም ብዙዎችን ለመከራ፣ ለሥቃይና ለችግር ሊዳርግ ችሏል። በዓለማችን ብሎም በሀገራችን ላይ ያየናቸው አሁንም የምናያቸው ጦርነቶች፣ የጅምላ ጭፍጨፋዎች፣ መጠፋፋቶች፣ ሕመሙ (ደዌው)፣ በዘር መከፋፈሉ ለዚህ ጥሩ ማስረጃዎች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን በኖኅ ዘመን የተፈጸመው ልዩ መከራና ጥፋት ከሰው ልጆች በደል የተነሣ የመጣ ነበር (ዘፍ. ፯፥፲)፤ በሰዶምና ገሞራ የሆነው ለዐይንም ለጆሮም እንግዳ የሆነው መከራና ጥፋትም ከሰው ልጆች ደካማ ምኞት ወይም ኃጢአት የተነሣ

የመጣ ነው (ዘፍ. ፲፱፥፳፬)፡፡ ለእስራኤላውያን የ፵ ቀን ጉዞ የ፵ ዓመት የሆነበት፤ ሕዝቡ በነዘር እባብ ተነድፎ ያለቀበት እንዲሁም ሌሎች ለገጠሟቸው ብዙዎቹ መከራዎች ምክንያት የሆነው የራሳቸው የፈቃድ ጥመትና ለፈጣሪ ሕግ አለመገዛታቸው ነው፡፡(ዘኁ. ፲፩፥፴፬፤ ዘኁ. ፳፩፥፯)

እንደ አንድ ግለሰብ ከተመለከትነው ደግሞ ትእዛዙን በመተላለፍ ሕጉን በመጣስ ከእግዚአብሔር እየለዩን ያሉት አብዛኛዎቹ ምክንያቶች የራሳችን ያልተገደቡ የሥጋ ምኞቶቻችን ናቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ‹‹ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም›› (፩ዮሐ. ፪፥፲፭) ይላል ፤ ቅዱስ ያዕቆብም ‹‹ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡›› (ያዕ. ፲፥፲፬) በማለት አንዱ የፈተናዎቻችን ወይም የመከራዎቻችን ምንጭ የራሳችን ምኞት መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

**ለ. ከዲያብሎስ፡-** መከራ ወይም ፈተና ከዲያብሎስ ሊመጣ ይችላል፡፡ ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ጌታችን ፊት ነሥቶ አሳፍሮ መለሰው እንጂ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ዲያብሎስ በትዕቢት፤ በፍቅረ ንዋይና በስስት ፈትኖት ነበር፡፡ ቅዱስ ሉቃስ ይህን ሲገልጠው ‹‹ዲያብሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ›› (ሉቃ.፬፥፲፫) ይላል፡፡ ዲያብሎስ ሥራውን ይሠራ ዘንድ የእኛን ደካማ ፍላጎት መሣሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ‹‹ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፤ ለዲያብሎስም መንገድ አትስጡት›› (ኤፌ.፬፥፳፯) ይላል፡፡ ይህም ዲያብሎስ በደካማ ፍላጎታችን ወይም ምኞታችን ተጠቅሞ ፈተናና መከራ ሊያመጣብን እንደሚችል የሚጠቁም ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በወንድማማች መካከል ያለን ፍቅር ማጣት ዲያብሎስ ለበለጠው መከፋፈልና መለያየት ይጠቀምበታል፡፡ በሰዎች መካከል ያለን የቃላት ጦርነት፤ ከፍ ወዳለው ፍጹም መጠላላት እና አካላዊ መጠፋፋት ያሳድገዋል፡፡

ሌላው ደግሞ እንደ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት መወደድና ክብር ሲኖረን፤ ሰይጣን ያለ ዕረፍት ጽኑዕ መከራዎችን ያመጣብናል ‹‹ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፤ ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቁስል መታው›› (ኢዮ. ፪፥፯) ይላል፡፡ መጽሐፍ ‹‹ባለጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና›› (፩ጴጥ. ፭፥፰) እንዲል፤ ባለጋራችን ፈተና እና መከራን በማብዛት ምርኮን ያገኝ ዘንድ ያለ ዕረፍት ዘወትር ይተጋል፡፡

**ሐ. ከእግዚአብሔር፡-** መከራ ለበረከትና ለሰማያዊ ዋጋ ከእግዚአብሔር ሊመጣ ይችላል፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይሠዋለት ዘንድ አዝዞት ነበር፤ ይህ ለአብርሃም ከእግዚአብሔር የቀረበ ትልቅ አስጨናቂ ፈተና ነበር፡፡ (ዘፍ. ፳፪፥፩-፲፭) ፤ አብርሃም ግን የታዘዘውን ለመፈጸም በእግዚአብሔር ፊት የእምነቱን ታላቅነት ገልጧል፡፡ በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን የሐዋርያትን እምነት ሲፈትን እናገኛለን፡፡ ጌታችን ወደ ታንኳ ገብቶ ከተኛ በኋላ ፤ ታንኳይቱ በማዕበል ተጨንቃ ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርቱም ከመጨነቃቸው የተነሣ፦ ‹ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን› እያሉ አስነሡት፡፡ ‹‹እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፡፡ ከዚህ በኋላም ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ›› (ማቴ. ፰፥፳፫) ይላል፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ነገ ትልቁን መከራ ይቀበላሉና፤ ከወዲሁ በፈተና ውስጥ ማለፍን ያለማምዳቸው ዘንድ እንዲሁም መከራ የመሸከም አቅማቸውን ለማሳደግ ይህን ፈተና ለእነርሱ አቀረበላቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ‹‹የዚህን ዓለም ድል ነሺዎች ሐዋርያትን ብቻ ይዞ ወደ መርከብ ገባ›› በማለት፤ ጌታችን ወደ ታንኳው ከመግባቱ አስቀድሞ ብዙ ሰዎች የተከተሉት ቢሆንም በታንኳው ለሚመጣው መከራ ግን የተመረጡት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ መሆናቸውን ይገልጣል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የሆኑ ፈተናዎችን ‹‹ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል፡፡›› (፩ቆሮ.፲፥፲፫) ሲል ይገልጠዋል፡፡

## በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔር ዝምታ

በቅዱስ ወንጌል እንደተገለጠው ፤ ታንኳይቱን ማዕበል እስኪደፍናት ድረስ በሆነው ፈተና ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ ተጨንቀው ሳለ ጌታችን ግን ተኝቶ ደቀ መዛሙርቱ እስኪቀሰቅሱት ድረስ አልተነሣም ነበር፡፡ (ማቴ. ፰፥፳፫)

በአስጨናቂ ማዕበል ውስጥ ሆኖ መንቃት የሌለበት እንደምን ያለ እንቅልፍ ነው? ሳያውቅ ቀርቶ ነው እንዳንል ጌታችንም ከእንቅልፉ እንደተነሣ፤ ‹ምን ተፈጠረ? ምንስ አገኛችሁ?› አላለም፤ ይልቁንም ‹እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ?› አላቸው እንጂ። የእግዚአብሔር ዝምታ ካለማወቅ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ መሆኑን ነቢዩ ‹‹እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር።›› (ኤር. ፳፫፥፳፫) በማለት ይናገራል። ጥበበኛው ቅዱስ ሰሎሞንም ምንም ክርስቶስ በሥጋው ተኛ ቢባልም በመለኮቱ ግን ሁሉን አዋቂ መሆኑን ‹‹እኔ ተኝቻለሁ፥ ልቤ ግን ነቅቶአል›› (መኃ. ፭፥፪) በማለት ይገልጠዋል።

በኪዳን ጸሎት ላይ ‹‹እምቅድመ ሕሊና ኵሎ የአምር፤ ወእምቅደመ ሕሊና ይፌትን ወዘእንበለ ንስአሎ ይሁብ ፍትወተነ፤ ከሕሊና አስቀድሞ ሁሉን የሚያውቅ፤ ከሐሳብ አስቀድሞ ሁሉን የሚመረምር፤ ሳንለምነው የምንሻውን አውቆ የሚሠጠን›› (ኪዳን ዘነግህ ክፍል ፪) ይላል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ደቀ መዛሙርቱ እስኪቀሰቅሱት ድረስ የክርስቶስን ከእንቅልፍ አለመነሣት እንዲህ ይገልጠዋል ‹‹እግዚአብሔር የምንፈልገውን ሳንነግረው ያውቀዋል፤ ጸሎት የምናደርገው እግዚአብሔርን ልንመራው ወይም ልናዝዘው አይደለም፤ ይልቁንም እኛ ስንለምን እርሱ እና እኛ መካከል ያለው ግንኙነት ይገለጥ ዘንድ፤ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ስንለምነው ትሕትናን ገንዘብ እንድናደርግና ኃጢአታችንን እናስታውስ ዘንድ ነው›› ይላል። (The Nicene and Post Nicene Fathers Volume 10 First Series; Chrysostom: Homilies on the Gospel Of St. Mattew; Page 290)

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ዝምታ አሕዛብ እንኳን ‹‹እውነት በእነርሱ ዘንድ የለችም፤ ፈጣሪያቸውም የለም›› ብለው እስኪናገሩ ድረስ ሊደርስ ይችላል። የንጹሓን ደም መፍሰስ፤ የአብያተ ክርስቲያናት እና ንዋያተ ቅድሳት መንደድ፤ የአገልጋዮች ሥቃይና ሞት፤ የሴቶች እና ሕፃናት መደፈር መነወር፤ እነዚህ ሁሉ ሲሆኑ ‹‹አሕዛብ አምላካቸው ወዴት ነው? እንዳይሉ፤ የፈሰሰውን የባሪያዎችህን ደም በቀል በዓይኖቻችን ፊት አሕዛብ ይወቁ›› (መዝ. ፸፰፥፲) እስከንል ድረስ እግዚአብሔር ዝም ሊል ይችላል። ወዳጄ ሆይ! እግዚአብሔር እንኳን የገጠመህን፣ በልብህ ያለውን አልፎም ስለነገህ ያውቃል! ነገር ግን የአንተን ድርሻ እንድትወጣ፣ የእምነትህንም ጽናት ያይ ዘንድ ይፈልጋል፤ ነገሩ ቢከብድህ የማይቻልህ ቢሆን በጸሎትህ ቀስቅሰው፤ እርሱ ጥያቄዎችህን ሁሉ ይመልሳል። ቅዱስ ጳውሎስ እና በርናባስ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል›› (ሐዋ.፲፬፥፳፩) ያሉትንም ዘወትር አትርሳ!!!

## በመከራ ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር አብሮነት

መከራ እና ፈተና ሲበዛ ‹‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን እንጂ እንዲህ አንሆንም ነበር›› ብለን ራሳችንንም ሰዎችንም እንሞግታለን። እውነት ነው! በኃጢአታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር በመራቃችን የሚመጡብን መከራዎች አሉ፤ እንዲህ ያሉ ፈተናዎችን ንስሓ ገብቶ ማሳለፍ ይገባል፤ ይህ ማለት ግን ሁሉም ፈተናዎች ከኃጢአት ብቻ የተነሣ ይመጣሉ ማለት አይደለም፤ ንስሓ ገብተን ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት እየኖርን ፈተናና መከራ ሊበረታብን ይችላል። በተጨማሪም የመከራ መደራረብና የፈተናዎች መብዛት የእግዚአብሔርን ከእኛ ጋር አለመኖር አያሳይም።

ፈጣሪ እያለ ፍጡር ሲጨነቅ ፤ ክርስቶስ እያለ ማዕበል ሲበረታ ‹‹"ክርስቶስ ከእኔ ጋር ባይኖር እንጂ ፈተና ባልበዛብኝ ነበር" አትበል። እርሱን ስትከተል ከእርሱ ጋር ስትኖር የእርሱ የሆነው መስቀሉም ከአንተ ጋር ነውና፤ ልብህን አታዘናጋ! "ፈልጎ ያገኘህ በመስቀሉ ነውና፤ አንተም ፈልገህ የምታገኘው በመስቀሉ ነው!።›› አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመጽሐፈ ምሥጢር ‹‹ልብ ሰነፎች ሆይ! (በጴጥሮስ ልብ ውስጥ ያለውን) መከራ አለመቀበልንና አለመሞትን ስላልወደደለት ጴጥሮስን እንደገሠጸው አትሰሙምን?›› (መጽሐፈ ምሥጢር ምዕራፍ ፲፭፥፲) በማለት መከራ መንፈሳዊ ትርጉም ያለው መሆኑን ይነግረናል። ሁላችንም በልጅነታችን ምሥጢራትን ስንካፈል፤ የክርስቶስ ቤተ መቅደስ ሆነን እርሱ በእኛ ውስጥ አድሯል፤ በእኛ ውስጥ ያለውን ጌታ የምንወደው ከሆነ፤ መስቀሉን ተቀብለን እኛ እንሸከመው፤ ‹‹ሊከተለኝ የሚወድ ሰው ራሱን ይካድ ጨክኖም የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ዕለት ዕለትም ይከተለኝ›› (ሉቃ. ፱፥፳፫) እንዳለ መድኃኔ ዓለም። በመሆኑም እግዚአብሔርን የያዙ ሰዎች የበለጠ ይፈተናሉ። ምሳሌ የሌላት እመቤታችን ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን ለሚመጡብን መከራዎች መሪያችን ምሳሌያችን ናት። ደቀ መዛሙርቱም ‹‹እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር

ነኝ›› ያለውን አምላክ ይዘው፤ ብዙ ጭንቅና መከራዎችን ተቀብለዋል፡፡

## በመከራ የመጽናት ዋጋ

በኃጢአት ምክንያት የሚያገኘን መከራ፤ ለሰማያዊው ሕይወት የእግዚአብሔር የንስሓ ጥሪ መሆኑን ዘወትር ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹የሚቴን ሞት አልፈቅድምና፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ፡፡›› (ሕዝ. ፲፰፥፴፪) ይላል፡፡ ስለዚህ በኃጢአት ምክንያት የሚመጣን መከራ ንስሓ በመግባት መሻገር ይገባል፡፡

በመከራ ውስጥ መጽናት በምድር ልዩ ልዩ ጸጋዎችን የሚያስጠን፤ በሰማይ ደግሞ ሰማያዊ አክሊል የምናገኝበት ነው፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ ‹‹በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና›› (ያዕ. ፩፥፲፪) ይላል ፤ ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ ‹‹አሥር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ ፤ እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ›› (ራእ. ፪፥፲) በማለት በመከራ የሚገኘውን ክብር ይገልጸዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ባህል አሥር ቊጥር ሙሉ ፍጹም ነገርን ይወክላል፤ ስለዚህም ክብርና ዋጋ ከመቀበል በፊት መከራው ፍጹምና ሙሉ እንደሚሆን ባለምሥጢሩ ሐዋርያ በምሥጢር ነገሮናል፡፡

በመከራ ውስጥ ጸንቶ ሰማያዊ ዋጋ ለመቀበል ፤ አንደኛው መሠረታዊ ነገር ጸሎት ነው፡፡ የሰው ልጅ ለመኖር መተንፈስ አለበት፤ ሰው አየር ካጣ መተንፈስ ካልቻለ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች፤ አየርን በኋላ እፈልገዋለሁ የሚል የለም፡፡ ያለምንም የጊዜ ገደብ የሰው ልጆች ይሹታል፡፡ አየር የዚህን ያህል ካስፈለገ፤ አየርን የፈጠረ አምላክ ለሰው ልጆች ምን ያህል ያስፈልግ ይሆን? ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ [For we ought to think of God even more often than we draw our breath› ‹‹እግዚአብሔርን ከምትተነፍሰው አየር በላይ አስታውሰው›› (Gregory of Nazianzus on The Five Theological Orations; Page 4)] ይላል፡፡ እንደ አንድ ክርስቲያን ስለ አሁን፣ ስለወደፊት፤ ስለተደረገልን፣ ስላልተደረገልን፣ ስለሚደረግልን ነገር ሁሉ እንድንጸልይ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ቅሊማቆስ ‹‹የጸሎትን በትር በእጃችሁ ከጨበጣችሁ አትወድቁም፤ ብትወድቁም አወዳደቃችሁ ለሞት የሚያደርስ አይሆንም›› (John Climacus, On the Ladder of Divine Ascent) ሲል ይመክረናል፡፡ እንኳን ፈተና ገጥሞን ይቅርና በደኅናው ሰዓትም አንድ ክርስቲያን ከጸሎት ሕይወት መለየት እንደሌለበት፤ ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ‹‹ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ›› (ማቴ. ፳፮፥፵፩) በማለት ካዘዘን ከጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከትሎ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሳታቋርጡ ጸልዩ›› (፩ተሰ. ፭፥፲፯) በማለት ይመክረናል፡፡ እንዲሁም በሐዋርያት እግር የተተኩ ቀደምት ሊቃውንትም ያስተማሩን ጸሎት ከክርስቲያን ሕይወት ሊለይ የማይገባው መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

> **‹‹በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና››**

በአጠቃላይ እውነተኛ አማኝ የሆነ ሁሉ በዚህ ዓለም ስላለው መከራ፣ የመከራ መምጫ፣ በመከራ ጊዜ እግዚአብሔር ለምን ዝም እንደሚል፣ በመከራ መታገሥ ሊያስገኘው የሚችለውን ጸጋ ወዘተ. ሁሉ በአግባቡ በመረዳት መርከብ በተባለች ቤተ ክርስቲያን በመጽናት፣ የመርከቧን ቀዛፊ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የዚህን ዓለም ፈተና ሁሉ በማለፍ ወደብ ከተባለችው ከመንግሥተ ሰማያት ሊያስገባ የሚያስችለውን ኦርቶዶክሳዊ ሕይወት መኖር ይገባል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ መስቀሉን ይዘን ጌታችንን በመከራው መስለነው፤ በትዕግሥትና በጽናት ቆመን መንግሥቱን ለመውረስ ያብቃን!!! ✞ ✞ ✞

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ነገረ ምጽአት

## ትምህርተ ሃይማኖት

*በመ/ሐ ምሥጢረ ሥላሴ ማናየ*

የሰው ልጅ የመጀመሪያ ተስፋ የወልደ እግዚአብሔር አካላዊ ቃል ቀዳማዊ ምጽአቱ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም ልኡካነ ቃል ነቢያትን አስነሥቶ በሥጋ እንደሚመጣ አናገረ፤ ነቢያት የወልደ እግዚአብሔርን መምጣት በብዙ ኅብረ ትንቢት እና ኅብረ ምሳሌ አስተማሩ፤ ስለቀዳማዊ ምጽአቱ ትንቢት ተናገሩ፤ ሱባኤ ቆጠሩ፤ የሰው ልጅ ልቡና የፈጣሪውን መምጣት በተስፋ ሰነቀ። በምጽአቱ የሚያገኘውን ድኅነት በተስፋ ጠበቀ። የተናገረውን የማያስቀር የማያደርገውን የማይናገር አምላክ ዘመኑ ሲደርስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በብሥራተ መልአክ ተወለደ፤ ይህ የመጀመሪያ ምጽአት ይባላል። ‹‹ዘመኑ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ›› እንዲል ገላ.፬፥፬።

ይህ አመጣጥ የዓለምን ገጽታ የቀየረ ለዘመናት በሰው ልጅ ላይ ጸንቶ የነበረውን መርገም የሻረ ከገነት ተሰዶ የነበረውን የሰው ልጅ ወደገነት የመለሰ የአረጀውን ዓለም ያደሰ የረከሰውን የሰው ልጅ ሕይወት የቀደሰ ልጅነትን በሃይማኖት የሰጠ መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን ያጠፋ ሞትን የገደለ የሰው ልጆችን ክብር የገለጠ ምጽአት ነው። በዚህ ግሩም ትሕትናውን አሳይቶ አምላክ በሥጋ በተገለጠበት ቀዳማዊ ምጽአቱ ሰው ሆኖ በመወለዱ ዓለም ያገኘውን ሕይወት መዘርዘር ያገኘውን ጸጋ መናገር በቁጥር የሚወሰን ስላልሆነ ይህን ያህል ነው ማለት አንችልም። እንዲያው በጥቅሉ የሰው ልጅ ከሞት ባርነት ከኃጢአት ተገዥነት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ ከመቅረት ነጻ የወጣው በቀዳማዊው ምጽአተ ወልደ እግዚአብሔር ነው።

የሰው ልጅ ፍቅር ስቦት ሰውን መውደዱ አገብሮት አምላክ ወዶ ፈቅዶ ሰው ሆኖ መጥቶ የሰውን ሁሉ መከራ ተቀብሎ አዳነን። ‹‹ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ፣ ደዌያችን ወሰደ ሕማማችን ተሸከመ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን›› (ኢሳ.፶፫ ፥፭) እንዲል።

ደዌ ሥጋን በተአምራት ደዌ ነፍስን በትምህርት ቀጣልን የደዌ የሕማማት ምንጭ የነበሩ አጋንንትን ድል ነሣልን። ሞታችንን ሞቶ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን ‹‹ዘዚኣነ ሞተ ነሥአ ወእንቲኣሁ ሕይወተ ወሀበነ፤ የእኛን ሞት ወስዶ የእሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን›› (እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ) በዚህ መንገድ ወገኖቹ አደረገን በሐዲስ ተፈጥሮ እንደገና ፈጠረን ከብሉይ ሰውነት አውጥቶ በሐዲስ ሰውነት አጽንቶ ሐዲስ ሕግ ሠራልን በቅዱስ ኑሮ መመላለስ እንችል ዘንድ በቅዱስ ቃሉ ‹‹ንዑ ትልውኒ፤ ኑ ተከተሉኝ›› ብሎ ጠራን ‹‹እናንተ ሸክም የከበደባችሁ ወደእኔ ኑ እኔ አሳርፋችኋለሁ›› (ማቴ.፲፩፥፳፰) ብሎ ሸክም የከበደበትን ዓለም ወደ እርሱ ወደ ሠርጉ ቤት ጠራው ቅዱስ ኑሮን ለሰው ልጅ አስተማረ ‹‹እኔ የዋህ ነኝ ከእኔ ተማሩ ለነፍሳችሁ ዕረፍትን ታገኛላችሁ›› በማለት አስተማረ። (ማቴ.፲፩፥፳፰-፴)

ጌታችን በመጀመሪያው ምጽአቱ እንዴት መኖር እንደሚገባን ለሰው ልጆች ሁሉ አስተማረን እንድንከተለውም ፍለጋውን ተወልን ‹‹ፍለጋውን እንከተል ዘንድ ምልክቱን ተወልን›› (፩ኛ ጴጥ.፪፥፳፪) እንዲል። በዚህ መንገድ እርሱን ተከትለንና መስለነው እንድንኖር መኖሪያ ቤት ቤተ ክርስቲያንን መመሪያ ሕግ የፍቅርና የትሩፋት ሕግ ወንጌልን ሰጠን የሚመሩ ሐዋርያትን፣ ጳጳሳትን፣ ሊቃውንትን የምንበላውን ቅዱስ ሥጋና የምንጠጣውን ክቡር ደሙን በነጻ ያለ ዋጋ በቸርነቱ አድሎን ይህን አድርጎ ዳግመኛ እንደሚመጣ ነግሮን ወደ ሰማያት ዐረገ በአባቱ ቀኝ (ዕሪና) ተቀመጠ።

ስለዚህ አሁን የሰው ልጅ የሚጠብቀው የወልደ እግዚአብሔርን ዳግም ምጽአት ነው። ይህም የሁሉም ፍጻሜ የሚሆንበት ወልደ እግዚአብሔር በቀዳማዊ ምጽአቱ መጥቶ በሰጠው ሕግ በአስተማረው ትምህርት መሠረት ለሠራነው መልካምም ሆነ ክፉ ሥራ ዋጋ ለመስጠት እንደ ቀድሞው ለትምህርት ሳይሆን እንደየሥራችን ለመክፈል ይመጣል። ይህ የጌታችን ዳግም መምጣት የሁሉ ፍጻሜ ነው የሚታየው ዓለም ያልፍበታል የሚመጣው ዘለዓለማዊ ዓለም ይገለጥበታል ቀዳማዊ ምጽአቱ ዘር ደኃራዊ ምጽአቱ መከር ነው በዘር ጊዜ ገበሬ መከራ እንደሚበዛበት ጌታችን በመጀመያው ምጽአቱ ለመከራ ነው የመጣው። በትሑት ሰብእና በመገለጡ ይህ

ዓለም ንቆታል፤ አቃሎታል፤ መዘባበቻም አድርጎታል፡፡ ‹‹ጋኔን አለበት ለምን ታደምጡታላችሁ?››፤ በብኤልዘቡል ያወፅኦሙ ለአጋንንት አጋንንትን በብኤልዘቡል በአጋንንት አለቃ ነው የሚያወጣቸው›› ዮሐ.፲፥፳፤ ማቴ.፲፪፥፳፬፡፡ እየተባለ ተዘበተበት፡፡ ይህን ሁሉ ጽርፈት በትሕትና ተቀብሏል፡፡ በቀዳማዊ ምጽአቱ ኃጢአተኛውን ዓለም በንስሓ ሊጠራ ነው የመጣው ፡፡ ‹‹ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም ኃጥኣንን ለንስሓ ልጠራ መጣሁ እንጂ›› ማቴ.፱፥፲፫ እንዲል፡፡

አሁን ዳግመኛ የሚመጣው ግን እንደቀድሞው ዓለምን በትሕትና ለመጥራት ሳይሆን የመከር ጊዜ ነውና ስንዴውን ከገለባው፣ ገለባውን ከፍሬው፣ እንክርዳዱን ከስንዴው፣ ስንዴውን ከእንክርዳዱ፣ ወዘተ ለይቶ ስንዴውን በጎተራው ሰብስቦ እንክርዳዱን እና ገለባውን በእሳት ሊያቃጥል ነው፡፡ መከር እንደዚያ ነውና ‹‹እንክርዳዱን ስትነቅሉ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉ አይሆንም ተውአቸው እስከ መከር አብረው ይደጉ በመከር ጊዜ አጫጆችን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በየነዶውም አስራችሁ በእሳት አቃጥሉት ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ›› (ማቴ.፲፫፥፳፱-፴) እንዲል፡፡

ከላይ ያየነው በሰም አነጋገር የተገለጠው የጌታችን ትምህርት እንክርዳድ በሚል የገለጣቸው የንስሓ፣ የመልካም ሥራ ፍሬ የሌላቸውን ኃጥኣንን ነው፡፡ ለመሥዋዕት በተመረጠው ስንዴ የመሰላቸው ደግሞ ጻድቃንን ነው፡፡ እሳት የተባለው ለዲያብሎስ እና ለሠራዊቱ የተዘጋጀው የዲያብሎስ የግብር ልጆች ዲያብሎስን መስለው ተከትለው የሚገቡበት ገሃነመ እሳት ነው፡፡ ጎተራ የተባለው ደግሞ ስንዴ በሚል ስም የተገለጡት ጻድቃን የሚወርሱት መንግሥተ ሰማያት ነው፡፡ ስለዚህ የጌታ ዳግም ምጽአት ለኃጥኣን መከራን ለጻድቃን ደስታን የሚያጐናጽፍ ነው፡፡

ከላይ በምሳሌ የገለጠውን በግልጽ እንዲህ በማለት ተርጉሞታል፡፡ ‹‹እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ነው፤ እርሻውም ዓለም (ሰው) ነው፤ መልካም ዘር የተባሉ የመንግሥት (የወንጌል) ልጆች እንክርዳዱም የክፉ ልጆች ናቸው የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፡፡ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው አጫጆች መላእክት ናቸው፡፡ እንግዲህ እንክርዳዱ ተለቅሞ እንደሚቃጠል በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) መላእክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሏቸዋል፡፡ በዚያ ለቅሶና ጥር ማፋጨት ይሆናል፡፡ በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ›› እንዲል ማቴ.፲፫፥፴፯-፵፫፡፡

ከላይ ባነበብነው መሠረት ለኃጥኣን ፍዳቸውን ለጻድቃን ዋጋቸውን (ክብራቸውን) ለመስጠት ይመጣል እንዲህ ከሆነ የእንክርዳድነትን ጠባይ አስወግደንና ተዘጋጅተን ንስሓ ለመቀበል መትጋት አለብን ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ጌታ የዘራውን ንጹሕ ዘር ይሰበስባል ዲያብሎስም የዘራውን እንክርዳድ ይለቅማል የኔ ሕይወት የትኛው ላይ ይሆን ብለን ራሳችን ግብራችንን መመርመር አለብን፡፡

## ፩. ዳግም ምጽአት በነቢያት

ቅዱሳን ነቢያት ዋናው የተልዕኳቸው ማእከል የቀዳማዊ ምጽአቱን በተስፋ ትንቢት ለሰው ልጆች ማወጅ ነው፡፡ እንዲሁም ይመጣል ብለው በትንቢት የተናገሩለት አምላክ እንደሚመጣ ወደ ሰማያት በክብር እንደሚያርግ ዳግም ለፍርድ እንደሚመጣ የወጉት ሁሉ እንደሚያዩት ለእያንዳንዱ ዋጋውን እንደሚከፍል አስተምረዋል በጥቂቱ እንመልከት፡፡

የእግዚአብሔር ሰው ሄኖክ ‹‹እግዚአብሔር ይፈርድ ዘንድ ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ ይመጣል ለሁሉ እንደየሥራው ይከፍለዋል ስለ ሠሩት ኃጢአታቸው ኃጥኣንን ይዘልፋቸዋል በእርሱ ላይ የማይገባ ነገር የተናገሩትን ሁሉ›› (ሄኖ.1፥9) በማለት ተናግሯል፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም ‹‹እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል መጥቶም ዝም አይልም እሳት በፊቱ ይነዳል ከላይ ሰማይን ይጠራታል በሕዝቡ ይፈርድ ዘንድም ምድርንም ይጠራታል›› መዝ.፵፱፥፪ በማለት አስረዳቷል፡፡ ይህ ማለት ሰማይ ልዑላኑን መኳንንትን መሳፍንትን የምድር ገዥዎችን የሚመለከት ሲሆን ምድር ያላቸው ደግሞ ትሑታንን ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ በዳግም ምጽአቱ ለፍርድ በፊቱ ያቆማቸዋል፡፡

የእግዚአብሔር ነቢይ ዘካርያስ ‹‹በዚያም ጊዜ (ቀን) እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ተራራ ይቆማሉ›› (ዘካ.፲፬፥፬) በማለት ተናግሯል፡፡ ነቢዩ ዘካርያስ ምጽአቱ የሚደረግበት የምጽአቱ ምሥጢር መገለጫ ደብረ ዘይት የተባለው ተራራ መሆኑን ጭምር

ገልጧል፡፡ ይኸውም ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ፳፬፥፫ ጀምሮ በደብረ ዘይት ምሥጢረ ምጽአቱን ሲያስተምር ምጽአቱ የሚከናወነው በዚያ ሥፍራ መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሯል፡፡ ስለዚህ ዳግም ምጽአቱ በነቢያት ትንቢት ተነግሯል ማለት ነው፡፡ አምላክ ሰው ሆኖ ከአከናወነው ነቢያት ያልተናገሩት ምን አለ? እግዚአብሔር ገልጦላቸው ተናገሩ፤ የተናገሩትንም አምላክ ሰው ሆኖ ፈጸመው፡፡ ከተናገሩት መካከል ያልተፈጸመው ገና የሚፈጸም የምንጠብቀው ተስፋ የምናደርገው ዳግም ምጽአቱ ነው፡፡ ይህም የሁሉ ፍጻሜ የዓለም መጨረሻ የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ የአዲሱ ሕይወት መጀመሪያ ነው፡፡

ያን ጊዜ ጻድቁ (እውነተኛው) መከራ በአጸኑበትና ድካሙን በካዱ ነገሩን በናቁ ሰዎች ፊት በብዙ መገለጥ ይቆማል በግርማ እና በክፉ ማስፈራራት ሆኖ ባዩት ጊዜ ይታወካሉ፡፡ ድንቅ ስለሚሆን ደኅንነቱ ይደነቃሉ እየተጸጸቱና በተጨነቀ መንፈስ እየጮኹ እርስ በእርሳቸው ይናገራሉ እንዲህም ይላሉ ‹‹ቀድሞ በእኛ በሰነፎች ዘንድ መሳለቂያ መሽሚጠጫ የሆነው ሥራውን ስንፍና፣ ሞቱንም የተናቀ ያደረግንበት ይህ ነውን? እንዴት የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ? ርስቱስ እንዴት ለቅዱሳን ሆነች? ስለዚህ ከቀና መንገድ ወጥተን ስተናል፤ የጽድቅ ብርሃንም አልተገለጠልንም፤ ፀሐይ አልወጣልንም፤ በደልን እና ጥፋትን በመንገዳችን ሞላን፤ በምድረ በዳም ሄድን የእግዚብሔርን መንግሥት አላወቅንም፤ ትዕቢት ምን ጠቀመን? ከትዕቢት ጋር ያለ ባለጠግነትስ ምን አመጣልን? ይህ ሁሉ እንደ ጥላ ኃላፊ ነው›› ጥበ.፭፥፩-፱፡፡

## ፪.ዳግም ምጽአት በሐዋርያት

የነገረ ምጽአት ትምህርት ምንጩ ቀዳማዊው ምጽአቱ ነው ይህን ቀዳማዊ ምጽአት ቅዱሳን ሐዋርያት በዐይናቸው አይተዋል፤ የቃሉን ትምህርት በጆሯቸው ሰምተዋል፤ በእጃቸው ዳሰውታል፤ ከዋለበት እየዋሉ ካደረበት እያደሩ የእጁን ተአምራት እያዩ ለጌታችን ከአቀረቧቸው ጥያቄዎች መካከል ነገረ ምጽአት፣ የዓለም መጨረሻ፣ ምልክቶቹ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የነገረ ምጽአት ትምህርት በቅዱሳን ሐዋርያት ጠያቂነት በጌታችን መልስ ሰጭነት የተሰጠ ምሥጢራዊ ትምህርት ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ድንቅ የመምጣቱን ምሥጢር አስተምሯቸዋል እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጽፈው አቆይተውልናል ጥቂቶችን እንመልከት፡፡ ‹‹ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ መልሶ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንግዲህ ዋጋችን ምን ይሆን›› አለው ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ የተከተላችሁኝ እናንተ በዳግም ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ እናንተም በዐሥራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ በዐሥራ ሁለቱም ነገደ እስራኤል ትፈርዳላችሁ›› ማቴ.፲፱፥፳፯ በዚህ ጥያቄ ጌታችን በዳግም ምጽአቱ ቅዱሳን ሐዋርያት የሚያገኙትን ዋጋ እና ከፍ ያለ ክብር ያስተማረበት ነው፡፡ ይህን ምጽአት እየናፈቁ በትጋት እንዲያገለግሉት አስተምሯቸዋል፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት የነቢያትን ትንቢት የተረጎሙ በቀዳማዊ ምጽአቱ ነቢያት ለዘመናት ሊያዩት የተመኙትን ያዩ ነቢያት ሊሰሙት የወደዱትን የሰሙ፣ ፈጣሪያቸውን በእግር ተከትለው በግብር መስለው የእጁን ተአምራት ያዩ፣ የቃሉን ትምህርት የሰሙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የከበሩ፣ የጨለማውን ዓለም በወንጌል ብርሃንነት ያበሩ፣ ክርስቶስን መስለው ሰማዕትነትን ያስተማሩ፣ በዓለም ዳርቻ የተበተኑትን የሰው ልጆች በወንጌል መረብነት የሰበሰቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሐዋርያት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጠይቀው ባገኙት መሠረት ሁላችን ዝግጅት እንድናደርግና በተስፋ እንድንጠብቀው ጽፈውልናል፡፡ ለምሳሌ፡-

የሐዋርያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹የእግዚአብሔርን የመምጣት ቀን ተስፋ እያደረጋችሁ በተቀደሰ ኑሮ ለመኖር ቸኩሉ›› 2ኛ ጴጥ.፫፥፲፩፡፡ በማለት በቀዳማዊ ምጽአቱ የተቀበልነውን የጸጋ ልጅነት፣ ድኅነት፣ ነጻነት ወዘተ አጽንተን በተቀደሰ አኗኗር እንድንኖር አስረድቶናል፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም "የሰው ሁሉ ተስፋ የወልደ እግዚአብሔርን መምጣት ይጠብቃልና" (ሮሜ. ፰፥፲፱) በማለት በሮም ለሚገኙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን አመጣጥ አስረድቷል፡፡ በመሆኑም ሐዋርያው እንደነገረን የዓለም ተስፋ የእግዚአብሔር መምጣት ነው ሌላ ተስፋ የለውም፡፡ በቀዳማዊ ምጽአቱ የተሰጡ የድኅነት ተስፋዎች ሁሉ የሚጠናቀቁትና የሚረጋገጡት በእግዚአብሔር ዳግም መምጣት ነው፡፡

ሐዋርያት ከጌታ ባገኙት ትምህርት የነገረ ምጽአትን ጉዳይ በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ስለነገረ ምጽአት የነገሩንም

በሃይማኖት ጸንተን በንጽሕና በቅድስና እንድንኖር ነው፡፡ ከገቡ የማይወጡበት፣ ከአገኙ የማያጡት ዘለዓለማዊ ደስታ አለና ያን ተስፋ አድርገን ለመልካም ሥራ እንድንቸኩል ለማድረግ በምልዓት አስረድተውናል፡፡ የአባቶቻችንን መልካም ትምህርት ጠብቆ የማያልፈውን ሕይወት ተስፋ እያደረጉ በቅድስና በንጽሕና በንስሓ ሕይወት እየተመላለሱ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እየተቀበሉ መኖር ከእኛ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

## ፫.የምጽአቱ ምልክቶች

**ሀ.የብዙዎች ሐሰተኞች መነሣት ብዙዎችን ማሳታቸው፡-** ጌታችን መድኃኒታችን ሲየሱስ ክርስቶስ ይህን ሲገልጥ ‹‹ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ›› ማቴ.፳፬፥፭ ብሏል፡፡ አሁን እንደምናስተውለው ብዙ ሐሰተኞች እንደ አሸን ፈልተው የሐሰት ትምህርት እያስተማሩ ብዙዎችን ከእውነተኛው የክርስትና መንገድ እያወጡ ይገኛሉ፡፡ ነቢይ ነኝ፣ ሐዋርያ ነኝ ተአምራት አደርጋለሁ በሚል ውሸት ብዙዎችን እያታለሉ ነው፡፡ እውነትን በሚጠሉ ሰዎች ድጋፍ ለቁጥር በሚያታክቱ የግንኙነት መስመሮች (ቻናሎች) ዓለምን እያደናቆሩት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የዳግም ምጽአትን መቅረብ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ‹‹እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ›› ተብለናልና እንጠንቀቅ፡፡

**ለ. ጦርነት፡-** በሁለተኛ ደረጃ ምልክት ሆኖ የተጠቀሰው ጦርነት ነው፡፡ አሁን ዓለማችን ዕለት ከዕለት ጆሮአችንን የሚያድነቁረን የጦርነት ወሬ ነው፡፡ አሁን ዓለም ዓለምን የሚያጠፉ የጦር መሣሪያ (ኒኩለር) አመረተኩ ተምዘግዛጊ ሚሳኤል በስውር የሚበር የጦር ጀት አለኝ ነው ዜናዋ ይህም ዓለም ለጥፋት እየቀረበች መሆኑን አመልካች ነው፡፡ ‹‹ጦርንም የጦርነትንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ ግድ ነው ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ አትደንግጡ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፡፡›› እንዲል፡፡ ማቴ.፳፬፥፮

**ሐ. በሽታ፡-** ከረኃብም ላይ በሽታ የምድር መናወጥ ይህን የመሳሰሉት ሁሉ የዳግም ምጽአትን አዋጅ እየመረረንም ቢሆን የሚያውጁ ናቸው፡፡ በተለይ አሁን ዓለምን ሥጋት ላይ የጣለው የኮረና ቫይረስ ለዚህ ዋና ማሳያ ነው፡፡ ዓለም ታሟል ፈውሱ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው፡፡ ‹‹ረኃብ፣ ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይሆናል›› እንዲል፡፡ ማቴ.፳፬፥፪

**መ. የክርስቲያኖች ለመከራ ተላልፎ መሰጠት፡-** አሁን ዓለማችን እንደፋሽን የተያያዘችው ተግባሯ ክርስቲያኖችን መግደል፣ ማፈናቀል፣ ማሳደድ፣ ማንገላታት፣ ማዘረፍና አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል ለክርስቲያኖች ፍትሕ አለመስጠት የዚሁ የዳግም ምጽአት ምልክት አንዱ አካል ወይም ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በተለይም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እየደረሰ ያለው መከራ ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው፡፡ ‹‹በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል ይገድሏችኋማል፤ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ በዚያ ጊዜ ብዙዎች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ፤ እርስ በእርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ›› ማቴ.፳፬፥፱ እንዲል፡፡

**ረ. የፍቅር መጥፋትና የዐመፃ ብዛት፡-** እነዚህን ሁሉ የሚያደርገው የፍቅር መጥፋት የዐመፃ እና የዐመፀኞች መብዛት ነው፡፡ ይህም የምጽአት ምልክት እንደሆነ ጌታችን አስተምሯል፡፡ አሁን መቸም ፍቅር አለ ብሎ መናገር ይከብዳል፡፡ አለም ካለን በጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው ይህ ደግሞ ፍቅርን ሳይሆን ዐመፃን የሚያነግሥ ነው፡፡ ‹‹ከዐመፅም ብዛት የተነሣ የብዙዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች እስከ መጨረሻ የሚፀና እርሱ ይድናል ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል ይሰበካል በዚያን ጊዜ መጨሻው ይመጣል›› እንዲል ማቴ.፳፬.፲፪፡፡

## ፬. የመምጫው ሰዓት

ከላይ የተዘረዘሩት ምልክቶች በትክክል ሰዓቱን ለይተው በዚህ ጊዜ ነው የሚሉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድንገት የሚሆን ነውና፡፡ ‹‹በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል በዚያን ጊዜ የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ የሰው ልጅንም በኀይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል መላእክቱንም ከታላቅ የመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል ከሰማያት ዳርቻ እስከ ዳርቻዋ ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ›› ማቴ.፳፬.፴፤ ‹‹በኖኅ ዘመን እንደሆነ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል›› ማቴ.፳፬፥፴፮ ማለት ቀንዋን እና ሰዓቷን የሚያውቅ የለም ተዘጋጅቶ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በዕለተ ዕርገቱ ለቅዱሳን ሐዋርያት በመላእክት አንደበት

‹‹ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ያረገው ኢየሱስ ነው ሲያርግ እንዳያችሁት ዳግመኛ ይመጣል›› ተብሎ ተነግሯልና በግልጥ ይመጣል። ሐዋ.፩፥፱-፲፩ ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ ‹‹እነሆ በሰማይ ደመና ይመጣል፤ ዐይን ሁላ ታየዋለች እነዚያም የወጉትም ይመለከቱታል፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ ስለእርሱ ያለቅሳሉ›› በማለት እንደተናገረው እየታየ በግልጥ ይመጣል። ራዕ.፩፥፯።

በዚህ መልኩ መጥቶ ዓለምን እንደ ሸማ ጠቅልሎ ያሳልፋታል ይህን ጊዜ ምድር የተቀበለችውን አደራ ታስረክባለች። ሙታን ይነሣሉ፤ የተዘራው ዘር ፈርሶ በስብሶ ተነሥቶ እንዲያፈራ አውሬ የበላው፣ ነፋስ የበተነው፣ ውኃ የወሰደው፣ በልዩ ልዩ ሞት በነፍስ ወደገነት ወይም ወደ ሲኦል የተወሰደውና በሥጋ በመቃብር ውስጥ ያረፈው ሁሉ ይነሣል። ‹‹በመጀመሪያ የአዋጅ ቃል በልዩ ልዩ ሞት የሞተው አውሬ የበላው ውኃ የወሰደው የፈረሰው የበሰበሰው የሰው አካል ራስ ካለበት ይሰበሰባል። በሁለተኛው አዋጅ የተኛህ ንቃ በሚለው ያለ መንቀሳቀስ ትኩስ በድን ይሆናል። በሦስተኛው አዋጅ ጻድቃንም ኃጥኣንም ከዓለም የተከተላቸው ሥራቸውን ይዘው ይነሣሉ።›› (ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ) ምድር ይህን አደራዋን ካስረከበች በኋላ ታልፋለች። የማያልፈው ዘለዓለማዊውን ርስት ለማውረስ ጻድቁን በቀኙ ኃጥኡን በግራው የሚያቆመው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ይህ በጌታችን ምጽአት የሚደረገውን ትንሣኤ ሙታንን ተከትሎ የዘለዓለም ሕይወት ለጻድቃን የዘለዓለም ኵነኔ ለኃኣን የሰጣል። ‹‹በመቃብር ያሉ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉ ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ እና በዚህ አታድንቁ›› ዮሐ. ፭፥፳፰ ከዚህ ትንሣኤ በመቀጠል የዘለዓለም ፍርድ የሰጣል።

## ፫.የዘለዓለም ፍርድ

የሰው ልጅ በክብሩ በመጣ ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ ያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣሉ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ እረኛም በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ ይለያያቸዋል። በጉችን በቀኙ ፍየሎችን በግራው ያቆማቸዋል ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል ‹‹እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ተርቤ አብልታችሁኛልና ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ታርዤ አልብሳችሁኛልና ታምሜ ጠይቃችሁኛልና ታስሬ ወደኔ መጥታችኋልና ጻድቃንም መልሰው ይሉታል ጌታ ሆይ ተርበህ አይተንህ መቼ አበላንህ? ተጠምተህስ መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህስ መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታስረህ አይተንህ መቼ ጠየቅንህ? ታርዘህ መቼ አለበስንህ? ወይስ ታስረህ ታመህ መቼ ወደ አንተ መጣን ይሉታል።

ንጉሡም እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ማድረጋችሁ ለእኔ ማድረጋችሁ ነው›› ይላቸዋል። በግራ ያሉትን ደግሞ ‹‹ብራብ አላበላችሁኝም ብጠማ አላጠጣችሁኝም ብታረዝ አላለበሳችሁኝም … እነርሱም ደግሞ መልሰው ጌታ ሆይ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ታመህ ወይስ ታርዘህ መቼ አይተንህ አላገለገልንህም? ይሉታል። ያን ጊዜ እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ አለማድረጋችሁ ለእኔ ደግሞ አለማድረጋችሁ ነው›› ብሎ ይመልስላቸዋል። ከዚያም ኃጥኣን ወደ ዘለዓለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሄዳሉ። ማቴ.፳፭፥፴፩-፵፮ ከዚህ በኋላ የሁሉም ፍጻሜ ይሆናል መንግሥተ ሰማያት ለጻድቃን ገሃነመ እሳት ለኃጥአን ይሰጣቸዋል እንደየሥራቸው ያገኛሉ። ‹‹እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱ እንደየሥራው መጠን እከፍለው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ›› እንዲል። ራእ. ፳፪፥፲፪

በአጠቃላይ የነገረ ምጽአት ጉዳይ ከላይ በሰፊው በተገለጸው መንገድ እንደሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። የመምጫው ጊዜ እንደቀረበ የሚያስታውሱ ምልክቶችን ተነገረን እንጂ ሰዓቷን በትክክል አልተነገረንም። በዚህ ፈንታ ግን ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ተብለናል። ስለዚህ ዋጋን ለመቀበል በቅዱስ ኑሮ ለመኖር መቸኮል ያስፈልጋል "የእግዚአብሔርን የመምጣት ቀን ተስፋ እያደረጋችሁ በተቀደሰ ኑሮ ለመኖር ቸኩሉ" ተብለናልና በሃይማኖት ጸንተን መልካም ሥራ ሠርተን እግዚአብሔር አምላካችን በክብር በመጣ ጊዜ በቀኙ ከሚቆሙት እድል ፈንታችንን ጽዋዕ ተረታችንን ያደርግልን ዘንድ መልካም ፈቃዱ ይሁንልን አሜን። ✝ ✝ ✝

# ቤተ ክህነት እና ቤተ መንግሥት

ዳዊት ደስታ

## እንደ መግቢያ

የሰው ልጅ አብሮ ለመኖር እንዲችል አካሄዱን የሚቆጣጠሩትና የሚመሩት ወደ ተፈለገውም ዕድገትና ብልጽግና እንዲደርስ የሚያስችሉት ሁለት የሥልጣን ተቋማት (ቤተ-መንግሥት እና ቤተ-ክህነት) አሉ፡፡ እነዚህ ተቋማት አንዱ ለመንፈሳዊ፣ ዘላለማዊና ሰማያዊ ጉዞውና ፍላጎቱ ሌላው ለሥጋዊ ጊዜያዊና ምድራዊ ጥቅሙና ዕድገቱ ላይ ተመሥርተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት በጥብቅ ግንኙነት ለረጅም ዓመታት አብረው ዘልቀዋል፤ ትስስሩም በሁለቱም መፈላለግ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው የሚለው መርሕ ተግባራዊ አፈጻጸሙ አጠያያቂ ነው፤ ሁለቱም በተመሳሳይ ሕዝብ ላይ ስለሚያተኩሩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ‹‹መነካካታቸው›› አይቀሬ ነውና፡፡ በሀገራዊ ጉዳዮች ከመንግሥት ጋር መተባበር በየትኛውም አኳኋን ‹‹ፖለቲከኛ›› ሊያሰኝ አይገባም፤ ለሃይማኖቱም ምድራዊ ህልውና የሀገር ሰላምና ልማት ያስፈልጋልና፡፡ የሁለቱም ህልውና የተመሠረተው በሕዝቡ ላይ መሆኑ ያገናኛቸዋል ብቻ ሳይሆን ወደ የራሳቸው ፍልስፍና በመሳብ ሂደት ውስጥ ያነታርካቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ‹‹በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት›› ናት፤ ምድራዊው መንግሥትም በሕዝብ ተመሥርቶ፣ ለሕዝብ የሚሠራ፣ ሕዝባዊ ነው፡፡ እናም ሁለቱም ያለ ሕዝብ (ሰዎች) ህልዎታቸው ሊነገር አይችልም፡፡

ግንኙነቱ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ትስስር በዓለምም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የነበረ፣ ዛሬም ድረስ የሚስተዋል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ነገሥታትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፤ የረጅም ጊዜ ቁርኝት ነበራቸውና፡፡ በብሉይ ኪዳን በንግሥት ሳባ የተጀመረው ግንኙነት (፩ነገ.፲፥፩)፤ በኋላ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በ፴፬ ዓ.ም. በዘመኑ የአገሪቱ ገንዘብ ሚኒስቴር በነበረው (ጃንደረባው ባኮስ) አማካይነት ክርስትናን ስትቀበል (የሐዋ.፰፥፳፮-፴፪) የበለጠ ተጠናከረ፡፡ ይህ ክስተት ከተለመደው የግሪኮ-ሮማን ዘመን የክርስትና ታሪክ (ክርስትና በተራ ሕዝቦች ተጀምሮ ወደ ነገሥታቱ ከምትጎተትበት ሁኔታ) ጋር ተቃራኒ ነበር፤ በተገላቢጦሹ በኢትዮጵያ ክርስትናን ለሕዝቡ የሰበከው የቤተ መንግሥቱ ጃንደረባ ነውና፡፡

ቤተ ክህነት ነገሥታቱን ቀብታ በማንገሥ ሕዝቡም ለእነርሱ እንዲገዛ ባላት ተሰሚነት በማሳመን፣ ለሕዝብ ጠንካራ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ግንባታ ግንባር ቀደም ሚናን ተጫውታለች፡፡ ነገሥታቱም አንድም ሃይማኖተኞች ስለ ነበሩ፣ በሌላም መልኩ ደግሞ ለፖለቲካዊ አስተዳደራቸው እጅግ ስለምታስፈልጋቸው ማለትም የመንግሥታቸው ህልውና የሚለካው ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት መጠን ስለ ነበር፡ ቤተ ክርስቲያንን የሙጥኝ ብለዋት አልፈዋል፤ በአንድ መልኩ ሲደግፏትና በሌላ ጊዜም ሲገፏት፡ ማለትም ሲጠቀሙባት ኖረዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሁሉ ጉዞዋ ለሀገር ያበረከተቻቸው አስተዋጽኦዎች አሉ፡፡ እነሱም በሀገር ግንባታ፣ ከመንግሥት ጋርግንኙነት በመፍጠር፣ በመልካም ዜጋ ግንባታ፣ በፖለቲካ፣ በሀገር ጥበቃ እና አርበኝነት የነበራት አበርክቶ ቀላል አይደለም፡፡ ድርሻዋም ምን እንደ ነበር የሚከተሉትን ጥቂት ማብራርያዎችን እንመልከት፡፡

## በሀገር ግንባታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ተፈርታ እና ተከብራ እንድትኖር ካደረጓት ነገሮች አብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሠራቻቸው ሥራዎች

ናቸው፡፡ አንድን ሀገር ሀገር የሚያሰኘው ሕዝቡ እና የአኗኗር ዘይቤው፡ ያለው መልክዐ ምድሩና ሕዝባዊ ሥርዓተ ማኅበር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችን ኢትዮጵያ መሠረት እና ጉልላት፣ድር እና ማግ ናት፡፡ ለሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ የኩራት ምንጭ መሆንዋን የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ታቦም ቤኪ የተናገሩትን ጠቅሶ በፍቅር ለይኩን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ድርሻ እንዲህ አስፍሮታል፡፡ ዘመናዊው የአፍሪካ የነፃነት ንቅናቄ የመነጨው ወደ ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ በደቡብ አፍሪካ ነበር፣ የዚህ ንቅናቄ የቀድሞ መሥራቾች የሀገራችን የመጀመሪያዎቹ ዘመናዊ አፍሪካውያን ልሂቃን ናቸው፡፡ የተነሡትም ከአብያተ ክርስቲያናት ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም ነበሩ፡፡

እነዚህ ዘመናዊ የአፍሪካ ልሂቃን ከአውሮፓውያን ሚስዮናች ራሳቸውን አላቀው በቤተ ክርስቲያናን ላይ ባለቤትነታቸውን ሲያውጁ፣ እንደመነሻ የተጠቀሙት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በመዝሙረ ዳዊት ፷፰ ላይ ይገኛል፤ ይህም፡- ‹‹መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፣ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች፡፡›› የሚለው ነው፡፡ አፍሪካ የአውሮፓውያን የቅኝ ግዛት እሽቅድድም ሰለባ ሆና በኖረችበት ወቅት ኢትዮጵያ ነፃነቷን እንደያዘች መቀጠሏ መነሳሳትን ይሰጣቸው ነበር፤ እናም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተተነበየው ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ስትዘረጋ ቤተ ክርስቲያናችን በአፍሪካዊ ሥነ ምግባር ትሞላለች ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ይህች እውነተኛ የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አፍሪካውያን በሙሉ ለነፃነት፣ ለባህላቸው፣ ለልዑላዊነታቸው፣ ለማንነታቸውና ለሰብአዊነታቸው እንዲከበር ላላቸው ህልም እንደማከማቻ ቦታ ሆና ታገለግላለች ብለው ያምኑ ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ እውነታ እና ታሪካዊ ሀቅ ላይ ተመሥርተው ነበር፡፡ እነዚህ የጠቀስናቸው አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብለው የሰየሙት፣ በአህጉራችን ላይ የመጀመሪያው ዘመናዊ የብሔራዊ ንቅናቄ የሆነው የደቡብ አፍሪካው አፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ (ANC) የተወለደውም ከእነዚሁ ከሀገራችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው...የፓርቲያችን የመጀመሪያ ፕሬዝዳንት የነበሩት ቄስ ጆን ዱቤም የዚሁ የደቡብ አፍሪካ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበሩ...፡፡›› በማለት ገልጿል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለቅኝ ገዥዎች እንዳትንበረከክ የሰበኩን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች እነ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሰማዕትን እና እነ አቡነ ሚካኤልን ማን ይረሳቸዋል፡፡ የሀገር ፍቅርን ከነኩራቱ፣ ጀግንነትን ከነጥበዓቱ፣ ፊደልን ከነቁጥሩ፣ ዘመንን ከነቀመሩ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ያበረከተችው ቤተ ክርስቲያናችን ናት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገራችን በኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ የነበራትን ሚና ለመረዳት የመንግሥት አወቃቀር በኢትዮጵያ ምን እንደ ነበር በሚገባ ማጤን ይገባል፡፡

ለምሳሌ ከንግሥት ማክዳ ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ከመጽሐፍ ቅዱሱ ከንጉሥ ሰሎሞን የዘር ሐረግ የተገኙ ነገሥታት ሥዩመ እግዚአብሔር (በእግዚአብሔር የተቀቡ እየተባሉ) የቤተ ክርስቲያናችን ብፁዓንና ቅዱሳን ፓትርያርኮች እየቀቡ ያነግሡአቸው እንደ ነበር የኢትዮጵያን ታሪክ የተማረ ሁሉ የሚያውቀው እውነት ነው፡፡ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ድረስ የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ንግሥናቸውንም ሆነ አስተዳደራቸውን የሚያገኙት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ ንጉሡ እና ፓትርያርኩ የጠበቀ ቁርኝት እንደነበራቸው በሁሉ የታወቀ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላለችው ኢትዮጵያ መሠረታዊ መገለጫዋ ናት ብሎ የጻፈው (ያዕቆብ ቡልቲ ፳፻፲፪፡፲) ነው፡፡ አክሎም በገጽ ፲ ላይ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ ድርሻ በኢትዮጵያ እድገት ላይ ተጫውታለች›› በማለት ይገልጻል፡፡ ሲያብራራም ‹‹በትምህርት መስክ የትምህርት ሚኒስቴር በመሆን እንደዚሁም በልማት መስክ ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽንን በማቋቋም በዚህ ኮሚሽን የገጠር የንጹሕ ውኃ ሥራ፣ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከል ላይ እንዲሁም ንጽሕና

እና ጤና አጠባበቅ ላይ እያበረከተች ያለውን አስተዋጽኦን አስፍሯል።››

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገረ መንግሥት ግንባታ ለኢትዮጵያ ያበረከተችውን አስተዋጽኦ ምን እንደ ነበር ማሳየት ተገቢ ነው። ለሀገር ግንባታ ካበረከተቻቸው አስተዋጽኦዎች መካከልም የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው። የተስተካከለ ሥነ ምግባራዊ ሰብእና ያለው፣ አርበኛ ጀግናና ሀገር ወዳድ ትውልድ መፍጠር፣ ማኅበራዊ ጥንካሬ በመፍጠር፣ በአፈርና ብዝኃ ሕይወት ጥበቃ፣ ሀገር በቀልና ዓለማቀፋዊ ትምህርቶችን በማስፋፋት፣ የባህልና የቱሪዝም፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ቅርጻ ቅርጽ፣ የኪነ ሕንፃ፣ የሥነ ዜማ ጥበባዊ ሀብቶችን በማስፋፋት በማስጠበቅ ብሎም ለዓለም በማስተዋወቅ፣ በሕዝቦች መካከል ጠንካራ ማኅበራዊ ትስስርንና ሀገራዊ አንድነትን በመፍጠር፣ በድህነት ቅነሳ፣ አካል ጉዳተኞችን በማብቃት፣ የሀገርን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት በማፋጠን፣ ሰላምም በማስፈን፣ ለምሁራን በጥናትና ምርምር ማዕከልነት እንዲሁም ዘመናዊ ሕክምና ባልነበረበት ወቅት የሕክምና ማዕከል ሆና ስታገለግል መኖሯ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ካበረከተቻቸው አስተዋጽኦዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው።

## ከመንግሥት ጋር ያላት ግንኙነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት የሀገሪቱ መሪ እና አስተዳዳሪዎችን በማስተማር በማብቃት በመሾም ሲያጠፉ በመገሠጽ የመሪነት ሚናዋን እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ ስትጫወት የነበረች ሲሆን እስከዚሁ ዘመንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት የነበረ ሲሆን እስከዚሁ ዘመን ድረስ ምንም ዓይነት ልዩነት በቤተ መንግሥቱ እና በቤተክህነቱ መሀል አልነበረም ከደርግ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከላይ እንደገለጽነው መንግሥት እና ሃይማኖት ተለያይተዋል። ‹‹የመንግሥት እና የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደ ቀኝ እና ግራ እጅ ነበር›› ብሎ የጻፈው ዓለማየሁ ብርሃኑ የተባለው አጥኚ የሀገሪቱ ንጉሥ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ድረስ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል መሆን እንደ ነበረበትም እንዲሁ አእምሮ የተባለ ምንጭን (፲፱፻፸) ጠቅሶ ገልጧል። የሀገሪቱን ሕግ የሚያወጡት እንደዚሁም ሀገሪቱን ሲመሩ እና ሲያስተዳድሩ የነበሩትም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባላት በመሆናቸው የሃይማኖቱ ጠበቆች ነበሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ ሁነኛ የመንግሥት የልማት አጋር ስትሆን በሁሉም የሀገራችን ስፍራዎች ሁሉ ከኅብረተሰቡ ጋር በጥብቅ በሥነ ምግባር እና በምጣኔ ሀብት አብራ የምትሠራ መሆንዋን ይገልጻል። አክሎም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሀገሪቱ ሁነኛ የልማት አጋር በመሆን የምትጫወተው ሚና ቀላል እንደማይባል ነው። (ዓለማየሁ ብርሃኑ፣ ፳፻፲፱)

ዓለማየሁ ብርሃኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተቋማዊ አስፈላጊነት በከተማ ልማት (Relevance of Ethiopian OrthodoxTewahido Church Institutional Setup for Rural Development:) በሚል ርእስ ባዘጋጀው የ፪ኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፉ ላይ ገጽ ፲ ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ፣ ታሪካዊ፣ ብሔራዊ እና ሃይማኖታዊ እንደ መሆንዋ በሀገሪቱ ላይ በርካታ አሻራዎችን አኑራለች። በሀገር አንድነት እና በሰላም ግንባታ፣ በሀገር ነፃነት እና ሉዓላዊነት እንዲጠበቅ ቤተ ክርስቲያኒቱ የአርበኝነት ሚናን ስትጫወት ነበር›› ሲል ገልጧል። አክሎም ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉር የራስዋ የሆነ ፊደል ያላት በዛም የምትጽፍ እና የምታነብ እንድትሆን፣ የራስዋ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ያላት የራስዋ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ያላት አሁንም የምትጠቀምበት ፊደል፣ ቁጥር እና የዘመን መቁጠሪያ የቤተ ክርስቲያን ሀብት እንደ ሆነ፤ በ፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ባፈራችው በቅዱስ ያሬድ የተገኘው የዜማ ስልት ከመንፈሳዊው አገልግሎት ባሻገር ለዓለማዊው ዜማም መሠረት ሆኖ ሀገር እንደምትገለገልበት ይገልጻል።

## በመልካም ዜጋ ግንባታ

የመልካም ዜጋ ግንባታ የሀገራችን መንግሥት መርሕ ነው። በሥነ ትምህርት (በትምህርት ፖሊሲው) ላይ በዓላማ ከተቀመጡ ቁልፍ ቃላት አንዱ መልካም ዜጋ መፍጠር ነው። እርግጥ የዘርፉ ምሁራን እንደሚስማሙበት የሥነ

ምግባር እና ሥነ ዜጋ ትምህርት መልካም ዜጋ ፈጥሯል ወይ የሚለው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው።

በዚህም ምክንያት የሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት በቅርቡ እንደገና ተሻሽሏል። መልካም ዜጋ ሀገሩን የሚወድ ሙስና (ጥፋትን) የሚንቅ በበጎ ሥነ ምግባር የታነፀ፣ ክፋውን የሚጠላ ነው። እርግጥ እንደዚህ ያለ ዜጋ ለመፍጠር የሥነ ዜጋ ትምህርት እና የሥነ ዜጋ እና ሥነ ምግባር መምህራን አልቻሉም። መልካም ዜጋ የሚፈጠረው ስለ መልካም ዜግነት በመጽሐፍ በማስተማር ብቻ ሳይሆን መልካም ዜጋ ሆኖ በማሳየትም ጭምር ነው። የመልካም ዜጋ ግንባታ የሚጀመረው እንደ ሕንፃ ከታች ነው። ብዙ ጊዜ በሀገራችን ስለ መልካም ዜጋ ግንባታ የሚሰበከው ግን ልጆች ካደጉ በኋላ ነው።

> **ኦርቶዶክስ ሀገር ናት ሀገራችን እንደ ሀገር ሉዓላዊነትዋ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገችው ዛሬ ድረስ በየትኛውም ዓለም እንድንኮራ መመኪያ እና መኩሪያ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት።**

ሕጻናት ከሕፃንነታቸው ጀምረው መልካም ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ በፈሪሀ እግዚአብሔር ሰውን በማክበር በትሕትና እንዲያድጉ የቤተ ክርስቲያንን ሚና ማንም ሊተካው አይችልም። ሀገር የምትፈልገው መልካም ዜጋ ከሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ከሃይማኖት ተቋማትም ጭምር ነው። መንግሥት ይህን ዐውቆ ለመልካም ዜጋ ግንባታ የሃይማኖት ተቋማት የሚያበረክቱትን አስተዋጽዖ ትልቅ ቦታ በመስጠት በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከጎናቸው ሊቆም እና አብሯቸው ሊሠራ ይገባዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሥነ ምግባር የታነፀ መልካም ዜጋ ማፍራት ትችልበታለች። ታዲያ ለዚህ ተግባሯ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ሊያደርግላት ይገባል። ይህ ሲሆን ሙስናን የሚጠየፍ በመልካም አስተዳደር የተመሰከረለት ተስፋ የሚጣልበት ከክፉ ሥራ ሁሉ የራቀ የሀገሩን ጥቅም ለሌላው አሳልፎ የማይሰጥ ሀገሩን የሚወድ ለሀገሩ የሚሞት ዜጋን ማፍራት ይቻላል።

## በፖለቲካ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከትላንት እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ማንም ሊተካው የማይችለውን ሚና እየተጫወተች ያለች ሀገር ናት። ኦርቶዶክስ ሀገር ናት ሀገራችን እንደ ሀገር ሉዓላዊነትዋ ተጠብቆ እንዲቆይ ያደረገችው ዛሬ ድረስ በየትኛውም ዓለም እንድንኮራ መመኪያ እና መኩሪያ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት። ምዕራባዊ ባህል እና ፍልስፍና ያልተቀላቀለባት ቅድስት፣ አሐቲ፣ ኩላዊትና ሐዋርያዊት ናት። ለሀገራችን በፖለቲካው መስክ ደግሞ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ድረስ ነገሥታቱን ቀብታ በማንገሥ በንግሥናቸው ዘመንም ስታማክር በማጠናከር፣ መልካም ሲሠሩ በማመስገን ክፉም ሲሠሩም ያለ ፍርሀት በመገሠጽ ተቋማዊ ኃላፊነቷን በትጋትና በቁርጠኝነት ስትወጣ ኖራለች። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሀገር ወዳድ ልጆችን ወልዳ ያሳደገች፣ ጀግንነትንና የሀገር ፍቅርን ያስተማረች ለሀገር መሞት ክብር መሆኑን የእምነት አባቶቿን እነ አቡነ ጴጥሮስ እና አቡነ ሚካኤልን ፊት አውራሪ በማድረግ ፋሺስት ኢጣሊያን የተፋለመች፣ ታቦት አውጥታ ዐውደ ውጊያ ድረስ የዘመተች የሀገር ባለ ውለታ ቤተ ክርስቲያን ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የሀገራችን ልዕልና ቋንቋችን እና ማንነታችን ተጠብቆ በራሳችን ቋንቋ የምንናገረው በራሳችን ፊደልም የምንጽፈው ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካው መስክ በነበራት ንቁ ተሳትፎ ማንነታችንና ክብራችን ተጠብቆልን ስለ ኖረ ነው።

ዛሬ ላይ ግን ጥንት የነበራት ፖለቲካዊ ሚና በዓለማዊነት አገዛዝ ስም ተዳፍኖ ሀገርን የሚያበጣብጥ፣ የሕዝብን ሰላም የሚያናጋ የዘረኝነት መንፈስ በሰሜን እና በደቡብ በምስራቅ እና በምዕራብ ተንሰራፍቶባታል፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያን በሀገር ፖለቲካ ላይ የነበራት ሚና መቀማት ውጤት እና የውጭ ኃይሎች ሥውር የማፈራረስ ተልእኮ እንዲሁም የሴራ ፖለቲካቸው (የሴራቸው) ውጤት ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ሀገራችን ዕሴቷንና ባህሏን ጠብቃ እንደ ሀገር መቆም የምትችለው የእምነት ተቋማት ጠንካራ ዘመኑን የዋጀ አመራር ሲኖራቸው ነው፡፡

ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ከሰሀራ በታች ባሉ በቅኝ ግዛት ጊዜ የተጀመረ ፖለቲካዊ ሃይማታዊ እንቅስቃሴ ሲሆን የተጀመረውም ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው በደቡብ አፍሪካ ነው፡፡

እንቅስቃሴው በ፲፰፻፺ እ.አ.አ. በአፍሪካ ያሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ በአንድ ለመሰብሰብ የተመሠረተ ነው እንደ ትመቡ ተሪቢያል ቤተ ክርስቲያን እና የአፍሪካ ቤተክርስቲያን (Tembu tribal church and the Church of Africa. ቃሉን መጀመሪያ የተጠቀመው Mangena Mokone የተባለ ሰው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ባገኘ ጊዜ እንደ ሆነ እና ዘረኝነትን ለመዋጋት እና ቅኝ ገዥዎችን ለመቃወም የተጀመረ እንቅስቃሴ እንደነበረ የሚገልጸው ብሪታኒካ ኮነሰስ ኢንሳይክሎፒዲያ ገጽ ፳፻፴፱ ላይ ነው፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ላይ በናይጄሪያ፣በካሜሮን፣በጋና እና በሌሎች ቦታዎች ላይ ይህ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መጀመሩን ይገልጻል፡፡

ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱ የኢትዮጵያ መነኮሳት እና ምእመናን እስከ ፲፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ መልካም የሆነ የውጭ ግንኙነት ይፈጥሩ እንደነበር እና በሀገራችን ስላለው ጥሩጥሩ ነገር እንደ አምባሳደር በመሆን በደረሱበት ሁሉ ለሚያገኙት በመንገር ሀገራቸውን ማስተዋወቃቸውን የሚነግሩን በአ.አ.ዩ.የታሪክ እና የቅርስ ጥናት የት/ት ክፍል መምህር የሆኑት ዲ/ን ጌታቸው መረሳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚና በመካከለኛው ዘመን የውጭ ግንኙነት በሚል ርእስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው ገጽ ፫ላይ ነው፡፡

## በሀገር ጥበቃ እና አርበኝነት

የሀገር ሉዓላዊነት የሚጠበቀው በሀገር የቁርጥ ቀን ልጆች የሥጋ የደም እና የአጥንት ዋጋ የነፍስ ዋጋ በመክፈል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንግንባር ቀደም በመሆን ሀገርን ከጠላት በመከላከል እና ወራሪ ኃይልን በጸሎትም እንደዚሁም ልጆቿዋን ወደ ዐውደ ጦር ግንባር በመላክ ለሀገር ያላትን ታማኝነት ከየትኛውም በኢትዮጵያ ከሚገኙ ቤተ እምነቶች በላይ ለዘመናት ስታሳይ ኖራለች፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰውን ግደሉ ብላ አታስተምርም በሀገር ሉዓላዊነት ላይ ሲመጡ በመጀመሪያ በጸሎት፣ በትሕትና እና በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነገሮች እንዲያልቁ ትጥራለች እንደዛ ሆኖ ማለቅ ካልቻለ ግን ወደ ዐውደ ጦር የሚያስወጣ ግዳጅ ሲመጣ ታቦት አውጥታ እግዚኦታ አድርሳ ልጆቿዋን ለጦርነት ትልካለች፡፡ አሸንፈውም ሲመጡ ጀግንነታቸውን በመጽሐፍ በሐውልት ትዘክራለች፣ የሞቱትን ፍትሐት ፈታ ወደ ላይኛው መንግሥት በክብር ትሸኛቸዋለች፡፡ ✞ ✞ ✞

ምንጭ፡-ሕርያቆስ (አባ)፣ፍኖተ ቤተ ክህነት ወቤተ መንግሥት (፳፻፲፪ ዓ.ም.)

*Alemayehu Birhanu፣ ፳፻፲፱ Study of Perceptions of A.A. DioceseMembers on Communication practice of EOTC. Addis Ababa University.*

*Jacob Bulti Smørdal ፳፻፲፪ Religion and Development in Ethiopia Department of International Environment and Development Studies Norwegian University of Life Science (UMB)BritannicaCONCISE ENCYCLOPEDIA ፳፻፮*

# አባ ተከሥተ ብርሃን



*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*



## ልደት

አባ ተከሥተ ብርሃን ከአባታቸው መልከ ጼዴቅ እና ከእናታቸው ድል በኢየሱስ በሰሜን ሸዋ አካባቢ የተወለዱ በ፲፫ኛውና በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አባት ናቸው፡፡ አባ ተከሥተ ብርሃን የቀድሞ ስማቸው በኪሞስ ይባል የነበረ ሲሆን የደብረ ሊባኖሱ የእጨጌ ፊልጶስ ደቀ መዝሙርም ነበሩ፡፡ ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ባዘጋጁት የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ግን ልደታቸው በ፲፬ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ተጽፏል፡፡

## የአገልግሎት ሕይወት

አባ ተከሥተ ብርሃን ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ወደ ጎጃም በመሄድ፣ ወንጌልን አስተምረዋል፡፡ በዚያም ድንቅ ድንቅ ተአምራትን አድርገዋል፡፡ በርካታ ምእመናንን በማሳመንና በማጥመቅም ዕድሜያቸውን ሙሉ እግዚአብሔርን አገልግለዋል፡፡ ከደብረ ሊባኖስ ወደ ጎጃም የሄዱበት ምክንያትም ንጉሡ አፄ አምደ ጽዮን የእንጀራ እናቱን ማግባቱን እጨጌ ፊልጶስ ስለተቃወሙት እርሳቸው ማለትም አባ ተከሥተ ብርሃንም ደግሞ በወቅቱ የእጨጌ ፊልጶስ ደቀ መዝሙር ስለነበሩ የንጉሡ ሰዎች የእጨጌ ፍልጶስ ተባባሪ ናችሁ ብለው ካደረሱባቸው መከራ የተነሣ በስደት ነበር፡፡ አፄ አምደ ጽዮን መነኰሳቱን ሲያሳድዳቸው አባ ፊልጶስ አባ በኪሞስን አንተ ወደ ምድረ ጎጃም ሂድ እኔ ክፍሌ በመንዝ አካባቢ በምትገኘው ደብረ ዕንቊ ነው" ብለዋቸው ወደ ጎጃም እንዲመጡ ሆኗል፡፡

አባ ተከሥተ ብርሃን ገና ደብረ ድማኅ ከመድረሳቸው በፊት በስደት እያሉ ደብረ ዕንቊ በምትባል ዋሻ ሱባዔ በመግባት የመምህራቸውን የእጅ መስቀል ለምልክት በቦታው ትተው በመምጣት በሞጣ አድርገው ወደ ዲማ በመግባት በዚያ ዐረፉ፡፡ በዚህም ቦታ በዲማ ማለት ነው ‹‹ወረከበ ዐቢየ ጾላዕተ በውስተ አሐቲ ሀገር እንተ ይእቲ ደብረ ድማኅ ይላል፤ ዲማ በምትባል ሀገር ውስጥ ትልቅ ዋሻ አገኘ፡፡›› በዚህም ዋሻ ውስጥ በእመቤታችን ስም የተቀረፀች የሰማዕታት አለቃ ቅዱስ ጊዮርጊስ በሕይወተ ሥጋ ሳለ ‹‹ደምርኒ እሙ ምስለ ፍልሰትኪ›› እያለ ይጸልይባት የነበረችውን ታቦትና ንዋየ ቅድሳት አገኙ፡፡ በዚያም የእመቤታችንን ጽላትና ንዋየ ቅድሳቱን በክብር አስቀምጠዋል፡፡ እርሳቸውም አብረዋቸው ከሚኖሩ መንፈሳውያን ልጆቻቸው ጋር በጎጃም አውራጃ ሁሉ እየወጡና እየወረዱ ወንጌልን አስተምረዋል፡፡

ከዚያም በኋላ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ከአካባቢው ስለ አሳደዳቸው ወደ በጌ ምድር ደብረ ግሸና በመሄድ በዚያ ወንጌልን በስፋት አስተምረዋል፡፡ ከዚያም ተመልሰው ሞጣ ደብረ ጦት በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተ ክርስቲያን ተክለው ዘጠኝ ዓመት አስተምረዋል፡፡ በተለያዩ ቦታ እየተዘዋወሩ ተቋርጦ የነበረውን ሐዋርያዊ ሥራቸውን በመቀጠል ምእመናንን በማጥመቅ እንደ ጮለሚት ማርያም (ብቸና አካባቢ ያለች ገዳምን) መሥርተዋል፡፡ በአዴት፣ በሳርካ፣ በአመዳሚት (ወሰንአም) እየተዘዋወሩ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን እያነፁ ብዙ ሕዝብ አስተምረዋል፡፡

አባ ተከሥተ ብርሃን ከደብረ ሊባኖስ ወደ ዲማ ገዳም በሄዱ ጊዜ በአካባቢው ትመለክ የነበረች እመ ቡላድ የምትባል

ሥጋ ለባሽ ሰይጣን ነበረችና ክርስቶስን ከሰይጣን ጋር ብርሃንንም ከጨለማ ጋር አንድ የሚያደርገው ማነው? ምእመናንን ከመናፍቃን ጋር ርስተ መንግሥተ ሰማያትን የሚያካፍላቸው ማነው? እያሉ በማስተማርና በመስበክ ሥጋ ለባሽዋ ሰይጣን እመ ቡላድ የነበረችበትን በረሃ የቅዱሳን ቦታ አደደረጉት፡፡ ክርስቶስ ባደረበት ሰይጣን፣ ብርሃን ባለበትም ጨለማ ሊኖር እንደ ማይችል ሁሉ ምእመናንም ባሉበት መናፍቃን ሊኖሩ አይችሉም በማለት ያችን ሥጋን የለበሰች ሰይጣን (እመ ቡላድ) በእግዚአብሔር ቸርነት ቀድሞ የግብር አባቷ ሳጥናኤል ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተወርውሮ በተጣለበትና ድል በተነሣበት የብርሃን መስቀላቸው ከአካባቢው አስወጥተው እስከ ካራ ተራራ ድረስ (ዝሪም ይሉታል አዊ ሀገረ ስብከት ይገኛል) አባረዋታል፡፡ ከዚያም አልፎ እስከ ምድረ ሱዳን ሊያባርሯት ሲሉ እኔ የቤት እመቤት ‹‹ስሜ ማርያም›› ይባላል እያለች ሕዝቡን አሳተቻቸው፡፡ በዚህ ጊዜም ሕዝቡ የአባ ተከሥተ ብርሃንን ትምህርት መስማት ሲገባው የእሷን ነገር ተቀብሎ እኛ እንቀበላታለን ብሎ መልሷቸዋል፡፡

በዚሁ በአዊ አካባቢ ቡላድን ሲያባርሩ ያዩ ሰዎች እንዳያባሯት አንድ አርሶ አደር አባ ተከሥተ ብርሃንን በጅራፍ ገርፎ ሲያባርራቸው እሳቸውም ‹‹ተው ይህቺን ሰይጣን ላስወጣልህ እስከ ልጅ ልጆችህ ድረስ ስትገዛህ ትኖራለች›› ብለው ቢለምኑት ‹‹የለም እመቤቴንማ አላስወጣትም›› አላቸው፡፡ እሳቸውም በአካባቢ ያለውን ሕዝብ በማስተማር ወደ በአታቸው ዲማ ሲመለሱ ጉታ፣ ሜጫ፣ መርአዊ የሚባሉ አካባቢዎችን ሰብከዋል፡፡ ያቺ ቡላድ ዛር (ሰይጣን) ግን በአንዳንድ አካባቢዎች እስከ አሁን ድረስ እየተመለከች ትገኛለች፡፡

አባ ተከሥተ ብርሃን በደብረ ድማኅ እንዲህ ባለ ሐዋርያዊ አገልግሎት ወንጌልን በመስበክ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ኖረዋል፡፡ በበአታቸው በዚሁ በደብረ ድማኅ በነበራቸው የ፲፫ ዓመታት አገልግሎትም ገዳሙን አጠናክረዋል፡፡ አባታችን በዚህ በአቋቋሙት ገዳም ወንዶች ከገዳሙ በስተምሥራቅ ሴቶች ደግሞ በስተምዕራብ አቅጣጫ መኖሪያቸውን አድርገው በአንድ በር እየገቡ በአንድ አዳራሽ እየተሰበሰቡ እንደ ማዕረጋቸው በቆብና በአስኬማ ተወስነው እየኖሩ የዕለት ምግባቸውን እንዲመገቡ የሚያደርገውን ሥርዐትም የሠሩት አባታችን አባ ተከሥተ ብርሃን ናቸው፡፡

አባ ተከሥተ ብርሃን ይህንን ሥርዓተ ምንኵስና ሠርተው ገዳም መሥርተው በገዳሙ ለ፲፫ ዓመታት በመንፈሳዊ ተጋድሎ መኖራቸውን ንጉሡ ዐፄ ዳዊት (፲፫፻፹-፲፬፻፲፪) ሰምቶ በመምጣት ዛሬ ገድእና ዝያ በሚባሉ ወንዞች መካከል ያለውን ርስት በጉልትነት በመስጠት በ፲፫፻፸፱ ዓ.ም አካባቢ ገዳሙን አጽንቶታል፡፡ ይህ የርስት ጉልት ቦታ በአሁኑ ጊዜ ተቆራርጦና ለኗሪው ተሰጥቶ የገዳሙ መሬት በጣም የተወሰነ ሁኗል፡፡ በእርግጥ ገዳሙ በፍጹም የለውም ባይባልም አስቀድሞ ከተሰጠው ይዞታ አንጻር ግን እጅግ የተወሰነና ይህን ያህላል የሚባል አይደለም፡፡

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ባዘጋጁት የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት እንዲህ የሚል መረጃ ተጽፎ ይገኛል፡፡

አባ ተከሥተ ብርሃን ትሩፋታቸውና ገድላቸው ብዙ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ በጎጃም ክፍለ ሀገር እየተዘዋወሩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል፡፡ ከነዚህም ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል ፩ኛ. ለመጀመሪያ ጊዜ ቀዳሚት ማርያም በዲማ፣ ፪ኛ ሞጣ ደብረ ሚካኤል፣ ፫ኛ ቢቸና ጨለሚት ማርያም ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ሌላ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አስተክለዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ አነሣሣቸውና ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር ሄደው በአድያቦ አውራጃ እየተዘዋወሩ ነገደ ኵናማዎችን አስተምረውና አሳምነው አጥምቀዋል፡፡ በአክሱም ጽዮን ንቡረ እድነት ተሹመው ጥንታዊት ጽዮንን አገልግለዋል፡፡ (የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ገጽ ፺፱-፻፩)

## በአገልግሎት ዘመናቸው የደረሰባቸው መከራ

አባ ተከሥተ ብርሃን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ‹‹ሊከተለኝ የሚወድ ሰው ራሱን ይካድ ጨክኖም የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ዕለት ዕለትም ይከተለኝ›› (ሉቃ. ፱፥፳፫) በማለት ያስተማረውን ትምህርት በተግባር የፈጸሙና መልካሙን ገድል የተጋደሉ አባት ናቸው፡፡ ከበአታቸው ሁለት ሦስት ጊዜ ተሰደዋል፤ በሰዎች ተደብድበዋል፤ በዙ መከራና እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ ለማሳያ ያህልም በዚያን ዘመን ንጉሡ ዐፄ አምደ ጽዮን ብዙ ውጊያዎችን ከአረማውያን ጋር በማድረጉ ከእነርሱ የተማራቸው ብዙ ባህሎች ነበሩት፡፡ በዚህ ምክንያት የእንጀራ

እናቱን እስከ ማግባት ደረሰ፡፡ ያን ጊዜ ዮሐንስ መጥምቅ ሄሮድስን እንደተቃወመው የደብረ ሊባኖሱ ፫ኛ እጨጌ አባ ፊልጶስ ፊት ለፊት ተቃወሙት፡፡

ንጉሡም ከስሕተቱ ከመመለስ ይልቅ እጨጌ አባ ፊልጶስን ወንጂ በተባለ ከተማቸው ደማቸው እንደ ውኃ እስኪወርድ ድረስ አስደብድቦ ወደ ትግራይ አጋዛቸው፡፡ በዚህም የተነሣ ከእርሳቸው ጋር ተባብራችኋል ተብለው አባ ተክሥተ ብርሃንም ተጋዙ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ከበአታቸው አሳድዷቸው በበጌምድር ደብረ ግሽና ተቀምጠዋል፡፡

## የአደረጓቸው ተአምራት

አባ ተክሥተ ብርሃን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ " እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የምሠራውን ሥራ እርሱም ይሠራል፤ ከዚያም የሚበልጥ ይሠራል" (ዮሐ.፲፬፥፲፪) በማለት እንደተናገረ በርካታ ተአምራትን አድርገዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ እመ ቡላድን ከአካባቢው ማባረራቸው ነው፡፡ ከላይም እንደተገለጸው ይህቺ እመ ቡላድ የምትባለው ሥጋን የለበሰች ጋኔን እየተገለጸች ልጃችሁን አሳድጋለሁ የተገዛ ከብታችሁን አረባለሁ፤ ቤታችሁንም እጠብቃለሁ እያለች ሕዝብን የምታስት ስትሆን ከዚህም የተነሣ በአካባቢው ሕዝብ ትመለክ ነበር፡፡ እርሷም ከገዳሙ በስተምዕራብ ጥልቀቱ ፭፻ ሜትር በሚሆን ገደል ላይ ተሠውራ ሰዎችን ስታስትና ስታስጨንቅ እስከ አባ ተክሥተ ብርሃን መምጣት ድረስ ቆይታለች፡፡ በዚያ በረዥም ገደል ላይ ተሠውራ ሕዝቡን ስታስት አባታችን አባ ተክሥተ ብርሃንም በበትር እየደበደቡ ከአካባቢው አስወጥተው አባረዋታል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ከዕለታት አንድ ቀን በጎጃም ክፍለ ሀገር ይኸውም እነሴና እነብሴ በሚባለው አካባቢ በሚገኘው ነድ አጹራ ማርያም በሚባለው ቦታ ያሉ ሰዎች የእጁን ተዓምራት የቃሉን ትምህርት ሰምተው ከማመናቸው የተነሣ በአንድ ቀን ፺፱፻፺፱ (ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ) ሕዝብ በማጥመቃቸውና ሕዝቡን ሳያቈርቡት ቀኑ መሽቶ ስለነበረ ብርሃን ስለወረደላቸው አባ ተክሥተ ብርሃን የሚል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡

## የተሰጣቸው ቃል ኪዳን

አባ ተክሥተ ብርሃን እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ በዳዊት ላይ አድሮ "ከመረጥኋቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ" (መዝ.፹፰፥፫) በማለት እንደተናገረ ጽኑ የሆነ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡ ከገባላቸው ቃል ኪዳንም መካከል እመ ቡላድን ከአካባቢው ከአስወጡበት ጊዜ ጀምሮ በአማላጅነታቸው አምኖ ጸሎት ላደረገ ሁሉ የልቡ መሻት እንደሚፈጸምለት፣ የታመመም ከደዌው እንደሚፈወስ ከተገባላቸው ቃል ኪዳኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ እስከ ዛሬ ድረስም በተሰጣቸው ቃል ኪዳን አምነው ከአራቱም ማዕዘን የሚመጡ ሕሙማን ይልቁንም በእመ ቡላድ ስም ታመው የሚመጡት ሁሉ ገድላቸው እየተነበበላቸው ጠበላቸውን እየጠጡ እየተፈወሱ የሚሄዱ ሆነዋል፡፡ በስማቸው በፈለቀው ጠበልም በርካታ በሽተኞች በተለይም በእመ ቡላድ የሚሠቃዩት ይፈወሱበታል፡፡

ዳግመኛም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደመና ተገልጾ ጎጃምን ከዐባይ እስከ ዐባይ ታስተምር ዘንድ የመጀመሪያ አዲስ ሐዋርያ አድርጌሃለሁ ብሏቸዋል፡፡ በኋላኛው ዘመን መናፍቃን ይነሣሉ፡፡ ነገር ግን መካነ ዕረፍትህ የምትሆን ደብረ ድማኅን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የመናፍቃን እግር አይረግጧትም፡፡ ቢረግጧትም አያድሩባትም ብሎ ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸውም ሊታወቅ ከእርሳቸው ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በእግዚአብሔር ቸርነት በሊቃውንት ብርታት ከደብረ ድማኅ የምንፍቅና ትምህርትም ሆነ እግረ ፍለጋቸው እንዳልደረሰ በቦታው የሚገኙ ሊቃውንትና ምእመናን ምስክር ናቸው፡፡

## ዕረፍት

አባ ተክሥተ ብርሃን እንዲህ ባለ መንፈሳዊ አገልግሎት በበአታቸው ደብረ ድማኅ በሌሎችም አካባቢዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ በመጨረሻም ጊዜ ዕረፍታቸው እንደ ደረሰ ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ነግሯቸው እግዚአብሔር አምላክም ለቅዱሳኑን የሚሰጠውን ቃል ኪዳን ሰጧቸው መጋቢት ፲ ቀን በሰላም ዐርፈዋል፡፡ ዕረፍታቸው እንደታወቀም ሱባኤ ይይዙበት በነበረው ዋሻ ውስጥ ተቀበሩ፡፡ በዓለ ዕረፍታቸውም በደብረ ድማኅ በየዓመቱ መጋቢት ዐሥር ቀን ይከበራል፡፡

✝ ✝ ✝

*(ምንጭ በገዳሙ የተዘጋጀ የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ አጭር ታሪክ እና ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ያዘጋጁ የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት)*

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

*ክፍል ሁለት*



*በቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*

***ውድ አንባብያን ባለፈው ወር ዕትማችን በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዐምዳችን የትዳርንና ትዳር የሚፈርሱባቸውን ምክንያቶች በተመለከተ የሚነሡ ጥያቄዎችን መሠረት አድርገን ምላሽ ይሰጡን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በምሥራቀ ፀሐይ ቀበና መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል አገልጋይ የሆኑትን መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰን ጋብዘን እንደነበርና መልሳቸውንም ለእናንተ ማካፈላችን ይታወሳል። ቀጣዩን ክፍል ደግሞ በዚህ ወር ዕትማችን እናቀርባለን መልካም ንባብ።***

***ፏ.ሐመር፡-*** በአሁኑ ጊዜ የብዙዎች ትዳር ከሚፈርሱባቸው ምክንያቶች አንዱ በሩካቤ *ሥጋ* ጊዜ የስሜት አለመጣጣም ችግር እየተፈጠረባቸው እንደሆነ ጠቅሰዋል? ለዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን መፍትሔውስ?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ለዚህም ጥያቄ በርከት ያሉ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ዋና ዋና የምላቸውን ለመጥቀስ ልሞክር፡-

**ሀ. የግንዛቤ ችግር፡-** ስለ ሩካቤ የሚኖራቸው ግንዛቤ ምንአልባት ለአንዳንዶች ፍርሃት ሊሆን ይችላል። ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የአደጉበት ሁኔታ፣ ባህልና ልዩ ልዩ መንገዶች ምክንያት እየሆኑአቸው ወንድየው ሚስቱን ለመጠጋት ሚስትም ባሏን ለመጠጋት የሚፈሩበት ሁኔታ ይፈጠራል። ውስጣቸው ዝግጁ ስላልሆነ በግዴታ ቢቀርቡም ስሜታቸው ይቀዘቅዝና ለግብረ *ሥጋ* ግንኙነት ፍላጎት ያጣሉ።

ለሌሎች ደግሞ ሩካቤ *ሥጋን* እንደ ስሕተት መመልከት ሊሆን ይችል። እንዲሁ አስቀድመው በንጽሕና በቅድስና እንደቆዩ ሁሉ ሲያገቡም ከባልና ከሚስት ጋር የሚደረገውን ግብር እንደ ኃጢአት ሊቆጥሩት ይችላሉ። ራስን ጠብቆ በቤተ ክርስቱያን አስተምህሮ መሠረት ማደግ ተገቢ መንገድ ነው። ሆኖም ግን በዚህ ሁኔታ ቢያድጉም ወደ ትዳር ሲገቡ ደግሞ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው፤ ለመኝታቸውም ርኵሰት የለውም፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን



**መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ**

ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል" (ዕብ.፲፫፥፬) የተባለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ በመዘንጋት፣ ልጆች የሚተኩበት አምላካዊ ሕግ መሆኑንም ባለመረዳት የስሜት አለመጣጣም ችግር ሊከሠት ይችላል።

**ለ. ግልጽ አለመሆን፡-** ይህ ከፍቅር ማነስም የሚከሠት ሊሆን ይችላል በፍቅር ውስጥ ፍርሃት የለም። በፍቅር ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ጉዳይ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "ፍቅር ያሳታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቀናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር ልቡናን አያስታብይም፤ ብቻየን ይድላኝ አያሰኝም፤ አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርንም አያሳስብም፤ ጽድቅን በመሥራት ደስ ያሰኛል እንጂ ግፍን በመሥራት ደስ አያሰኝም፤ በሁሉ ያቻችላል፤ በሁሉ ያስተማምናል፤ በሁሉም ተስፋ ያስደርጋል፤ በሁሉም

ያስታግሣል።" (፩ቆሮ.፲፫፥፫-፯) በማለት ይዘረዝርልናል። ከልብ መዋደድ ሲኖር ይሉኝታ የለም፣ መተፋፈር የለም፣ ስሜትን በግልጽ አለመነጋገር አይቻልም። ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን መተፋፈር፣ መደባበቅ፣ በግልጽ አለመወያየት እየጠነከረ ይሀድና በመጨረሻም ለፍች ይዳረጋሉ።

**ሐ.ራስን አለመጠበቅ፡-** መንፈሳዊ ተግባራት ወሳኞች ናቸው። ይሁን እንጂ በሚያስፈልገው ወቅት ደግሞ የሚገባውን ምግብ መመገብና ዐቅምን ማጠናከር ሲገባ በጾም ወቅት በለመዱት መንገድ መጓዝና በምግብና በልዩ ልዩ መንገድ ዐቅምን አለመጠበቅ ለድካም ያጋልጣል። የአቅም ማነስ፣ ተደጋጋሚ ሊድን በሚችል በሽታ መያዝና መዳከምን ከዚህም ሲያልፍ ስሜት አልባ መሆንን፣ ሙሉ በሙሉ ስሜት አልባ ባይሆኑም ድካም ሊኖር ስለሚችል የፍላጎት አለመጣጣምን ያስከትላል ።

**መ. የጤንነት ችግር ሊኖር ይችላል።** አንዳንድ ጊዜ በተፈጥሮም ሆነ በሕመም ምክንያት፣ በሕክምናም ከመገናኛ (ከመራቢያ) አካላት ጋር በተገናኘ በወንዱም ሆነ በሴቷ ላይ የጤና ችግር ሊኖር ይችላል። የሚታይና አካላዊ የሆነ የጤና ችግር ባይኖርም የሥነ ልቡና ውድቀትም ሊከሠት ይችላል። በወንዱም ሆነ በሴቷ በኩል ራስን እንደ ዝቅተኛ ማየት ራስን እንደጤነኛ ሰው አለመቁጠር፣ የበታችነት ስሜትን አስቀድሞ ወደ አእምሮ መላክ፣ ወዘተ ሁሉ በግብረ ሥጋ አለመጣጣም ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ይኖረዋል። ይህ እንዳይፈጠር አስቀድሞ የጤናን ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል።

## መፍትሔ

ከላይ የተጠቀሱትን በአግባቡ መረዳት፡- በማንኛውም ጉዳይ አስቀድሞ ችግሩንና የችግሩን መንሥኤ በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል። ከላይ የተዘረዘሩት ደግሞ ለችግሩ መንሥኤዎች ናቸው። ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን በአግባቡ መረዳት ቀዳሚው ጉዳይ ነው።ከላይ የተዘረዘሩትን በአግባቡ ከመረዳት በተጨማሪ የሚከተሉትን ጉዳዮች ልብ ማለትም ያስፈልጋል።

**ሀ. በፍቅር መመሥረት አለበት፤**

**ለ. ሥነ ልቡናዊ ውድቀትን ማስተካከል፤**

**ሐ. መታገሥ በትዕግሥት ብናልፈው ሊስተካከል እንደሚችል ማመን፤**

**መ. አጉል ፍርሃትን ማስወገድ በተገቢው ጊዜ የሚደረግ ግንኙነት የተፈቀደ ስለሆነ ከይሉኝታና ከሃፍረት መውጣት፤**

**ሠ. መመካከር (መወያየት)፤**

**ረ. ለባለሙያ ወይም ለመምህረ ንስሓና በዕድሜ ለሚበልጡን፣ ማማከር።**

***፮. ሐመር፡-*** በባለ ትዳሮች መካከል አለመተማመን ይፈጠራል፤ ከፍ ሲልም መፋታታቸውን ሳያውጁ (በትዳር እያሉ) ወንዱ ከሌላ ሴት ሴቷም ከሌላ ወንድ ጋር አላስፈላጊ ግንኙነት ይፈጥራሉ። ይህ በትዳራቸውም ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት፣ ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮም አንጻር እንዴት ይታያል?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** በመጀመሪያ አለመተማመን ደረጃ ላይ ለምን ደረሱ የሚለውን ከችግሩ ልነሣ ባልና ሚስት ከላይም በተደጋጋሚ እንደተገለጸው አንድ አካል ናቸው። ይህ ሆኖ ሳለ ግን አይተማመኑም። ምክንያቱም፡-

**፩. በፍቅር አለመጋባት፡-** ጋብቻቸው በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ከሆነ ባልም ሆነ ሚስት ሌላ ሊታያቸው ሊታሰባቸውም አይችልም። ግን እንዲሁ አፍአዊ በሆነ መስፈርት የተመሠረተ ጋብቻ ልክ ሰርጉ እንዳበቃ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይቀየርና ከትዳርነት ይልቅ የጭቅጭቅ ቤት መሆን ይጀምራል።

**፪. ሳይለወጡ ማግባት፡-** እዚህ ላይ ለውጥ ማለት መንፈሳዊውን ለውጥ ነው። በሁለቱም በኩል ካወቁበትና ከተረዱት ጋብቻቸው ፍጹም ከሆነው የቅድስና ደረጃ ላይ ያደርሳል። ለዚህ ግን ቀደሞ የነበረ መጥፎ አመልን አስወግዶ ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ለውጥን ገንዘብ አድርጎ መግባት ያስፈልጋል። የቀድሞ ግብርን ሳይተውና መንፈሳዊ ለውጥ ሳይኖር ቢጋቡ ከጋብቻ በኋላም ወደ ቀደመ ማንነታቸው እየሄዱ በውስጣቸው አለመተማመናቸው እየሰፋ ይሀዳል።

**፫ ፈሪሀ እግዚአብሔር ሲጠፋ፡-** ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወት መሠረቱ ሊያደርግ ይገባዋል። ዮሴፍ በዘፍ.፴፱ ላይ ታሪኩ ተጽፎ እንደምናገኘው ሰው በሌለበት ጊዜና ቦታ የዝሙት ጥያቄ ቀርቦለት ነበር። ያውም ከእመቤቲቱ በዚህ ጊዜ ዮሴፍ "ሰው ባያይ እግዚአብሔር ያያል" በማለት አይሆንም አለ። የጲጥፍራ

ሚስት ባል እያላት፣ ሌላ ተመኝቶ ዛሬም ሰዎች በተለያየ ምክንያት ለምሳሌ በሥራ፣ በትምህርት፣ ወዘተ በተለያየ ቦታ ሲኖሩ ሰው ባያይ እግዚአብሔር ያያል ብለው ለትዳራቸው ለገቡት ቃል ኪዳን ለኅሊናቸው ይልቁንም ለእግዚአብሔር መታመን አለባቸው። ሚስት ባትኖር እግዚአብሔር ያየኛል ባል ባይኖር እግዚአብሔር ያየኛል በማለት ቸልተኝነትንና ግዴለሽነትን ማስወገድ ያስፈልጋል።

## ጉዳቱን እናንሣ

**፩. ኀጢአት ነው፡-** እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ ከሰጠው ዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ "አታመንዝር" (ዘፀ.፳፥፲፬) የሚለው ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ተላልፎ እንዲህ ያለ ሥራ መሥራት ኃጢአት ነው። የኃጢአት ደሞዝ ደግሞ ሞት ነው። ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ "የነፍስ ገዳዮችም፣ የሴሰኞችም፣ የአስማተኞችም፣ ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲኝና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ውስጥ ነው፤ ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው" (ራእ.፳፩፥፰) በማለት እንደተናገረው። ከሥጋ ፍሬዎቹም አንዱ ነው። (ገላ.፭፥፲፱) ስለዚህ የነፍስ ሞትን የሚያመጣ ኃጢአት ነው። ኃጢአተኛን ኃጢአቱ ተቀጣዋለች እንደሚል ሁሉ ቅጣት ያደርስበታል።

**ልጆች የሚቀረጹት እናት አባቶቻቸው በሚያሳዩአቸው ነገር ነው። ልጆች ክፉውንም በጎውንም ከቤተሰቦቻቸው ይማራሉ። በቃል ከምንሰብካቸው በላይ የአባትና የእናት ተግባር ያስተምራቸዋል። ስለዚህ ባልና ሚስት አለመተማመን የሰፈነበት ኑሮ የሚኖሩ ከሆነ ልጆችም በውስጣቸው ተቀርጾ የሚያድጉት አሉታዊ የሆነው የእናትና የአባቶቻቸው ጠባይ ነው።**

**፪. በሽታን ያስከትላል።** በሽታ አስተላላፊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ ዝሙት ነው። በዝሙት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ደግሞ በሰው ሰውኛው እስከማይድን በሽታ ይደርሳል። ይህ ደግሞ ለራስም ለጋብቻ አጋርም፣ እልፍ ሲልም ለቤተሰብ ሁሉ ጠንቅነው።

**፫. የሥነ ልቡና ጉዳት ያስከትላል፡-** ባለመተማመን ወደ ሌላ በመወስለት የሥነ ልቡና ጉዳት ይደርስበታል። ሚስቱ ሳታየው ከሌላ ጋር ዝሙት የፈጸመ ሰው መቼም ቢሆን ውስጡ ጤነኛ ሊሆን አይችልም። ታወቀብኝ አልታወቀብኝ በማለት ውስጡ ይጨነቅበታል። ኅሊናው ይካሰስበታል። ከምንም ባለይ ሰው ያላየኝ ቢመስለው ከኅሊና ዳኝነት ሊያመልጥ ወይም ሊሠወር አይችልምና በመጨረሻ የሥነ ልቡና ጉዳት ያስከትልበታል።

**፬. ትዳር ይፈርሳል፡-** ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ባለመተማመን የሚከሠቱ ናቸው። በዚህ ምክንያት ከሁለቱ አንዱ በትዳራቸው መኖርን አልፈልግም ቢል ይችላልና ትዳራቸው ሊፈርስ ይችላል። እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮም በዝሙት ምክንያት ከሆነ ትዳር እንዲፈርስ ይፈቀዳል። መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለፍቺ በተጠየቀበት ወቅት "ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም ያገባ ያመነዝራል" (ማቴ.፲፱፥፱) በማለት የመለሰው መልስ በዝሙት ምክንያት ከሆነም መፋታት ኃጢአት እንዳልሆነ ያስረዳናል። ስለዚህ ለነፍሳቸውም ሆነ ለሥጋቸው በማይጠቅም የዝሙት ሥራ ትዳርን ማፍረስ ትልቅ ጉዳት ስለሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

**፭. የልጆች አሉታዊ ጠባይ መውረስ፡-** ልጆች የሚቀረጹት እናት አባቶቻቸው በሚያሳዩአቸው ነገር ነው። ልጆች ክፉውንም በጎውንም ከቤተሰቦቻቸው ይማራሉ። በቃል ከምንሰብካቸው በላይ የአባትና የእናት ተግባር ያስተምራቸዋል። ስለዚህ ባልና ሚስት አለመተማመን የሰፈነበት ኑሮ የሚኖሩ ከሆነ ልጆችም በውስጣቸው ተቀርጾ የሚያድጉት አሉታዊ የሆነው የእናትና የአባቶቻቸው ጠባይ ነው።

***፮. ሐመር፡-*** ትዳራቸው የተባረከና ፍጹም ፍቅር የሰፈነበት እንዲሆን ባለትዳሮች ምን ማድረግ አለባቸው?

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-***

**ሀ. ፍቅርን ገንዘብ ማድረግ፡-** ፍቅር ለባለትዳሮች ከምንም በላይ አስፈላጊ ነው። ‹‹ዘአፍቀረ ብእሲቶ ርእሶ ፈፍቀረ፤ ሚስቱንም የሚወድ ራሱን ወደደ›› (ኤፌ.፭፥፳፰) በማለት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እንደራሱ አካል የመውደድን ጥበብ ተላብሶ መኖር ይገባል፡፡ የትዳር ሕይወት ማስተዋልን፣ ፈሪሀ እግዚአብሔርን፣ ፍቅርን ወዘተ ገንዘብ አድርገው ሲኖሩበት የሚታወቅና የሚለመድ እንጂ በትምህርት የሚማሩት፣ በሥልጠና የሚያዳብሩት አይደለም፡፡ ፍቅርን ገንዘብ አድርገው ሊኖሩ ይገባል፡፡ ከውጫዊው ይልቅ በውስጣዊው ማንነታቸው እየተደሰቱ እንዲኖሩ እንጂ ባልም ሆነ ሚስት ለልጁ ስል ነው የምኖረው እንዲሉ አይመከርም፡፡ ልጅ ማሳደግ ግዴታቸው ነውና፡፡

**ለ. ዘወትር ስለ ትዳር ማወቅ፡-** በትዳር ውስጥ ሁል ጊዜ ደስታ ላይኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን አስቀድመው ከመግባታቸው በፊት ስለትዳር ማወቅ አለባቸው ቢባልም በየጊዜው የሚፈጠሩ ጉዳዮች የተለያዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ሁሌም ስለትዳር መማርና ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ትዳር "ትንሺ ቤተ ክርስቲያን ናት" ተብሏልና ብዙ ነገሮችን የምንማርበት ትምህርት ቤትም ነውና ስለሕይወትም ስለ ትዳርም ስለ ብዙ ነገር እንማራለን፡፡

**ሐ. ጊዜ መስጠት፡-** ጊዜ መስጠት ማለት አንድ ላይ መቀመጥ ብቻ አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች "በጊዜነው ቤቴ የምገባው" ይላሉ፡፡ በጊዜ ገብቶ አንድ ላይም ተቀምጠው አንድ ላይ የማይሆኑበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ የሚወያዩበት፣ እርሱ ስለ እርሷ እርሷም ስለ እርሱ የሚነጋገሩበት የጋራ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡ አብሮነት "እንዳይታጐል" እንደሚባለው መሆን የለበትም፡፡ ጓሊናቸውን የሚጠልፍ ነገር ካለ እርሱን አስወግደው በግልጽ የሚወያዩበትና የሚመካከሩበት ጊዜ መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡

**መ. ይቅርታ መደራረግ፡-** ምንም አንድ አካል ናቸው ቢባልም ይህን በጥልቀት ያልተረዱ ባልና ሚስት ሁል ጊዜ እርሱም ስለራሱ እርሷም ስለ ራሷ የሚጨነቁበት ጊዜ ይኖራል፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱ ሌላውን ሊያስቀይም ይችላል፡፡ እንዲህ የመቀያየም ሁኔታ ሲፈጠር በቶሎ ይቅርታ መጠያየቅ ያስፈልጋል፡፡ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የተባለው ሰው በሚስቱ ላይ ቂም መያዝ የለበትም፡፡

**ሠ. በመንፈሳዊ ምግባራት መትጋት፡-** ከመምህረ ንስሓ ጋር ዕለት ዕለት እየተመካከሩ፣ እየጾሙ ንስሓ እየገቡ ሥጋውን ደሙን እየተቀበሉ በመንፈሳዊ ሕይወትና በመንፈሳዊ ምግባራት ጸንተው ሊኖሩ ይገባል፡፡ በቃና ዘገሊላ በተዘጋጀው ሰርግ የወይን ጠጅ ማለቅ ችግር ነበር፡፡ ችግሩ ግን አልዘለቀም፡፡ ምክንያቱም ባለቤቱን ጠርተውታልና፣ የባለቤቱ የጌታ እናት ድንግል ማርያምና ደቀ መዛሙርቱም በዚያ አሉና፡፡ ባለትዳሮችም በጾም፣ በጸሎት፣ በምጽዋት፣ በንስሓ፣ በቅዱስ ቁርባን ሕይወት ጸንተው ሲኖሩ፣ እግዚአብሔርን በትዳራቸው ሲይዙት ትዳራቸው የአማረ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ትዳር መፍረስ አይደለም ለሌሎችም ማስተማሪያ የሚሆን አርአያነት ያለው የእነከሌን ትዳር ተመልከቱ የሚባል ይሆናል፡፡

***ጅ. ሐመር፡-*** በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ዕድሉን እንስጥዎት፡-

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** ተጋቢዎቹ ቅድመ ጋብቻ የትዳርን ምንነት፣ በረከቱን፣ በትዳር ውስጥ የሚኖረውን ፈተና ወዘተ የመሳሰለውን ሁሉ አስቅድመው መረዳት አለባቸው፡፡ ምንም እንኳን ሰውን ማጥናት ከባድ ቢሆንም መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን አስቀድሞ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ መኪና በሙከራ የሚለመድ ቢሆንም መሠረታዊ የሆነውን ዕውቀት ግን አስቀድመው ይይዙታል፡፡ ዛሬ ዛሬ ትዳርን የመንጃ ፈቃድ ያህል እንኳን ቦታ ሲሰጡት አይስተዋሉም፡፡ ስለዚህ ቅድመ ጋብቻ በጥንቃቄ ተመልክተው ማወቅ ያለባቸውን መሠረታዊ ነገር ዐውቀው ሊገቡ ይገባል፡፡

በትዳር ውስጥ ያሉትም ብዙ ነገሮች በጊዜ ሂደት በልምምድ የሚስተካከሉ መሆናቸውን መረዳትና ማመን ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ መንፈሳዊ ጉዳዮች በመንፈሳዊ ልምምድ፣ የገቢ ጉዳይ ቀስ እየተባለ በጊዜ ሂደት፣ የጤና ችግርም ካለ እንዲሁ ይስተካከላል የሚለውን ማመን ይኖርባቸዋል፡፡ አንድ ተማሪ ተምሮ ያሰበው ላይ እስኪደርስ ብዙ ደብተር ሊጨርስ ይችላል፡፡ ግን "ለበጐ ነው" ብሎ በትዕግሥት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹ችኩል ለመጉደል ይቸኩላል›› ይባላልና በችኮላ የሚሆን ነገር ስለሌለ ትዳርንም በትዕግሥት መምራት ያስፈልጋል፡፡ የእርስ በእርስ ውይይትንም ማዳበር፣ ሁል ጊዜም በግልጽ በመካከር ለችግሮች ሁሉ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል፡፡

***ሐመር፡-*** ውድ ጊዜዎትን ሠውተው ላነሣናቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢውን ማብራሪያ ስለሰጡን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡

***መጋቤ አእላፍ ቀሲስ ፋሲል ታደሰ፡-*** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

✞ ✞ ✞

# እንደ ራባቸው ሊሄዱ አይገባም



*በቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን*

ቃሉን የተናገረው ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ የተናገረበት ምክንያት ከየአቅጣጫው የተሰበሰቡት ሕዝብ ለተለያየ ፍላጎት እንደሆነ ያውቃልና ከፍላጎታቸው አንዱ ደግሞ አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት "በሉ እጅግም ጠገቡ ለምኞታቸውም ሰጣቸው፡፡ ከወደዱትም አላሳጣቸውም" (መዝ.፸፯፥፳፱) ተብሎ እንደተነገረ ኅብስት አበርክቶ ያበላናል ብለው የመጡ ነበሩ፡፡ እነዚህ ከየሰፈሩ የተሰበሰቡት ሰዎች እንደተራቡ ያውቃልና ደቀ መዛሙርቱ ቀድሞ እንዲያሰናብታቸው ሲጠይቁት "የሚበሉትን ስጧቸው እንጂ እንደራባቸው ሊሄዱ አይገባም" በማለት ተናገረ፡፡ ሙሉ ፅንሰ ሐሳቡን እንጥቀስና ዝርዝር ጉዳዩንም እንመለከታለን፡፡

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው በቅዱስ ወንጌል "ጌታችን ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ በታንኳ ሆኖ ከዚያ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤ ሕዝቡም ሰምተው ከየመንደሩ በእግር ተከተሉት፡፡ በወጣም ጊዜ ብዙ ሰዎችን አይቶ አዘነላቸው፤ ድውዮቻቸውንም አዳነላቸው፡፡ በመሸ ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ቦታው ምድረ በዳ ነው ሰዓቱም አልፏል፤ ወደ መንደር ገብተው ምግባቸውን ይገዙ ዘንድ ሕዝቡን አሰናብታቸው አሉት፡፡ ጌታችን ኢየሱስም እንደራባቸው ሊሄዱ አይገባም እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው እንጂ አላቸው፡፡" (ማቴ.፲፬፥፲፫-፲፯) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡፡

ሰው የሚቸገረው በምግብ ብቻ አይደለም፡፡ መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈትነው ለመጣው ጠላት ዲያብሎስ የመለሰለት መልስ በቅዱስ ወንጌል "ሰው የሚኖረው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ እንዳይኖር ተጽፏል አለው" (ማቴ.፬፥፬) ተብሎ እንደተጻፈ ከቃለ እግዚአብሔር የተለየ ይኖራል፤ የጤና ችግር ያለበት ይኖራል፤ ከኀኑ ሆኖ አይዞህ የሚለው አጥቶ በብቸኝነት የሚቸገር ሊኖር ይችላል፤ በሥነ ልቡና ተጎድቶ ችግር ላይ የወደቀ ሊኖር ይችላል፤ በእንደዚህና በሌላውም መሰል ችግር የወደቀ ሰው ረኃብተኛ ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በዋናነት ወደዚህ ዓለም የመጣው ድኅነተ ነፍስን ለሰው ልጅ ሁሉ ለማደል ቢሆንም ድኅነተ ሥጋንም እንዲሁ አድሏል፡፡ ከላይም እንደተገለጸው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት "ከወደዱትም አላሳጣቸውም" (መዝ.፸፯፥፳፱) በማለት እንደተናገረው በልዩ ልዩ ፍላጎት የመጡትን እንደየችግራቸውና እንደየ ፍላጎታቸው አስተናግዷቸዋል፡፡

ሰዎቹ የሚደረግላቸው የአቀባበል ሁኔታ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ሰው ለችግሩ መፍትሔ ከማግኘቱ በፊት መልካም አቀባበል ሲያደርጉለት እጅግ ደስ ይለዋል፡፡ አበው በብሂላቸው "ከፍትፊቱ ፊቱ" እንዲሉ፡፡ ወደ መፍትሔ ከመሄድ አስቀድሞም ችግሩ ምንድን ነው? ብሎ ሊረዱት ይገባል፡፡ በተረዱት መጠንም ሊያዝኑለትና የሚችሉትን ለማድረግ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "ዐይቶ አዘነላቸው" እንደተባለ ችግራቸውን ተረድቶ አዘነላቸው፡፡

አሁን ያለንበት ወቅት እንደሚታወቀው ታላቁ ጾም ጾመ ኢየሱስ ነው፡፡ ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታም ስንመለከት በሰው ሰውኛው ችግሩን መፍታት ይቅርና ዘርዝረን መጨረስ እንኳን አይቻለንም፡፡ ስለሆነም የጀመርነውን ጾም መጾም ባለብን አግባብ ብናከናውነው አሁን ያለንበትን ሀገራዊ ችግርም ለመፍታት ያግዘናል፡፡ በማንኛውም ጊዜ መልካም ነገርን ለመፈጸም መትጋት ቢኖርብንም ከመቼውም ጊዜ በላይ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት መትጋት ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ፡- ከጾም ጋር አብረው ሊፈጸሙ የሚገባቸው ወይም ከጾም የማይነጣጠሉ ተግባራት አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ በርቱዐ ሃይማኖት እንዲህ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ "በጽሐት ጾም እመ ኵሉ ምግባራት ጸሎት እኅታ ወምጽዋት ወለታ ለሠለስቲሆን አሐዱ ብሔሮን ወአሐዱ አቡሆን፣ ወአሐቲ እሞን እስመ ይትወለዳ ጥዩቀ እምቅድስት ማኅፀን ዘውእቱ ሃይማኖት በአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ የምግባራት ሁሉ እናት የሆነች ጾም ደረሰች፤ ጸሎት እኅቷ፣ ምጽዋት ልጇ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ለሦስቱ ሀገራቸው አንድ

ነው፤ አባታቸው አንድ ነው፤ እናታቸውም አንዲት ናት፤ ከተቀደሰች ማኅፀን ተወልደዋልና፡፡ ይኸውም አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ነው" (ምንባብ ዘጥንተ ጾም) እንዲል፡፡

በዚህ ምንባብ የማይነጣጠሉ ሦስት ነገሮችን እነዚህ ሦስት ነገሮች ደግሞ የሚወለዱባትን (የሚገኙበትን) የተቀደሰች ማኅፀን እንመለከታለን፡፡ ጾም የበጎ ምግባራት ሁሉ መገኛ ስትሆን ጸሎት እኅቷ፣ ምጽዋት ደግሞ ልጇ እንደሆነች ይነግረናል፡፡ እነዚህ ቤተ ሰቦች አይነጣጠሉም፡፡ ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ የሌሎች እርዳታ እጅግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንኳንስ በሚታይ፣ ለመሸከም እጅግ በሚከብድ ችግር ውስጥ ወድቀው ሳለ የሰዎች መኖር ለእነርሱ መኖር ወሳኝ ነው፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት መንፈሳዊ ተግባራትም እንዲሁ የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

ሊቁ ከተቀደሰች ማኅፀን ተወልደዋልና ይለንና የተወለዱባት የተቀደሰች ማኅፀን ደግሞ "አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ነው፡፡" ይለናል፡፡ በእግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት የማያምን ሰው አይጾምም ባይባልም በጾሙ ግን ዋጋ አያገኝም፡፡ በመጾሙ ዋጋ የሚያገኘው በእግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት አምኖ ሲጾም ነው፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ምእመናን በላከው መልእክቱ "ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሊያምን ይገባዋል" (ዕብ.፲፩፥፮) በማለት እንደተናገረው እምነት መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር አንድነት ሦስትነት ማመን ካልቻለ ጾሙ ዋጋ ሊያስጠው አይችልም፡፡ እንዲሁም ጾም እንደሚያድነው የማያምን ሰው አይጾምም፡፡ ስለዚህ የተወለዱባትን የተቀደሰች ማኅፀን "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማመን" ናት በማለት ያስረዳናል፡፡

በመሆኑም ስንጾም እኅቷን ጸሎትን መጋበዝ ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ማለት ስለእኛም ሆነ ስለ ተቸገሩት ሁሉ ልንጸልይ፣ በረኀብ፣ በጥም፣ በመጠለያ እጦት፣ በፍትሕ መጓደል ወዘተ እየተቸገሩ ያሉትን በጸሎታችን ልናስባቸው ይገባል፡፡ እናቲቱን ስንጠራ ልጇ የተባለችውን ምጽዋትንም እንዲሁ እንጠራና የተራቡትን ልናበላቸው፣ የተጠሙትን ልናጠጣቸው፣ መጠለያ ያጡትን ልናስጠጋቸው፣ በሥነ ልቡና የተጎዱትን የምክር አገልግሎት በመስጠት መንፈሳዊ ሕክምና ልናደርግላቸው፣ ብቸኝነት ያንገላታቸውን ከጎናቸው ሆነን አለንላችሁ ልንላቸው ይገባል፡፡ ምጽዋትም የሚፈጸምበት መንገዱ ብዙ ነውና ከላይ በተዘረዘረው ሁሉ መሳተፍ ይኖርብናል፡፡

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በእስራኤል ዘንድ የነበረውን ጾምና እነርሱ እየጾሙበት የነበረበትን መንገድ "ስለምን ጾምን አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለምን አዋረድን አንተም አላወቅኸንም? ይላሉ፡፡ እነሆ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፡፡ እነሆ ለጠብና ለክርክር ትጾማላችሁ፤ ድሃውንም በጡጫ ትማታላችሁ፤ በምትጮኹበት ጊዜ ድምፃችሁ እንዲሰማ ለእኔ ትጾማላችሁን? ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም እኔ ይህን ጾም የመረጥሁት አይደለሁም፤ እንደዚችም ባለች ቀን ሰው ራሱን ቢያሳዝን አንገቱንም እንደቀለበት ቢያቀጥን ማቅ ለብሶ በአመድ ላይ ቢተኛ ይህ ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ አይደለም፡፡ ይህን ጾም የመረጥሁት አይደለም ይላል እግዚአብሔር፡፡" በማለት ገልጾት እናገኛለን፡፡

**ፍቅር የሕግ ሁሉ ማሰሪያ፣ በሃይማኖት የመኖራችን መሠረት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ልንወድ ማለትም ሕጉን ልንፈጽም እንዲሁም ባልንጀራችንንም ልንወድ ይገባናል፡፡**

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ያለውን ጾም እግዚአብሔር እንዳልተቀበለላቸው፣ ያልተቀበለበት ምክንያትም ምን እንደሆነ ከነገራቸው በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፡፡ "ነገር ግን የበደልን እስራት ፍታ፤ ጠማማውን ሁሉ አቅና፤ የተጨነቀውንም ሁሉ አድን፤ የዐመፃ ደብዳቤንም ተው፡፡ ለተራበውም እንጀራህን አጥግበው፤ ድሆችን ወደ ቤትህ አስገብተህ አሳድራቸው፤ የተራቆተውንም ብታይ አልብሰው፤ ከሥጋ ዘመድህ አትሸሽግ፡፡ ያን ጊዜ ብርሃንህ እንደ ንጋት ይበራል፤ ፈውስህም ፈጥኖ ይወጣል፤ ጽድቅህም በፊትህ የሄዳል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ይጋርድሃል" (ኢሳ.፶፰፥፮-፰)፡፡

በዚህ ኃይለ ቃል ነቢዩ ኢሳይያስ በርከት ያሉ ቁም ነገሮችን አስተላልፏል፡፡ ከተናገራቸው ቁም ነገሮች መካከል በተወሰነ መልኩ ዘርዘር አድርገን ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ነጥቦች እናገኛለን፡፡

**ሀ. የበደልን እስራት ፍታ፡-** ዛሬ ዛሬ እየተፈጸመ ያለውን በደል እንኳንስ ልንቋቋመው ስንሰማው ይዘገንናል፡፡ ይህን ግፍ እየፈጸሙ ያሉ አካላት ሊያሳኩት የሚፈልጉት ዓላማ ስላላቸው በአርአያ እግዚአብሔር በተፈጠረ ሰው ላይ እንዲህ ያለ ግፍ ሲፈጽሙ ምንም መስሎ አይታያቸውም፤ ይሁን እንጂ ይህን ግፍ ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ባይቻልም በመተባበርና በመደጋገፍ ልንቀንሰው እየተገፉ ላሉትም ልንደርስላቸው ይገባል፡፡ "የበደልን እስራት ፍታ" ስንባልም ሕግ ጥሶ፣ ወንጀል ሠርቶ የጠባይ ማስተካከያ እንዲያደርግ በሕግ አግባብ የተያዘውን አይደለም፡፡ በግፍ ያለምንም ወንጀል የታሰሩ፣ ምን አልባትም ለመሪዎች የተሳሳተ አሠራር አልመች ስላሉ የግፍ ቀንበር የተጫነባቸው በርካታ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሁሉ በመድረስ የምንችለውን ልናደርግ ይገባል፡፡

**ለ.የተጨነቀውንም ሁሉ አድን፡-** የሰዎች ጭንቀት በብዙ መልኩ ሊመጣ ይችላል፡፡ በእነርሱ ደረጃ መፍታት የማይቻል መስሏቸው በጭንቀት ውስጥ ያሉትን እንደየችግራቸው ዓይነትና መጠን በመቅረብ ከገቡበት ጭንቀት የሚወጡበትን መንገድ መፈለግ የግድ ይላል፡፡ ምን አልባትም በቃል አትጨነቁ ከማለት ባለፈ ቀረብ ብሎ የችግሩን ሁኔታ በመረዳት ተግባራዊ ምላሽ የሚያስፈልገውን በተግባር እየመለሱ ሰዎችን ማረጋጋት ይገባል፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ የእስራኤልን መከራ ሲገልጽ "በከተማ ጎዳና እንደ ተወጋ ሰው በዛሉ ጊዜ ነፍሳቸውም በእናቶቻቸው ብብት እለይ እለይ ባለች ጊዜ እናቶቻቸውን እህልና ወይን ወዴት አለ? ይሏቸዋል፡፡" (ሰቆ.ኤር.፪፥፲፪) በማለት እንደተናገረው ሕፃናት ልጆቻቸውን እንዳዘሉ ከቤታቸው ተፈናቅለው ሕፃናቱ የእነርሱን ችግር ሳይረዱ ቀርተው ምግብ እንዲሰጧቸው በየሰዓቱ ሲያለቅሱባቸው እናቶች በውስጣቸው ሊፈጠር የሚችለውን ጭንቀት መረዳት አይከብድም፡፡ በዚህ ሁሉ ከጎናቸው ሆነን አይዟችሁ ልንላቸውና ልናረጋጋቸው ይገባል፡፡

**ሐ. ለተራበውም እንጀራህን አጥግበው፡-** ይህ የችግር ዓይነቱም በሚገባ ተለይቷል፤ ሌላ ችግር አይኖርበትም ባይባልም ግን በስም ተጠቅሶ የተራበውንም እንጀራ አጥግበው ተብሏል፡፡ በረኃብ እየተሠቃየ ያለውን ሰው ልምከርህ፣ ላረጋጋህ፣ ወዘተ. ቢሉት ሊሰማን አይችልም፡፡ ስለዚህ በምንችለው መጠን አነሰ በዛ ሳንል ያገኘነውን ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማድነቅ እንደተናገረላት "ጌታችን ኢየሱስም በሙዳየ ምጽዋት ፊት ለፊት ተቀምጦ በሙዳየ ምጽዋቱ ገንዘብ የሚጨምሩ ሰዎችን ያይ ነበር፤ ብዙ ባለጸጎች ብዙ ገንዘብ ይጨምሩ ነበር፡፡ አንዲት ደሃ መበለትም መጥታ ቆንደራጢስ የሚሉትን ሁለት መሐልቅ አገባች፡፡ ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ እንዲህ አላቸው፡፡ እውነት እላችኋለሁ በሙዳየ ምጽዋቱ ውስጥ ገንዘብ ካገቡት ሁሉ ይህቺ ደሃ መበለት አብዝታ አገባች፡፡ ያገቡ ሁሉ ከትርፋቸው አግብተዋልና፤ እርሷ ግን ከድህነቷ የነበራትን ንብረቷን ሁሉ አግብታለችና፡፡" (ማር.፲፪፥፵፩-፵፬) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ በምንችለው መጠን ማገዝ እንጂ እየተራብ እያየን እንዲሁ ማለፍ የለብንም፡፡ ከላይም እንደተጠቀሰው በዚህ በጾም ወቅት እናናቱን ጾምን ገንዘብ ስናደርግ ልጇን ምጽዋትንም አብረን ከመንፈሳዊው አገልግሎት ማሳተፍ ይኖርብናል፡፡

**መ. ድሆችን ወደ ቤትህ አስገብተህ አሳድራቸው፡-** ድህነት የባሕርይ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንግዚአብሔር ባወቀ አንዱን ደሃ አንዱን ሀብታም ያደርገዋል፡፡ ይልቁንም በአሁኑ ወቅት በሰው ሠራሽ ችግሮች ብዙዎች ከድህነት ጎጆ እንዲጠለሉ ሆነዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ፈጥኖ መድረስና ቤቴ የእግዚአብሔር እንጂ የእኔ አይደለምና በደህነት የሚቸገሩ ሰዎች ሊያርፉበት ይገባል ልንልና ልናስጠጋቸው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር በቤታችን ያድር ዘንድ ቤታችንንም ይባርክ ዘንድ ከፈለግን

ከቤታቸው ተፈናቅለው ስደተኛ ሆነው የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር የሚፈራረቅባቸውን ሰዎች ከቤታችን እናሳድራቸው:: እንዲህ የመሰለውን መልካም ሥራ እየሠራን ስንጾም ጾማችንም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል::

ሠ.የተራቆተውንም ብታይ አልብሰው፡- ብዙዎች ሀብት ንብረታቸው ተዘርፎ ሀብታም የነበሩት ደሃ ሆነው፣ ቤት ንብረት የነበራቸው አሁን ምንም የሌላቸው ሆነው፣ በየጊዜው ልብስ እያማረጡ ይለብሱ የነበሩት አሁን መቀየሪያ እንኳን ሳይኖራቸው እንዲያውም በብርድ እየተሠቃዩ ይገኛሉ:: በዚህ ጊዜ የተራቆተውን ማልበስ ጾማችንን እውን ያደርገዋል:: በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ራቁቱን ሆኖ ሲሠቃይ እያዩ እንዳላዩ ሆነው ቢያልፉት እግዚአብሔርን ራቁቱን እያየነው ዝም ብለን እንዳለፍነው መቊጠር ይኖርብናል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን የቀረሰለት፣ ደሙን ያፈሰሰለት ክቡር ፍጥረት ነውና ይህ ሰውነት ራቁቱን ሆኖ በቀን ሐሩር በሌሊት ቁር ሲሠቃይ ማየት እጅግ የሚከብድ ችግር ነውና ልናስብበት ይገባል::

ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ ጾማችን ከእነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት ጋር መፈጸም እንዳለበት ያስገነዝበናል:: ካልሆነ ግን የግፍ ግፍ እየሠራን፣ ተበድለው እያየናቸው ሳናዝንላቸው ጾምን የምንል ከሆነ እግዚአብሔር አይቀበለውም:: ነቢዩም "ይህን ጾም የመረጥሁ አይደለም ይላል እግዚአብሔር" (ኢሳ.፶፰፥፯) በማለት የነገረን መልካምነት ሳይታከልበት የሚጾምን ጾም ነው::

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ "እናንተ ግን በሥራው ሁሉ እየተጋችሁ በእምነት በጎነትን ፣ በበጎነትም ዕውቀትን ጨምሩ፤... እግዚአብሔርንም በማምለክ ወንድማማችነትን፣ በወንድማማችነትም ፍቅርን ጨምሩ፤ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጋችኋልና" (፪ጴጥ.፩፥፭-፰) በማለት ማንኛውም ሰው በሃይማኖት ሲኖር ገንዘብ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነገሮችን አስረድቶናል:: እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አንዱን ብቻ ይዘን ይበቃኛል የምንላቸው ሳይሆን አንዱን በሌላው ላይ እየጨመርን መንፈሳዊ ሕይወታችንን የምናሳድገባቸው መንግሥቱን የምንወርስባቸው ምግባራት ናቸው:: ሃይማኖታችን፣ በበጎነት፣ በወንድማማችነት፣ እርስ በእርስ በመዋደድ ሲገለጽ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንሆናለን በእንደዚህ ያለው መልካም ሥራችንም እግዚአብሔር ይደሰትበታል::

ፍቅር የሕግ ሁሉ ማሰሪያ፣ በሃይማኖት የመኖራችን መሠረት ነው:: እግዚአብሔርን ልንወድ ማለትም ሕጉን ልንፈጽም እንዲሁም ባልንጀራችንንም ልንወድ ይገባናል:: ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ "እኛም እርስ በእርሳችን እንዋደድ፤ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና:: እግዚአብሔርን እወደዋለሁ የሚል ወንድሙን ግን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው፤ የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ ግን የማያየውን እግዚአብሔርን እንደምን ሊወደው ይችላል? እግዚአብሔርን እንወደው ዘንድ ወንድማችንንም እንወድ ዘንድ ከእርሱ የተቀበልነው ትእዛዝ ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን የሚወድ ሁሉ ወንድሙን ይወዳል" (፩ዮሐ.፩፥፲፱-፳፩) በማለት የሕይወታችን መሠረት የሆነውን ገንዘብ ማድረግ እንዳለብን ያስረዳናል::

በአጠቃላይ በምንኖርባት ዓለም አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ ነው:: ሰው በራሱ ፍጹምና ምሉእ አይደለም:: ስለዚህ እርስ በእርስ መረዳዳት፣ የአንዱን ጉድለት ሌላው መሙላት ይኖርበታል:: ይልቁንም በአሁኑ ወቅት ችግረኞች የበዙበት፣ ችግራቸውም በየዘርፉ የሆነበት፣ ከፊሉ የሚራብበት፣ ከፊሉ መጠለያ አጥቶ በሜዳ ላይ የወደቀበት፣ ከፊሉ፣ በሥነ ልቡና ጫና ወድቆ መመለሺያ የሌላው በሚመስል የአእምሮ ሕመም የወደቀበት፣ ብቻ ዘርፉ ብዙ በሆነ መልኩ እየተቸገረ ያለበት ነው:: በዚህ ጊዜ መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእኔ ተማሩ" ብሎናልና እርሱን አብነት አድርገን ለችግረኞች ልንደርስላቸው "እንደራባቸው ሊሄዱ አይገባቸውም" ልንላቸው ይገባል:: ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን:: ✝ ✝ ✝

# ዘር ቆጣሪ

*በእንዳለ ደምስ*

የቀኑ ሐሩር እናት ይበሳል፣ ከአስፋልቱ ግለት የሚወጣው ወላፈን ፊትን ከመለብለብ አልፎ ልብ ይሰልባል፡፡ በዚያ ጠራራ ፀሐይ እመቤት ከንስሓ አባቷ ጋር ለያዘችው ቀጠሮ በሰዓቱ ለመድረስ እየተጣደፈች ከአራት ኪሎ ቁልቁል በመውረድ፣ በፓርላማ በኩል አድርጋ ወደ ታእካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም አቀናች፡፡ ቁና ቁና እየተነፈሰች ታእካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ስትደርስ አማትባ ወደ ውስጥ በመግባት በስተቀኝ ካለው ዛፍ ሥር ድንጋይ ላይ ዐረፍ አለች፡፡ ቀይ ፊቷ ብስል ቲማቲም መስሏል፤ በነጠላዋ ጫፍ የፊቷን ላብ ጠርጋ በረጅሙ "ኡፍፍፍፍ…" ብላ የድካም አየር አስወጥታ ዛፎቹና ንፋሱ ከሚፈጥሩት ቀዝቃዛ አየር ወደ ውስጥ ሳበች፡፡ ጥቂት ዕረፍት አድርጋ አስፋልቱን ይዛ በቀዝቃዛ አየር ታጅባ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራች፡፡ የታእካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ግቢ በጥንታዊ ሀገር በቀል ዛፎች እንደተከበበ ግርማ ሞገሱን ተላብሶ ይታያል፣ ነፋሻማው አየር ደግሞ ለነፍስ ሐሤትን ያጎናጽፋል፣ የአዕዋፋቱ ዝማሬ በተመስጦ ሰማየ ሰማያት አድርሶ ይመልሳል፡፡

እመቤት ቅዳሴ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለደረሰች ግቢው ውስጥ የሰው ዘር አይታይም፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዳቀናች በሴቶች መግቢያ በኩል በማምራት ተንበርክካ በመሳለም የልቡናዋን መሻት ይፈጽምላት ዘንድ ፈጣሪዋን፣ እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በምልጃዋ እንድትረዳት ስትማጸን ቆየች፡፡

የኔታ ወልደ ዮሐንስ ከቅዳሴ በኋላ ጥቂት ዕረፍት ወስደው በቀጠሯቸው መሠረት እመቤትን ለማግኘት በገዳሙ ግቢ ውስጥ ካለው ማረፊያ ቤታቸው በመውጣት ወደ ሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት በማምራት ከተሳለሙ በኋላ እመቤትን ፍለጋ በዐይኖቻቸው ግራ ቀኝ አማተሩ፡፡

እመቤት ቀድማ ስላየቻቸው በፍጥነት ወደ ንስሓ አባቷ አመራች፡፡ መስቀል ተሳልማ ከዛፎቹ መካካል በመግባት ጠፍጣፋ ድንጋዮችን ፈልገው ተቀመጡ፡፡ ሁለቱም ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ጤንነት፣ ከተጠያየቁ በኋላ በመካከላቸው ጸጥታ ሰፈነ፡፡ የኔታ ወልደ ዮሐንስ እመቤት ልትነግራቸው የፈለገችውን ነገር ለመስማት ከአሁን አሁን ትናገራለች ብለው እየጠበቁ ነው፤ እርሷ ደግሞ ከየት እንደምትነሣ ግራ ገብቷት የምትጀምርበትን ጫፍ ፍለጋ በሐሳብ አንዱን ጥላ አንዱን ስታነሣ ቆየች፡፡

"ትርሲተ ማርያም፣ እስቲ እንደዚያ ያስጨነቀሽን ነገር ከመጀመሪያው ጀምረሽ ንገሪኝ፡፡ ምንድነው የገጠመሽ?" አሉ የኔታ ወልደ ዮሐንስ የእመቤት ዝምታ ግራ አጋብቷቸው፡፡ ጠዋት በስልክ እንደምትፈልጋቸው እያለቀሰች ስትነግራቸው የጉዳዩ አሳሳቢነት አስጨንቋቸው ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ጣቶችዋን እያፍተለተለች አቀርቅራ ሲመለከቷት መናገር እስክትጀምር በትዕግሥት ለመጠበቅ ወሰኑ፡፡

እመቤት ካቀረቀረችበት ቀና ብላ የኔታ ወልደ ዮሐንስን ተመለከተች፡፡ "እንዴት እንደምነግርዎ ተቸግሬ ነው" አለች፡፡

"ግድ የለሽም ልጄ አባትሽ ነኝ፡፡ ከእኔ የምትደብቂው ነገር አይኖርሽም፡፡ ብትደብቂ ደግሞ ኃጢአት ነው፤ ስለዚህ ንገሪኝ" አሉ የኔታ ወልደ ዮሐንስ ትኩር ብለው እየተመለከቷት፡፡

ትርሲተ ማርያም ጥቂት ስታሰላስል ቆይታ "ወላጆቼ ከተለያዩ ብሔረ ሰቦች የተገኙ ናቸው፡፡ በፍቅር ኖረው ከእነርሱ የተገኘነውን ሦስት ልጆቻቸውን በፍቅር አሳድገው፣ በሃይማኖታቸው ጸንተው፣ እኛንም በሰንበት ትምህርት ቤት እንድንማር፣ ከመንፈሳዊው ማዕድ እንድናቋደስ፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጣዕም እንድንቀምስ ያደረጉና ለወግ ለማዕረግ ያበቁ ናቸው፡፡ አንድም ቀን ብሔራቸው በመካከላቸው እንቅፋት ሆኖ አያውቅም፡፡ የሁለቱንም ቤተሰቦች እኩል

ዐውቀን፣ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሁለቱም አያቶቻችን ዘንድ እየሔድን ምርቃት ተቀብለን ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡

እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ እኔም ቤተሰብ የመመሥረት ዕድሉ ገጥሞኛልና ምኞቴ ሁሉ ወላጆቼ ባለፉበት መንገድ በማለፍ በፍቅር መኖር ነበር፡፡ ምኞቴ ግን በአጭሩ ተጨናገፈ- አባቴ!" በማለት ስቅስቅ ብላ አለቀሰች፡፡

የኔታ ውልደ ዮሐንስ በዝምታ እያደመጧት ነበር፡፡ ለማባበል አልሞከሩም፡፡ 'ትንሽ አልቅሳ ይውጣላት' በሚል ዝምታን መረጡ፡፡

እመቤት ለተወሰኑ ደቂቃዎች እያለቀሰች ከቆየች በኋላ ራሷን አረጋግታ ያስጨነቃትን ሁሉ ለመተንፈስ ተዘጋጀች፡፡ "ይቅርታ አባቴ! የደረሰብኝ ነገር ዕረፍት ነስቶኝ ነው፡፡ እርስዎም እንደሚያውቁት ከባለቤቴ ጋር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወደንና ፈቅደን ከተጋባን ገና ስድስተኛ ወራችን ነው፡፡ ነገር ግን ገና ሳንጀምረው ልንለያይ ነው፡፡ በዚህ ላይ የሦስት ወር ፅንስ በሆዴ ቀርቷል፡፡ አባቴ ትዳሬን ያድኑልኝ!" ብላ እያለቀሰች ከየኔታ ወልደ ዮሐንስ እግር ሥር ተደፋች፡፡

የኔታ ከተቀመጡበት ተነሥተው እመቤትን ከተደፋችበት ለማንሣት ታገሉ፤ ግን አልቻሉም፡፡ "የኔ ልጅ ሁለታችሁም ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁኝ ልጆቼ ናችሁ፤ ችግራችሁ ችግሬ ነው፡፡ አቅሜ የፈቀደውን ሁሉ አደርጋለሁ፣ እግዚአብሔርም ይረዳናል፡፡ በዚህ አጭር ጊዜ ደግሞ ምን ተፈጠረ? ባለፈው ሳምንት ፍቅረ ማርያምን አግኝቼው ነበር ምንም የነገረኝ ነገር የለም፡፡ ምንድነው የተፈጠረው ትርሲተ ማርያም?!" አሉ ግራ በመጋባት፡፡

እመቤት ፈቃደኛ ስለሆኑላት ደስ ብሏት ከወደቀችበት ተነሣች፡፡ "ይቅርታ አባቴ፣ ስለጨነቀኝ ነው፡፡ ትዳሬን በፍጹም ማጣት አልፈልግም፡፡ ግን የብሔርና ቋንቋ ጉዳይ ትዳሬን ሊያፈርስብኝ ነው፡፡ እኔና ብርሃኑ የተገናኘነው ገና በለጋነታችን በትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ በወቅቱ ለመንፈሳዊ ትምህርት ብዙም የቀረበ ስላልነበር በሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሳተፍ፣ በተሰጠው ጸጋ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ገፋፍቼው ተሳክቶልኝ ነበር፡፡ ከልጅነት የተመሠረተው ትውውቃችን አድጎ በዩኒቨርሲቲም ቀጥሎ ሥራ ከያዝን በኋላ እግዚአብሔር ፈቅዶ እርስዎም እንደሚያውቁት ለትዳር በቃን፡፡ አሁን ግን ትዳሬ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡

ባለቤቴ ብርሃኑ በቅርቡ ጸባዩም፣ ቋንቋውም ተለውጧል፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚያናግረኝ ሁለታችን በምንግባባበት ቋንቋ አይደለም፡፡ እኔ ደግሞ እርሱ የሚናገረውን ቋንቋ አልችልም፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ በአማርኛ "ገና ምን አይተሽ እናጠፋችኋለን!" እያለ ይዝትብኛል፡፡ የራሱን ብሔር መርጦ አለማግባቱንና እኔንም በማግባቱ እንደተጸጸተ ይነግረኛል፡፡ ሰክሮ ገብቶ በውድቅት ሌሊት ከቤት እያባረረኝ ጎረቤት ለበርካታ ቀናት አድሬ አውቃለሁ፡፡ አንድም ቀን በመካከላችን ስለ ብሔራችን አንስተን የተነጋገርንበት ጊዜ አልነበረም፡፡ አሳስቦንም አያውቅም ነበር፤ አሁን ግን ምን አዲስ ነገር እንደ ተከሠተ ግራ አጋብቶኛል፡፡ መኝታ እንኳን ከለየን ሁለት ወራት ተቆጥረዋል፡፡"

የተከሠተውን ችግር ለቤተሰቦቼ ባማክራቸውም ትተሽው ነይ እኛ ለአንቺ መሆን አያቅተንም፡፡ ወይ እርሱን በይ ወይ እኛን በይ ብለው ርቀውኛል፡፡ እኔ ደግሞ የልጅነት ፍቅሬን ትቼ መሄድ አልፈለግሁም፡፡ በርካታ ዘመናት በፍቅር ቆይተናል፡፡ አሁን ወደ ብሔሩ አደላ ብዬ ልሸሸው አልፈልግም፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠኝ ስጦታዬን፣ በእግዚአብሔርና በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በካህኑ ፊት የገባሁትን ቃል አላጥፍም" አለች እመቤት መፍትሔ በመሻት የኔታ ወልደ ዮሐንስን እየተመለከተች፡፡

የኔታ በሰሙት ነገር በጣም ተገርመዋል፣ አዝነዋልም፡፡

"ልጄ ጊዜ ያመጣው ጣጣ ነው፡፡ እግዚአብሔር ተቆጥቶናል፤ ለዘመናት በአባቶቻችን ተጋድሎ፣ በቅዱሳን ጸሎት ተጠብቃ የኖረችን ሀገር ለማፍረስ ዲያብሎስ ጦሩን ሰብቆ፣ ጎራዴውን ስሎ መጥቷል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ግድ ከሆነ ምን እናደርጋለን? የቻለ እግዚአብሔር ቁጣውን በምሕረት እንዲመልስልን እንደ ነነዌ ሰዎች መጾም፣ መጸለይ ነው፡፡ ዛሬ ሀገራችን ታማለች፣ ሁሉም ዘር ቆጣሪ ሆኗል፣ አንድ አድርጋ አስተባብራ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስትሰብክ

የኖረችውን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የማይቆፍሩት ጉድጓድ፣ የማይፈጥሩት አዲስ ታሪክ የለም፡፡ የአንድ እግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን፣ መኖሪያችን በሰማይ መሆኑ ተዘንግቷል፡፡ ለመሆኑ ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ጠይቀሽው ታውቂያለሽ?" አሉ ውስጣቸው እያዘነ፡፡

"ምንም የሚመልሰው መልስ የለውም፡፡ ስጠይቀው ለመማታትና እኔን ለመርገም ይፈጥናል፣ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጸያፍ ስድብ ይሳደባል፣ ይባስ ብሎ ትናንት አምሽቶ መጥቶ 'መፋታት እፈልጋለሁ' አለኝ፡፡ ሐሳቡን ይቀይር ይሆናል፣ አንድ አድርጎም ያስተሳስረናል ብዬ እርጉዝ እንደሆንኩ ነገርኩት፡፡ ነገር ግን የተረፈኝ ዱላ ነው፡፡ 'አልፈልገውም አስወጪው' አለኝ፡፡ አባ እኔ በጣም ተጨንቄያለሁ፡፡ ምን ላድርግ?" አለች በሁለቱም ጉንጮችዋ የማያቋርጥ የዕንባ ጎርፍ እየጎረፈ፡፡

የኔታ ወልደ ዮሐንስ በሚሰሙት ታሪክ እንዳዘኑ መፍትሔ ፍለጋ አቀረቀሩ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ካቀረቀሩበት ቀና ብለው "ፍቅረ ማርያምን ወደ እኔ ይዘሽው መምጣት ትችያለሽ?" አሉ በጥርጣሬ፡፡

"አባቴ አልችልም፡፡ በተደጋጋሚ ለምኜዋለሁ፡፡ እንኳን እርስዎ ዘንድ ለመምጣት ቤተ ክርስቲያንም ላለመሔድ ወስኗል፡፡"

**"ልጄ ይህ እኔ ላይ ለምን ሆነ ብለሽ እግዚአብሔርን እንዳታማርሪ፤ ከአንቺ የሚጠበቀው በሃይማኖት ጸንቶ እግዚአብሔርን በጸሎት መለመን ብቻ ነው፡፡ ከክፉ ራቂ፣ ክፉን በክፉ አትመልሺ፡፡ አሁን ያለንበትን ዘመን መሻገር የምንችለው በጾም በጸሎት፣ መልካም ነገርን በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ሀገራችን በዘር፣ በሃይማኖት ተከፋፍላ ሁሉም እኔ እኔ የሚልበት ወቅት ነው፡፡ ነገር ግን ዘላቂነትም የለውምና አትረበሺ፡፡ ነገ በሌሊት ከቤት ከመውጣቱ በፊት እቤታችሁ እደርሳለሁ፣ ራስሽን ጠብቂ ልጄ"**

"ልጄ ይህ እኔ ላይ ለምን ሆነ ብለሽ እግዚአብሔርን እንዳታማርሪ፤ ከአንቺ የሚጠበቀው በሃይማኖት ጸንቶ እግዚአብሔርን በጸሎት መለመን ብቻ ነው፡፡ ከክፉ ራቂ፣ ክፉን በክፉ አትመልሺ፡፡ አሁን ያለንበትን ዘመን መሻገር የምንችለው በጾም በጸሎት፣ መልካም ነገርን በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ሀገራችን በዘር፣ በሃይማኖት ተከፋፍላ ሁሉም እኔ እኔ የሚልበት ወቅት ነው፡፡ ነገር ግን ዘላቂነትም የለውምና አትረበሺ፡፡ ነገ በሌሊት ከቤት ከመውጣቱ በፊት እቤታችሁ እደርሳለሁ፣ ራስሽን ጠብቂ ልጄ" አሉ እመቤትን እያጽናኑ፡፡

"አባቴ ይህንን ጊዜ በጽናት አልፌው ዘንድ ጸልዩልኝ፡፡ እኔ ፈርቻለሁ፤ ወይ ከትዳሬ አልሆንኩ ወይ ከቤተሰቦቼ አልሆንኩ ተጨንቄ ነው" አለች በውስጧ ፍርሃት እንደ ነገሠ፡፡

"አይዞሽ እግዚአብሔር ይረዳናል" ብለው ጸሎት ጸልየው አሰናበቷት፡፡

❖

የኔታ ወልደ ዮሐንስ ከሌሊት ጀምሮ ከካህናቱ ጋር ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ ቆይተው ኪዳን እንደተጠናቀቀ አራት ኪሎ ወደሚገኘው ብርሃኑና እመቤት ቤት አመሩ፡፡

እንደደረሱም "እንደ ምን አደራችሁ ቤቶች?" አሉ የኔታ ወልደ ዮሐንስ፡፡

እመቤት ቀድማ ተነሥታ ሳሎን ውስጥ ሆና ትጠባበቅ ስለነበር "እግዚአብሔር ይመስገን፤ ይግቡ" አለች የሳሎኑን በር እየከፈተች፡፡

"ደኅና አደራችሁ ልጆች? በሌሊት መጥቼ ቀሰቀስኳችሁ?" አሉ ወደ ሳሎን ገብተው እመቤትን መስቀል እያሳለሙ፡፡

"አይ አባቴ ከተነሣሁ ቆይቻለሁ፡፡ ዐረፍ ይበሉ" አለች ሶፋውን እንደማስተካከል ብላ እንዲቀመጡ እያመለከተቻቸው፡፡

"ትርሲተ ማርያም አልቀመጥም፡፡ እስቲ በጣሳ ውኃ አምጪ ጸሎት ላድርስ፡፡ ፍቅረ ማርያም አልተነሣም እንዴ? ቀስቅሺው እንጂ፡፡"

“እሺ” ብላ ወደ መኝታ ቤት ልትገባ ስትል ብርሃኑ ከነ ሌሊት ልብሱ ዓይኑን እያሸ ብቅ አለ፡፡

“እንዴት አደርክ ልጄ?” ብለው ሊያሳልሙት መስቀላቸውን ወደ ግንባሩ ሲያስጠጉ ብርሃኑ ለመከላከል ሞከረ፡፡

“ምነው ልጄ? መስቀል አትሳለምም እንዴ?” አሉ መስቀላቸውን እየመለሱ፡፡

“አይ ዝም ብዬ ነው፡፡” ብርሃኑ አመነታ፡፡

“ምን ማለትህ ነው? ከመቼ ወዲህ ነው መስቀሉን መሸሽ የጀመርከው? በመስቀሉ አምላካችን ስለ ሰው ልጆች የከፈለውን ዋጋ ምነው ዘነጋህ? በል ና ተሳለም” አሉት ትእዛዝ ባዘለ ድምፀት፡፡

ብርሃኑ እያመነታም ቢሆን መስቀሉን ተሳለመ፡፡

እመቤት በጣሳ ውኃ አቀረበች፡፡

የኔታ ወልደ ዮሐንስ ብርሃኑን ካሳለሙ በኋላ ጸሎታቸውን ቀጠሉ፡፡

ብርሃኑና እመቤት የኔታ ወልደ ዮሐንስን ተከትለው ለጸሎት ቆሙ፡፡ ብርሃኑ በስርቆሽ እመቤት ላይ ከንፈሩን በጥርሱ እየነከሰ “እሠራልሻለሁ!” የሚል ዛቻ በምልክት እያሳያት ለማስፈራራት ሲሞክር ቆየ፡፡

የኔታ ጸሎታቸውን አጠናቅቀው ሁለቱንም ጸበል ከረጩ በኋላ ቤቱንና ደጁን ሁሉ ረጭተው ተመለሱ፡፡

“በሉ ኑ እስቲ ዐረፍ እንበልና ጥቂት ቃለ እግዚአብሔር እንማማር” ብለው ሁለቱንም እንዲቀመጡ ጋብዘው ከመጽሐፍ ቅዱስ “መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን”(ዕብ.፲፫፥፬) በሚል ቃል ማስተማራቸውን ቀጠሉ፡፡ በትምህርታቸውም ባልና ሚስት በፍቅር ሊኖሩ እንደሚገባቸው፣ከእግዚአብሔር ፍቅር እንዳይወጡ በጊዜያዊ ስሜትና ፍላጎት እግዚአብሔርን እንዳያሳዝኑ፣ ከዘመኑ ብሔር አቀንቃኞችና ጦርነት ናፋቂዎች እንዲጠበቁ ምክር አዘል ትምህርታቸውን አስተላለፉ፡፡

ከትምህርቱ በኋላ የኔታ ወልደ ዮሐንስ ቁጭ ብለው “እሺ ትዳር እንዴት ነው?” ብለው ሁለቱንም ጠየቁ፡፡ እመቤት ዝምታን ስትመርጥ ብርሃኑ ከአንገቱ አቀረቀረ፡፡

“ተናገሩ እንጂ!” አሉ ወደ ብርሃኑ እየተመለከቱ፡፡

“ጥሩ ነው” አለ ብርሃኑ እንዳቀረቀረ፡፡

“ጥሩ ነው ብቻ ማለት በቂ ነው?” አሉት በእርጋታ እየተመለከቱት፡፡

“አይ አባቴ አሁንም የቀየሁት እርስዎን በማክበር ነው እንጂ በትዳሬ ደስተኛ አይደለሁም፡፡ መፋታት እፈልጋለሁ” አለ ካቀረቀረበት ቀና እያለ፡፡

“ምን ማለት ነው፡፡ ትዳር ዝም ብለው የሚያፈርሱት የመንገድ አጥር ነው እንዴ ልጄ? የመንገድ አጥርም እኮ ባለቤት አለው፤ ያለ ምክንያትም አይፈርስም፡፡ ለመሆኑ ምክንያትህ ምንድነው? ትርሲተ ማርያም አስቀይማሃለች እንዴ?”

“አይ፡፡ በቃ እኔ ዘሬን ነው ማግባት የምፈልገው፡፡ ተሳስቼ ነበር፡፡”

“ዘር ስትል ምን ማለት ነው?”

“በቃ ከብሔሬ ነው ማግባት የምፈልገው፡፡”

“ክርስቲያን ብሔሩ ወዴት ነው? ዘሩስ ከወዴት ነው? ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፣ በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ” ይላል የእግዚአብሔር ቃል በሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ላይ አድሮ፡፡ (፩ኛ ጴጥ.፩፥፳፫)፡፡ እኛ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ነን፡፡ “እኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆን ለልቡናችን ምስክሩ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን ወራሾቹ ነን” የሚልም ቃል በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች መልእክት ላይ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ (ሮሜ.፰፥፲፮)፡፡ ስለዚህ ከሰማያዊ አባቱ ሸሽቶ ምድራዊው ብልጭልጩን ዓለም ሽቶ ወዴት ሊሄድ ይገባዋል? የአባቱ ርስት ተካፋይ ይሆናል እንጂ

አይኮበልልም:: ተጠንቀቅ ልጄ:: ዘመኑ ባነፈሰው ንፋስ አትወሰድ፣ ቆም ብለህ አስብ:: ወደ ጥፋት ጎዳና እያመራህ እንደሆነ አስብ:: የዘመኑ ፖለቲከኞች በሚነዙት ወሬና አሉባልታ ተሸብረህ ከአባትህ ቤት፣ እስከ ሞትም ድረስ ከታመነ አምላክ ፊት አትኮብልል:: መጨረሻው ጥፋት ነው:: ሉቃስ ፲፭ ላይ ከአባቱ ቤት እንደ ኮበበለው ልጅ የእሪያዎች ጠባቂና የእነርሱንም ትርፍራፊ የምትለቃቅም አትሁን:: እግዚአብሔር መርጦ ከሰጠህ ትዳርህ አትኮብልል::

ዘር፣ ብሔር የምትለው ነገር አያዛልቅህም:: በባዶ ትርክት ትዳርህን በትነህ በነፍስም እንዳትጠየቅ አሁንም ቆም ብለህ አስብ:: ሀገርን ለመበተን ልትተባበር ትችል ይሆናል፣ ዛሬ አይዞህ የሚሉህ ሁሉ ገንዘብ ሊሰጡህ ይችሉ ይሆናል፣ ንብረት ሊያካፍሉህ፣ ሥልጣን ሊሰጡህ ይችሉ ይሆናል:: እንዳንተው እግዚአብሔር በአምሳሉና በአርአያው የፈጠረውን የሰው ልጅ ልታጠፋ ትሮጥ ይሆናል፤ እግዚአብሔር ስላጠፋኸው ነፍስ ከእጅህ ይቀበላል፣ እግዚአብሔር መልሶ አንተን እንደሚያፈርስህ ዕወቅ:: የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና ልተፋህ ነው እንዳይልህ እግዚአብሔር በሰከነ መንፈስ ራስህን ጠይቅ፣ ጎዳናው ወዴት እንደሚወስድ ሳታውቅ እርምጃ አትጀምር:: ተጠንቀቅ!" አሉ የኔታ ወልደ ዮሐንስ በስሜት ተውጠው::

ሳሎኑ በዝምታ ማዕበል ተመታ:: ዝምታ ሰፈነ፣ ሁለቱም የትዳር አጋሮች ካቀረቀሩበት ቀና ማለት ተሳናቸው:: እመቤት እግዚአብሔርን እየተማጸነች ዕንባዋን ታጎርፈዋለች፤ ብርሃኑ አንደበቱ ተለጉሞ መልስ ፍለጋ ቢሸከረከርም ጠብ የሚል ነገር በማጣቱ ዝምታን መረጠ::

"ትርሲተ ማርያም እስቲ ንገሪኝ፣ ምንድነው የተፈጠረው?" አሉ ከብርሃኑ መልስ በማጣታቸው::

እመቤት እያነባች "አባቴ እኔ ትዳሬን ከማክበር፣ እንደ አቅሜም እግዚአብሔርን በመፍራት በታማኝነት ከመኖር ውጪ ምንም አላውቅም:: ባለቤቴን ከልጅነት ጀምሮ ስወደው ኖሬያለሁ፣ ሳስብለትና ስጨነቅለት፣ ሳፈቅረውም ኖሬያለሁ፤ አሁንም እወደዋለሁ:: ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግን ዓይንሽን ለአፈር ብሎኛልና ትዳሬን እንዲታደጉልኝ ነው የምፈልገው" አለች በነጠላዋ ጫፍ ዕንባዋን እየጠረገች::

"በል እስቲ ፍቅረ ማርያም ምንም ሳትደብቅ ንገረኝ:: ዘር፣ ብሔር ስትል ምን ማለትህ ነው? ከእግዚአብሔር ይበልጥብሃልን? ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች አይደለንም እንዴ? እስቲ መልስህን ልስማው?" አሉ የኔታ ወልደ ዮሐንስ::

ሲያመነታ ቆይቶ "የምትሉት እውነት እንደሆነ አውቃለሁ:: እስከ ዛሬም ይህንን አምኜ ነው የኖርኩት:: አሁን ግን በየሚዲያው የምሰማው፣ የቤተሰቦቼና የጓደኞቼ ግፊት ያለፈውን ሕይወቴን እንድጠላ፣ አዲስም ሰው እንድሆን ውስጤ ገፋፋኝ:: እውነቱ የቀደመው እንደሆነ ብረዳም አሁን በዘመኑ ላለው አስተሳሰብ ተሸነፍኩ:: እኔ ባለቤቴን ጠልቻት አይደለም ግን አዳዲስ ትርክቶችን በሰማሁ ቁጥር ውስጤን ፍቺ እንድፈጽም እየገፋፋኝ ያደረግሁት ነው" አለ ብርሃኑ ጸጉሩን አሥር ጊዜ እያሸ::

"እንግዲያውስ እውነቱን ተጋፈጥ ልጄ:: ለምን እንዲህ አደረግህ ብዬ ለሌላ ጥፋት እልህ ውስጥ እንድከትህ አልፈልግም:: ወደ ራስህ ተመለስ:: ይህ ጊዜ የወለደው ትርክትና ፉከራ አንድ ቀን ያበቃል፣ ዛሬ ያፈረስከው ትዳርህን፣ የካድከው የአብራክህ ክፋይን ግን ታጣለህ:: ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን ታጣለህ:: ስለዚህ ወደ ትዳርህ ወደ እግዚአብሔርም ተመለስ:: ዘር የሚያስፈልገው ገበሬው ነገ ለሚያመርተው ምርት ነው:: ሳይገባህ ያለ ሥራህ ዘር ቆጣሪ አትሁን:: በኋላ ታዝናህ:: በል እኅትህን፣ የትዳር አጋርህን አሳዝነሃታልና ይቅርታ ጠይቃት::" አሉት በአባትነት ተግሣጽ::

ብርሃኑ ከዚህ በላይ መጓዝ አልቻለም:: በእመቤት እግር ሥር ይቅርታን ፍለጋ ወደቀ:: ሁለቱም ተቃቅፈው ተላቀሱ:: የኔታ ወልደ ዮሐንስ በቀላሉ ስለተመለሰላቸው ልቡን ከፍቶ እንዲራራና ወደ ቀደመ ማንነቱ እንዲመለስ ያደረገውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: ሁለቱንም አስታርቀውና ቀኖና ሰጥተው ወደ በኣታ ለማርያም ገዳም ተመለሱ:: ✞ ✞ ✞

# አሐቲ ቤተ ክርስቲያን

## የነገዋ ቤተ ክርስቲያን

### ክፍል አንድ

*ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ እንደሰበከው*

***ውድ አንባብያን በዚህ ዓምድ ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ነገ ምን መሆን እንዳለባት የሚያሳይ፣ ለሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባል ቤተ ክርስቲያን ልትደርስበት የሚገባትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ልማታዊ አቅጣጫዎችን ማሳየት፣ ትውልዱም የድርሻውን እንዲወጣ ማመላከት ነው:: በመሆኑም አስቀድመን ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? የሚለውን መሠረታውዊ ዕውቀት መረዳት ይቻል ዘንድ ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ የሰበከውን በተከታታይ አቅርበንላችኋል መልካም ንባብ::***

እንደ እግዚአብሔር ቸርነት በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው "አሐቲ ቤተ ክርስቲያን፤ አንዲት ቤተ ክርስቲያን፤" የሚል ይሆናል::

በዘወትር ጸሎታችን አንድ አማኝ በየዕለቱ ምስክርነት የሚሰጥባቸው እምነቶች አሉት:: ማንኛውም ክርስቲያን በቀኖናችንና በታዘዘው መሠረት ጸሎት የሚጸልይ ከሆነ ጸሎተ ሃይማኖት (የሃይማኖት ጸሎት) የምንለውን ጸሎት ሳይጸልይ ሊውል አይችልም:: ሌሎች ጸሎቶች እንኳን ከደረሱ በኂላ መጨረሻ የሚጸለየው ጸሎተ ሃይማኖት ነው:: ይህ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ትእዛዝ ነው:: ይህ የሆነበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው ስንል ጸሎተ ሃይማኖት እንዳለ ተአምኖ ሃይማኖት ስለ ኾነ ነው:: የምናምነውን እምነት የምንመሰክርበት ክፍል ነውና፤ "ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ፤" የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን:: ከዚያ በኂላ ደግሞ "ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ. . ." እያልን እንቀጥላለን:: "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ . . ." እንላለን:: "ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት፤" በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን::

እነዚህም አሥራ ሁለት አንቀጾች ናቸው፤ እናምናለን፥ እናምናለን፥ እናምናለን እያልን አሥራ ሁለቱን እንገልጻለን:: በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ደግሞ በሰፊው በተለይ በሐዋርያት አመክንዮ ብዙዎቹን የምናምናቸውን ነገሮች እየዘረዘርን እናምናለን፥ እያልን የምናምነውን እየገለጽን በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር እንገናኛለን፤ አንድ እንሆናለን፤ እንተሳሰራለን:: በዚህ መንገድ ከምንገልጻቸው ዐበይት ነገሮች አንዱ "ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት፤" ሐዋርያት በሰበሰቧት፣ ከሁሉም በላይ በሆነች (በምትበልጠው)፣ በአንዲት፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን:: እንላለን:: በአንዲት ቤተ ክርስቲያን የማመን ጉዳይ በአንድ አብ እንደምናምነው፣ በአንድ ወልድም እንደምናምነው፣ በአንድ መንፈስ ቅዱስ፣ በሦስት አካላት፣ በሦስት ስም፣ በሦስት ግብር፣ በአንድ ባሕርይ፣ በአንድ አገዛዝ፣ በአንድ መለኮት፣ በአንድ አምላክ፣ እንደምናምነው ነው:: እግዚአብሔር ወልድ በደሙ በመሠረታት ከሁሉም በላይ በምትሆን በአንዲት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን:: ይህን ምስክርነት እየሰጠን ሁል ጊዜ እንጸልየዋለን:: ቢያንስ በጋራ ጸሎት ጊዜ፣ በቅዳሴውም ጊዜ፣ በሌላኛውም ጊዜ፣ እንጸልየዋለን::

በአብ ማመን በወልድ ማመን፣ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ምን ማለት እንደሆነ እናውቅ ይሆናል:: ወይም በተሻለ መጠን ተምረን ይሆናል:: ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በተለይ ከኢትዮጵያ ውጭ ስንወጣ በጣም የምንቸገርበት መሠረታዊ ችግር ይህ እምነት ምን እንደሆነ አለማወቅ ነው:: ይህን ካለማወቅ የተነሣ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች የፖለቲካ ልዩነትም ኾነ ሌላም ጸብ ሲኖራቸው፣ የተለያየ ልዩነት ሲያጋጥማቸው፣ በቤተ ክርስቲያንም ይለያያሉ:: እንደሚታወቀው በውጭ ሀገር ሁለት ቄስ የግድ አያስፈልግም፤ አንድ ቄስና አንድ ዲያቆን ካሉ የፈለጉ ምእመናን ተሰባስበው አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይከፍታሉ:: እነዚህን ችግሮች ስናያቸው አሁን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ፈተና ላይ ነች:: ይህ ፈተና ከምን የመነጨ ነው? የሚለውን ስናነሣው በእኔ ግምትና መረዳት መሠረታዊ ችግሩ ቤተ ክርስቲያን የምንላትን አካል በደንብ አለማወቅ ይመስላል:: ርእሳችን አንዲት ቤተ ክርስቲያን

ስለሆነ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ይቺ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፤ ኩላዊት ናት፤ የሁሉም ናት፤ ከሁሉም በላይ ናት፤ ሐዋርያዊት ናት፤ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ነው የምናምነው። "እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት፤" ብለን የገለጽነው እሱን ነው። ከዚህ በመነሣት ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን።

## ፩. የቤተ ክርስቲያን ምንነት

በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው? እንደምታውቁት ኦርቶዶክስ ያልሆኑ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች አሉ። እነርሱ ቤተ ክርስቲያን ሲሉና እኛ ቤተ ክርስቲያን ስንል ልዩነት አለው? ወይስ የለውም? መሠረታዊ ልዩነት ነው ያለው። በተለይ በምዕራቡ ዓለም ክርስቲያኖችና በምሥራቁ ዓለም ክርስቲኖች መካከል ካሉት መሠረታዊ ልዩነቶች አንዱና ዋናው ይህ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምንላትን አካል በማወቅ ረገድ ለምሳሌ የፕሮቴስታንቱ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የሚለው አንድ ጉባኤ ላይ አንድ አዳራሽ ውስጥ ሊሆን ይችላል፤ የተሰባሰቡትን የሰዎች አንድነት ኅብረት ድምር ነው። በኦርቶዶክስ ግን ቤተ ክርስቲያን የምትባለው እንደዚህ አይደለም፤ ያለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንልምና። ክርስቶስ ራስ የሆነላት፣ ተጋድሏቸውን ፈጽመው አሁን በአጸደ ነፍሳት ያሉ ቅዱሳንና በምድር ያለን የኛ የምእመናን አንድነት ነው ቤተ ክርስቲያን የሚባለው። እዚህ ያለነው ስብስብ ብቻ ማለት አይደለም። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየትም ቦታ ያሉ፣ ርትዕት በሆነች ሃይማኖት አምነው የሚጓዙ፣ ተጋድሏቸውን ያልፈጸሙ ምእመናንና ተጋድሏቸውን ፈጽመው፣ በአጸደ ነፍስ በገነት ያሉ ቅዱሳን አንድነት ናት። ሁለቱ አይለያዩም፤ በአጸደ ነፍስ ያሉትም ከኛ ጋር አንድነት አላቸው። እኛም ከእነሱ ጋር አንድነት አለን። ይህን ሐሳብ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች በተለይ በደንብ መረዳት አለባቸው።

ከፕሮቴስታንቱ ዓለም ጋር አንዱ ልዩነታችን ቅዱሳን ያማልዳሉ፥ አያማልዱም የሚለው ነጥብ ነው። እውነት ለመናገር ለእነርሱ በአጸደ ነፍስ ያሉት፣ በሌላ ዓለም ያሉ፣ ሌሎች አካላት ተደርገው ነው የሚታሰቡት። ለኛ ግን ሌሎች አይደሉም፤ እነርሱም የክርስቶስ አካላት ናቸው። እኛም የክርስቶስ አካላት ነን። ክርስቶስ ደግሞ ስንት አካላት ነው ያለው? አንድ አካል ነው፤ እርሱ አንድ እውነተኛ የወይን ግንድ ነው። እኛ ደግሞ ቅርንጫፎቹ ነን፤ እናም ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፤ ሁለት አይደለችም። በገነት ያለችው ሌላ፣ በሰማይ ያለችው ሌላ፣ በምድር ያለችው ሌላ አይባልም። ቤተ ክርስቲያን የምትባለው የእነዚህና የሁላችን አንድነት ናት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌ.፪፥፳-፳፪ ላይ "በሐዋርያት እና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።" ይላል። በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ ያለው ከነማን ጋር ነው? ብለን ስንጠይቅ፥ መልሱ 'ተጋድሏቸውን ከፈጸሙ ቅዱሳን ጋር' የሚል ነው። የማዕዘኑም ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የተመሠረትነው በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ነው። ቤተ ክርስቲያን የእነዚህ ሁሉ አንድነት ናት። እኛ አሁን በመንፈስ እንሠራለን፤ ተጋድሏችንን ፈጽመንም ወደ እነርሱ ሄደንም (በአጸደ ነፍስ) መቀላቀል እንሻለን፤ እንፈልጋለን። የጉዞው ዓላማም ይህ ነው፤ ስንጾም፣ ስንዘምር፣ ስናመሰግን፣ ስንጸልይ በመንፈስ ነው አብረን የምንሠራው።

ይህን አንድነት የሚያስረዱ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፭ ቁጥር ፩ እስከ ፰ እሱ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ተካዩም አባቴ ነው፥ እናንተ ደግሞ ቅርንጫፎች ናችሁ።" እኛ በዚህ የወይን ግንድ ላይ ያለን ቅርንጫፎች ነን። በሰማይ ያሉ ቅርንጫፎች አሉ፤ በምድር ያሉ ቅርንጫፎች አለን። የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ይህን በደንብ አድርጎ አብራርቶ ተናግሯል። ከተናገረው ለማሳያ ብናነሣ "እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ አዕጹቂሃ፤" እያለ የዘመረው አለ። ምሳሌው የቤተ ክርስቲያን ነው፤ ግንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "እንተ በምድር ሥረዊሃ፤" ሥሮቿ በምድር ያሉ፤ "ወበሰማይ አዕጹቂሃ፤" ቅርንጫፎቿ ደግሞ በሰማይ ያሉ፤ አንድ የወይን ሐረግ ቤተ ክርስቲያን ናት እንላለን። ለእመቤታችንም መስለው የዜማ መምህራን ይዘምሩታል። እመቤታችንም የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት፤ ግንዱ አንድ ነው፤ ያ የወይን ግንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ያለ ቅርንጫፍ አለ፤ በምድር ያለን ሥር ተብለን የተገለጽን ቅርንጫፎች ወይም ሥሮች አለን። መሠረታዊው ሐሳብ ይህ ነው፤ ይህን የሚያረጋግጥ በእኛ

አገልግሎት ውስጥ ብዙ ምንባባትና ምስክሮች አሉ፤ ብዙ ተአምራትም አሉ፤ እሱን እንገልጻለን፡፡

## ፪. የቤተ ክርስቲያን ባሕርያት

የቤተ ክርስቲያን ትርጉሙ የእኛ እና የሰማይ ቅዱሳን አንድነት ከሆነ የቤተ ክርስቲያን ፬ ባሕርያት አሉ፡፡ ፩ኛ. ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፤ ፪ኛ. ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ናት፤ ፫ኛ. ቤተ ክርስቲያን ኵላዊት ናት፤ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ናት፤ ፬ኛ. ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት ነች፡፡ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን የሚያምን ሰው እነዚህን አራቱን ባሕርያት አስተካክሎ ማወቅና ማመን አለበት፡፡ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚፈጠሩ ውዝግቦች መልስ የሚያገኙት አራቱን ባሕርያት ስንረዳ ነው፡፡ በቀጣይ እነዚህን ነጥብ በነጥብ እናያለን፡፡

፩ኛ. ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፡- በመጀመሪያ በኤፌሶን ምዕራፍ ፬ ቁጥር ፬ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚለውን ነጥብ ነው የምናየው፡፡ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፤ የሚለውን ኤፌሶን ፬፥፬ ላይ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት ይላል፡፡ በአንድ እምነት ያለ ጉባኤ ስንት ቤተ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል? ቅዱስ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን አንዲት እንደሆነች ያስረዳል፡፡

በዚህ ረገድ ከሌሎቹ ጋር አሁንም መሠረታዊ ልዩነት አለን፡፡ በሌሎችና በእኛ መካከል ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚባለው ምን ስትሆን ነው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ላይ ልዩነት አለ፡፡ ለምሳሌ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የምትለው በሮማው ጳጳስ ሥር ስትኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን አንድነት አስተዳደራዊ (ADMINISTARTIONAL) ይሆናል፡፡ በዚያ ሥር የሌለ አይቆጠርም ማለት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንም ራስ፥ የሁሉ የበላይ ፖፑ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በኦርቶዶክስ አስተምህሮ የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደዚህ አይደለም፡፡ ራሳቸውን የቻሉ የግብጽ፣ የአርመን፣ የሶሪያ፣ የሕንድ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ ልክ እንደዚህ በእውነተኛይቱ አንዲት ሃይማኖት ያሉ አስተዳደራቸው ግን የተለየ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ሲኖዶስ አላቸው፤ የራሳቸው ጳጳሳትና ፓትርያርክ አላቸው፤ የየራሳቸው አገልግሎት አላቸው፡፡ አስተዳደሩ ፭ ወይም ፯፤ ፰ም ቢሆን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚገልጸው አንድ አስተዳደር ወይም ዓለም ሁሉ በአንድ ፖፕ ወይም በአንድ ፓትርያርክ መተዳደር አይደለም፡፡ ከተቻለ የአስተዳደር አንድነት መልካም ነው፤ ለምሳሌ ዓለም ሁሉ ኦርቶዶክስ ሆኖ በአንድ ፓትርያርክ ቢመራ ችግር ነው ማለት አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርጋት ግን አስተዳደር ሊኾን አይችልም፡፡

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታትና አንድ የሚያደርጋት ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ እንዴት አድርጎ አንድ ያደርገናል? ለምሳሌ ከላይ የጠቀስናቸው አኀት አብያተ ክርስቲያናት እንዴት ነው አንድ የሚኾኑት? ሁላችንም አንዲት እምነት አምነን፣ አንዲት ጥምቀት ተጠምቀን፣ ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል፣ ክርስቶስ በእኛ ሲያድር እኛ ሁላችን የክርስቶስ አካል እንሆናለን፡፡ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ራስ የኾነ የክርስቶስ አካላት ይኾናሉ፡፡ ሁሉም የወይን ግንዱ የክርስቶስ ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ የሚያደርገን ትልቁ ምስጢር ሥጋ ወደሙ ነው፡፡ በአንዲት ሃይማኖት፣ በአንዲት ጥምቀት፣ በአንድ ሥርዓት ተፈጽሞ፣ አንድ ሥጋ ወደሙ ስንቀበል አንዲት አካልነታችን ይረጋገጣል፡፡ ክርስቲያኖች የትም ምድር ቢኖሩ አንድ የሚያደርጋቸው ወይም ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርጋት የወይኑ ግንድ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡ ክርስቲያኖች ቅርንጫፍ የምንሆነው እኛ የእሱን ሥጋና ደም ስንበላና ስንጠጣ እርሱ በእኛ ሲያድር እኛም በእርሱ ስንሆን በአንዱ ክርስቶስ ሁላችንም አንድ ግንድ ላይ የተተከልን ቅርንጫፎች ስንኾን አንድ እንኾናለን፡፡

የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፲፭-፲፯ ላይ እንዲህ ይላል፡፡ መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ፡፡ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡ ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፤ ድምጼንም ይሰማሉ፡፡ አንድም መንጋ ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ፤ ይላል፡፡ እረኛው አንድ፤ መንጋውም አንድ፤ ሁለት መንጋ የለም፡፡ ሌሎች በረቶች ውስጥ በጎች አሉ፤ ሌሎች ቤተ እምነቶች ውስጥ አሉ፡፡ የዋሃን ሰዎች በቅን ሕሊና፥ በንጹሕ ልቡና ሁሉም ትክክለኛ መንገድ መስሎዋቸው እግዚአብሔርን ከልብ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ "እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው፤" እንደተባለው፤ እነዚያን ልቦች እግዚአብሔር ያገኛቸዋል፡፡ ባገኛቸውም ጊዜ 'እዛው በረት ውስጥ መሆን ትችላላችሁ አይደለም የሚላቸው፤' ወደ አንዲቷ በረት

ያመጣቸዋል እንጂ። ወደ አንድ እምነት፣ ወደ አንድ ጥምቀት፣ ወደ አንድ ሥጋ ወደሙ ያመጣቸውና አንድ ያደርጋቸዋል። ሁለት በረት የለም፤ ሁለት መንጋ የለም፤ ሁለትም እረኛ የለም፤ እረኛው አንድ፥ መንጋውም አንድ እንጂ። ይህ አንድነት ከላይ እንደተባለው ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ነው።

የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ሲፈጸሙ፥ በተለይ በቅዳሴ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን አንዲትነት ይበልጥ ግልጽ ይኾናል። ይህ ምን ማለት ነው? በጸሎተ ቅዳሴ የምንሳተፈው በአጸደ ሥጋ ያሉ ካህናት፣ ልዑካኑና አስቀዳሾቹ ብቻ አይደሉም። ቅዱሳን በሙሉ ይሳተፋሉ፤ ለማሳያ ያህልም አሐዱ ከመባሉ በፊት ካህኑ "አቤቱ ይህቺ መንፈስ ቅዱስ የሚወርድባት ዕለት ምነኛ የምታስፈራ ናት? በማለት ይጸልያል። አስቀድሞ ሥራውን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ መኾኑን መስክሮ ያስረክባል። ሥጋ ወደሙ ሲፈትት፣ ማንኛውንም ነገር ሲያደርግ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ አይደለም የሚያደርገው፤ አንተ አድርገው ነው የሚለው። "ኦ እግዚኦ በከመ አሜሃ ባርክ ወፈተተ ወሃብ፤" አቤቱ ጌታዬ ሆይ ያን ጊዜ በጸሎተ ሐሙስ ኅብስቱን፥ ወይኑን ለውጠህ ሥጋህን ደምህን እንዳደረክ ዛሬም ይህን ኅብስትና ወይን አንተ ሥጋህን ደምህን አድርገህ፥ አክብረህ ስጥ ነው፤ የሚለው። ካህናቱ ተሰይመው ሲያገለግሉ የሚለውጠው፥ የሚያከብረው ራሱ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ ስላለ የእርሱ የሆኑ ቅዱሳን በሙሉ ደግሞ አሉ።

በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በእስክንድርያ አባ ብንያም የሚባል ጻድቅ ፓትርያርክ ነበር። የአባ መቃርስ ገዳም አርጅቶ ስለ ነበር አደሳው ተፈጽሞ ቅዳሴ ቤቱን ሲፈጽም፥ መንበሩን ሲባርክ አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህን መንበር አንተ ባርክ፤ እያለ የሚጸልየውን ጸሎት ጸለየ። በዚህ ጊዜ የበቃ ስለ ነበረ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እጅ ሲያማትብ አየሁ፤" ይላል። በዓይነ ሥጋችን እንኳን ባናየው ሁሉን የሚፈጽመው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ፓትርያርክ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን እጅ ሲያየው ደንግጦ ወደቀ። ሲወድቅ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አነሣውና አይዞህ አትፍራ ብሎ አበረታው። ወደ ማዕዘኑ ዘወር ሲል ደግሞ አንድ ጺሙ ዥርግግ ያለ ያማረ ትልቅ አረጋዊ አየ። ልክ ይህን ሲያይ በተመስጦ ውስጥ ሳለ እንዲህ ብሎ አሰበ። በማስተዳድራት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍት ሀገረ ስብከት ቢኖረኝ ይህን ሰው ጳጳስ አድርጌ እሾመው ነበር። ግን ክፍት ሀገረ ስብከት የለኝ ምን አድርጌ ልሹመው? ይህን በሕሊናው ሲያስብ ይላል ታሪኩ ያ ከወደቀበት ያነሣው ቅዱስ ገብርኤል ይህንማ አንተ ልትሾመው አትችልም። እርሱ የፓትርያርኮች ሁሉ አባት አባ መቃርስ ነው፤ ዛሬ ቤተ መቅደሱን ስለምታከብር ስለምትባርክ፥ ጌታም እንዳየኸው በመንበሩ ላይ ስለሚባርክ አብሮ ተገኝቶ ነው፤ አለው።

ክቡራን አንባብያን አስተዋላችሁን? ስለዚህ ስናስቀድስ የሚያስቀድሱት ቅዱሳን ሁሉ ጭምር ናቸው። የበቁት ያዩዋቸዋል፤ በቅዳሴ ጸሎታችን ላይ "ዝ ውእቱ ጊዜ ባርኮት ወዝ ውእቱ ጊዜ ዕጣን፤" ይህ የማመስገን ጊዜ ነው፤ የዕጣን ጊዜ ነው፤ ብለን እናመሰግናለን። በተጨማሪም "ተውህቦ ምሕረት ለሚካኤል፥ ወብስራት ለገብርኤል፤. . . ተውህቦ ልቡና ለዳዊት፥ ተውህቦ ጥበብ ለሰሎሞን፤ እያልን እያንዳንዳቸውን ቅዱሳን እያነሣን ስጪዉን አክባሪዉን በከበሩት በቅዱሳኑ በኩል እናመሰግነዋለን። በቅዳሴው ጊዜ ዕጣኑን የምናሳርገው እኛ ብቻ አይደለንም፤ እነዚያ ቅዱሳንም ናቸው እንጂ። ይህንን ስለምናውቅ ከእመቤታችን ጀምሮ ቅዱሳንን ሁሉ እናመሰግናለን። መልክአ ቁርባንም ላይ እናነሣቸዋለን፤ "ሰላም ለኪ" ከሚለው ጀምሮ "ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕት እለ አዕረፍክሙ በሃይማኖት፤"፣ "ሰላም ለክሙ ጻድቃን ዛቲ ዕለት ኵልክሙ፤" እያልን በዚህች ዕለት ያረፋችሁ ቅዱሳን ሁሉ ለእናንት ሰላምታ ይድረሳችሁ፤ እናንተ ለእኛ ጸልዩልን፤ እያልን እንጠራቸዋለን። እነሱም እያንዳንዳቸው ለኛ ይጸልያሉ፤ ያማልዱናል።

ቅዳሴውን በሙሉ ማስታወስ ይከብዳል እንጂ ከዳር እስከ ዳር ብናየው ቅዱሳን እንዳሉበት እንረዳለን። ለእያንዳንዱ ቅዱስ በዚያ ሰላምታ እንሰጣለን፤ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓቷ ምን ያህል እንደሆነ እንይ። ለቅዱሳኑ ብቻ አይደለም ሰላምታ የምንሰጠው፤ ዲያቆኑ "ተአምኑ በበይናቲክሙ፤" ሲለን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ሰላም እንባባላለን። ለክርስቶስ ምስጋና እናቀርባለን፤ አምልኮ እናቀርባለን፤ እንሰግዳለን። እሱም ይባርካል፤ ይለውጣል፤ ያነጻል፤ ይቀድሳል፤ ይቅር ይለናል፤ ይዋሐደናል። እኛን በመንፈስ አብራችሁ ተሠራላችሁ ያለው ለዛ ነው። ስንጸም፣ ስናስቀድስ ከእነዚሁ ቅዱሳን ጋር በመንፈስ አብረን እንሠራለን፤ መሠራት ማለት ይህ ነው። አሁንም ከእነርሱ ጋር እንድንሠራ እግዚአብሔር በቸርነቱ

ይርዳን፡፡ በእውነት ከዲያብሎስና ከሰራዊቱ ማኅበር ጽዋ ከመቆጠር በቸርነቱ ያድነን፡፡

ስለዚህ በእኛ አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት ስንል አስተዳደራዊ ሳይኾን ምስጢራዊ /sacramental/ ማለትም ሥርዓተ አምልኮታዊ ነው፡፡ አንድነቷም የሚታየው ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም፣ አብሮ በማስቀደስ፣ ኪዳኑን በማድረስ፣ በመቁረብና በመሳሰሉት ነው፡፡ አንድ ሰው ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲናገር ስለ እነማን ሁሉ እየተናገረ ነው ማለት ነው? ስለ ቤተ ክርስቲያን ስንናገር ስለ ቅዱሳን ሁሉ ነው የምንናገረው፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ስንናገር ስለ ክርስቶስ ነው የምንናገርው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር የተማሩ ሰዎች የሚፈጥሩዋት የሰዎች ስብስብ /comminu-ity/ አይደለችም፡፡ በኾነ ነገር ዙሪያ የተደራጁ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ወይም አንድነት ማለት አይደለም፡፡ በመረጡት ሰው እየተዳኙ ወይም እየተመሩ የሚሄዱበት አንድ ስብስብ ማለት አይደለችም፡፡

የቤተ ክርስቲያን ምስጢር ሊገባን ያስፈልጋል፤ ቤተ ክርስቲያን ብለን የምንጠራት በምድር ላይ በዕውቀት፥ ቤተ ክህነት በሚባል መዋቅር የምትመራ አስተዳደራዊ ተቋም ማለታችን ብቻም አይደለችም፡፡ ቤተ ክህነት በምድር ያለነው ክርስቲያኖች ይህን ምስጢር እያወቅንና እየተመገብን እንድንኖር የሚረዳ ተቋም ነው፡፡ ቤተ ክህነት ቤተ ክርስቲያን ሳይኾን ምእመናንን የሚያስተበብር፣ የሚመራ ምድራዊ ተቋም ነው፡፡ አገልጋይ ካህናትንና ምእመናንን የሚያመጋግብ፣ ንዋያተ ቅዱሳትንና ሌላውንም የቤተ ክርስቲያን ሀብት የሚያስተዳደር አካል ነው፡፡ ስለ ቁሳዊውና ስለ ሰዎቹ የተደራጀ መዋቅር ነው እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አጠቃሎ የሚይዝ አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን እና በቤተ ክህነት  መካከል ያለው ልዩነት ግልጽ ሊሆን ያስፈልገዋል፡፡ ቤተ ክህነት አስተዳደራዊ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ምስጢራዊ ናት፤ ሃይማኖታዊ ናት፤ ለዚህ ነው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን የምንለው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንል የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ማለታችን እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንል በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ያለውን አስተዳደር ያካትታል፡፡

ከመጠሪያነት ባለፈ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ከዚያ ያለፈችና ሰፊ ሃይማኖታዊ ምስጢራትን የተሸከመች መሆኑን ማወቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፯፥፳-፳፫ እንዲህ የሚል ቃል አለ፡፡ "ሁሉ አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፡፡" ከፊቱ ስላሉት ነው ጌታ እንደዚህ ያለው "ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ በእኔ ስለሚያምኑት ስለ ሁሉም ነው እንጂ፤" አለ፡፡ "አንተ እንደላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፤" ይልና "እኛም አንድ እንደሆን፥ አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ፥ አንተም በእኔ ስትሆን በአብ ፍጹም አንድ እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤" በማስተዋል ላነበበው "እኛም አንድ እንደሆን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤" ይልና "እኔም በእነርሱ፤" ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን አንድነት ማለት እርሱ በእኛ ውስጥ ሲኖር ነው፡፡ ይህ አስተዳደሩን የሚመለከት አይደለም፤ ሃይማኖታዊና ምስጢራዊ ነው የምንለው ለዚህ ነው፡፡ አንድነት ማለት ክርስቶስ በእኛ አድሮ ክርስቶስ ካደረባቸው ቅዱሳን ጋር አንድ ስንሆን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚለው አስተዳደራዊ ሳይኾን ሃይማኖታዊ የሚሆነው በዚህ ነው ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ክርስቶስ እየተናገረ ያለው በጊዜው አብረውት ስለነበሩት ብቻ ሳይኾን ለምሳሌ እኛ ክርስቶስ በምድር ላይ ተገልጾ በሚያስተምርበት ወቅት አልነበርንም፤ ብዙ ሰዎች አልነበሩም ግን በሥጋዌው፥ ሰው በመሆኑ ስለ እኛ ያ ቀረበው ጸሎት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁላችንም ላይ አድሮብን አንድ እንድንሆን ይርዳን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "እኛ ሁሉን እንማርካለን፤ የክርስቶስ ልብ አለንና፤ እንዳለው ክርስቶስ በሁላችንም ላይ ቢያድርና ሁላችንም ክርስቶሳዊ ሀሳብ ቢኖረን መለያየትና መከፋፈል ባልተፈጠረም ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ቅዱስ ዮሐንስም ክርስቶስ አድሮባቸው ሳለ ሊጣሉ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም በእነርሱ የሚሠራው ክርስቶስ አንዱ ክርስቶስ ስለ ኾነ እንዴት ሊለያዩ ይችላሉ? ፈጽሞ አይችሉም፡፡ ተመልከቱ እኛ ክርስቶስ በሁላችን ቢያድር ልንለያይ እንችላለን እንዴ? አንችልም፡፡ የምንለያየው እኛ ከክርስቶስ ስለ ተለየን ነው፡፡ ይህን በሚገባ ማወቅ አለብን፡፡ ክርስቶስ በእኛ ከሌለ ተመልከቱ እንግዲህ ሥጋዊ ደማዊ አስተሳሰባችንን ይዘን፥ በዚህ ዓለም የተማርናቸውን ትምህርቶች መሠረት አድርገን፥ የዚህን ዓለም መርሆች እያጣቀስን እንዲህ መሆን አለበት እንዲህ መሆን የለበትም ብንል ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መፍትሔ ልናመጣ አንችልም፡፡ እኛ ራሱ ከክርስቶስ አንድ ሳንሆን ምንም ዓይነት አንድነት ልንፈጥር አንችልም፡፡